17/6/07 ዓ.ም

## በዘመኑ የነበሩ ሌሎች ወገኖች ስለዚህ መጽሐፍ ምን ይላሉ?

ዶክተር ጥበበ ከጉርሱም አንሥቶ እስከ ሐረር የተጓዘባቸው - የልደት እና የዕድገት፥ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት - ጉዞው (የጉዞዬ 9%) ቀደም ሲል እንደ ነበርነው እንደ ብዙዎቻችን የኢትዮጵያ ልጆች ጉዞ ያለ ነበር፡፡ ለቅድመ-ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ወደ አፄ በዕደማርያም ትምህርት ቤት ከመጣበት ከ1962 ዓ.ም አንሥቶ በ1977 ዓ.ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ-ምረቃ ተማሪ ሆኖ "በሰፈራ" ፕሮግራም ወደ ጉምላክ እስከ ዘመተበት ጊዜ ድረስ ያለው የ15 ዓመታት ጉዞ ግን (የጉዞዬ 51%) በተለይ "የጥበበ ትውልድ" ጉዞ ታሪክ ነው፡፡ በእነዚያ ዓመታት ውስጥ፥ ጥበበ - በአዲስ አበባ፥ በደደር፥ በቆላድባ፥ በአማኑኤል የአእምሮ ሆስፒታል፥ በበዴሳ፥ በጅጅጋ፥ በአስመራ - ዋትቷል፡፡ የዛሬው "ዶክተር ጥበበ" (የጉዞዬ 40%) የዚያን ዘመኑን 'ጥበበ'፥ "ግራ በተጋባ ዘመን የሚኖር ግራ የተጋባ ሰው" ይለዋል፡፡

እውነቱን ለመናገር፥ ያ ትውልድ ግራ የተጋባ እና ግራ ያጋባ ብቻ አልነበረም፡፡ ያ ትውልድ ከእርሱ በፊት የነበሩትን ትውልዶች ውዝፍ ዕዳ ያወራረደ፥ ከእርሱ በኋላ የሚመጡትንም ትውልዶች ዕጣ ፈንታ ለመቀየር እራሱን በመሥዋዕትነት የማገደ፥ ባርኔጣችንን በአክብሮት ልናነሣለት የሚገባ፥ ትውልድም ነው፡፡ ስለዚያ ትውልድ የሚናገሩ መጻሕፍት እጄ ሲገቡ - ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ብቻ - ይሄ አራተኛዬ መሆኑ ነው፡፡ በሁሉም ውስጥ፥ 'የጥበበ ትውልድ' የከፈለውን ዋጋ ከፍተኛነትና እንዲሁም "ለሚወድዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ የሚያደርግላቸውን" የእግዚአብሔርን መግቦት (Providence) ጥልቀት አይቼባቸዋለሁ፡፡ ለዚህ ነው እንደዚህ ዓይነቶቹን መጻሕፍት እያሳደደ እንዲያነብባቸው የዛሬውን ትውልድ የምንተጉተው፡፡

*በቀለ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)*

"ጉዞዬ፡- ዝብርቅርቁ ሕይወቴና መለኮታዊው ጸጋ" በሚለው መጽሐፉ፣ ዶ/ር ጥበበ አሸቴ ትምህርታዊ፣ ጠቃሚና ገንቢ የሆነ እውነት አካፍሎናል። ተቃራኒ በሆነው የሃይማኖትና ዘመናዊ ትምህርት፤ የገጠርና የከተማ ሕይወት፣ ያለውና የሌለው የባህል ክስተት ውስጥ ማደግ ወጣቱን ትውልድ ምሕዋሩን (ኦርቢቷን) የሳተች ኮከብ እድርጓት እንደ ነበር ከጥበበ ሕይወት መረዳት ይቻላል።

በአፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ ብዙ ባልተመለሱ ጥያቄዎች የሕሊና ነውጥ ያደጉ ኢትዮጵያውያን፤ ሥር ነቀል በሆነው አብዮት የሃገሪቱ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ኢኮኖሚና የኅብረተሰቡ አንድነት ምስቅልቅሉ ሲወጣ የግለሰቦችም ሕይወት ዝብርቅርቁ ወጥቷል።

ሕይወቱ ትርጉም ባጣበት ወቅት፣ ማርክሲዝም፣ መጠጥ፣ ዳንስና ጭፈራ ሳይሆን፣ ክርስቶስ ኢየሱስ የመኖር ትርጉምንና የአእምሮን ሰላም እንደ ሰጠው ጥበበ አካፍሎናል። በባህላችን ሕይወቱን በግልጽ በጽሑፍ የሚያካፍል ሰው ማግኘት የተለመደ አይደለም። ዶ/ር ጥበበ በኃጢአትና በጸጋ የተላበሰ ሕይወቱን በማካፈል ለአምላኩና ለወገኖቹ ያለውን ፍቅር ገልጿል።

እኔም የእርሱ ትውልድ ተካፋይ ስለ ሆንኩ ያለ ዕቅድና ዝግጅት፣ እንዲሁም ያለ ሕዝብ ፈቃድ የሚካሄድ ለውጥ የሚያመጣውን የሕይወት ቀውስ ከዶ/ር ጥበበ ጽዋ ጠጥቻለሁ።

መጽሐፉ ከሌሎች ስሕተት ለመማር ተስፋ ላጣ፣ ተስፋን የሚሰጥ፣ የተነሣንበትንና ያለፍንበትን፣ መጥፎና ጥሩ ትዝታዎችን ወደ አእምሮ የሚያመጣ፤ ከጅጅጋ እንሥቶ አሜሪካ የሚያስገባ የሕይወት ጉዞን፣ የአምላከን ታማኝነት፣ ጸጋና ፍቅር የሚያሳይ ነው።

*ዶ/ር ዓለማየሁ መኮንን*

ዶ/ር ጥበበ በሚያስገርም ግልጽነትና ሐቀኝነት ግለ-ታሪኩን ያተተበትን ‹‹ጉዞዬ፡- ዝብርቅርቁ ሕይወቴና መለኮታዊው ጸጋ›› ብሎ የሰየመውን መጽሐፍ ለንባብ ሲያቀርብልን በተጓዳኝም በዛን ዘመን የነበረውን የብዙ ወጣቶች ሕይወት ግራ ያጋባውንና ለማያስፈልግ የሕይወት መሥዋዕትነት የዳረገውን የዘመኑን የፖለቲካ ሁኔታም በመጠኑም ቢሆን አሳይቶናል፡፡ ያ ትውልድ በዘመኑ ዋጋን የከፈለ ብቻ ሳይሆን፣ የአገሪቱን መጪ ሁኔታዎች ያሁኑንም ሂደት ጭምር በሁሉም አቅጣጫዎች የወሰነ ትውልድ ነበር፤ ነውም።

ይህን መጽሐፍ ያነበብኩት ከትውስታ ጋር ነው፡፡ በተመሳሳይ ወቅት ግን በጣም በተለያዩ ጎራዎች፣ ሆኖም ደግሞ እጅግ ውሱን ትውውቅ የነበረን የአግዜር ሰላምታ የምንለዋወጥ የቀድሞ የቀ.ኃ.ሥ.ዩ. በኋላ የአ.አ.ዩ. ተማሪዎች ነበርን። ጥበበ የማርክሲስት ሌኒኒስት ፍልስፍና በሚያቀነቅኑ ተማሪዎች መሀል እኔ ደግሞ የወንጌላውያን ክርስትና እምነት በሚያራምዱ መሀል አንዳችን በተዘበራረቀ ሕይወት፣ ሌላችን በተረጋጋ ሕይወት አልፈናል። ይህን መጽሐፍ ሳነብ በሚገርም ሁኔታ የታሪክ ፍሰት የሚቆጣጠረውን የእግዚአብሔርን ማንነት በውስጤ እያደነቅሁ ለሚቀበሉት የማዳን ጸጋው ተገልጦበት አይቻለሁ።

በዚህ ዘመን ያሉ ወጣቶች በዛን ወቅት የነበረውንና የአሁኑን (ፈረንጆች እንደሚሉት) ‹ሮድ ማፕ› የቀየሰውን ሁኔታ ከተለየ አቅጣጫ ለመገንዘብ ይህን መጽሐፍ ማንበብ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ጥበበ፦ የጠበቀህን፣ ወቅቱን ጠብቆ ያዳነህን የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለመጻፍ ያበቃህ ብቻውን እውነተኛ የሆነው እግዚአብሔር ይባረክ።

ዓለምባዘዘው (ዶ/ር)

በታሪክ ተመራማሪ አእምሮ የተዋቀረ እውነተኛ የሕይወት ታሪክ ነው፡፡ ውሉን ማግኘት ከሚያዳግት ከተጠላለፈና ከተወሳሰበ ሁኔታ በጌታ ኃይል የተፈታችን ሕይወት ምስክርነት የያዘና በተመሳሳይ የሕይወት ታሪክ ውስጥ በማለፍ ላይ ላሉ ትምህርት የሚሰጥ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው፡፡

ዶ/ር ጥላሁን ማሞ



**መታሰቢያነቱ፡-**

በለጋ እድሜው በሞት ለተለየኝ ለወንድሜ

**ጥርኝ እሸቴ**

## ምስጋና

በመጀመሪያ ስንቱን ፈፋ አሳልፎ፣ በሰልፌ ተሰልፎ፣ ምሕረት በተሞላበት የፍቅር ክንዱ ሸሽጎ፣ ለዚህ ወቅት ላበቃኝ አምላኬ ለእግዚአብሔር ምስጋናና ክብር ልሰጥ ይገባኛል።

በመቀጠል የእንግሊዘኛውን ቅጂ አንብቦ፣ ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎች፣ በተለይም፣ ለወጣቱ ክፍል፣ ለበፊቱም ቢሆን ለአሁኑ፣ እንዲደርስ ወደ አማርኛ እንዲተረጎም ላሳሰበኝም ሆነ ተግባራዊ እንዲሆን ብርቱ ድጋፍ ለሰጠኝ ለጸንጋፋው ጋሽ ሚሊዮን በለጠ ከጠለቀ ስሜትና አክብሮት ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ ።

እንዲሁም ባላሰለሰ መልኩ ብዙ ጊዜ ወስዶ በጥራትና በትጋት ጽሑፉን ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ለተረጎመልኝ ለዳግማዊ ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አሰጣለሁ።

በድካሜ ላልተለየችኝና የዕምነት አርበኛ ለሆነችው ለባለቤቴ አዜብ ተሰማ፣ ለልጆቼ ሣሙኤል፣ ሕሊና እና ጸጋም እንዲሁ።

በመጨረሻም እከሌ ብዬ ለመጥራት ለማልችለው ታሪኬን ከማስተምረው ጋር አያይዤ ባቀረብኩ ቍጥር በመሳብ እንድጽፈው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ላደፋፈረሩኝ የውጭ አገር የዩኒቨርስቲ ተማሪዎቼ ልባዊ ምስጋናን አደርሳለሁ።

መከራ ባሳየኸን ዘመን ፈንታ፥
ከፉም ባየንባቸው ዘመኖች ፋንታ ደስ ይለናል።
(መዝ. 90፡15 )

በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ፤ ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት፥ ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ፥ እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፥ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ። (ሮሜ 5:20-21)





# ጉዞዬ፡-

# ዝብርቅርቁ ሕይወቴ እና መለኮታዊው ጸጋ

ዶ/ር ጥበበ እሸቴ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

Originally written in English under the title of
*Crazy Life and Crazy Grace* by Professor Tibebe Eshete
Copyright© Tibebe Eshete February 2014, Michigan, U.S.A.

Amharic Edition of this book is published by SIM Publication
P. O. Box 127
Addis Ababa, Ethiopia

Printed by SIM Press
P. O. Box 127
Addis Ababa, Ethiopia

**በግልጽ ካልተመለከተ በቀር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ከ1954 ዓ.ም ትርጉም የተወሰዱ ናቸው።**

March 2014

የመጀመሪያው እትም፡- ጥቅምት 2007 ዓ.ም (2014)
ትርጉም፡- ዳግማዊ ውቤ
አርትዖት፡- ዘነበ ገብረሐና

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING





## ማውጫ

መግቢያ ..... 8
የየዋህነቱ ዘመን፡- ለጋ ልጅነት ..... 11
በሐረር የነበረኝ የትምህርት ቆይታ ..... 25
ትምህርትና የልጅነት ሕይወት ..... 28
የቀድሞ የዩኒቨርስቲ ሕይወት ..... 35
በተንሳፋፊ ዓለም ውስጥ መኖር ..... 46
ከደደር ወደ ዩኒቨርስቲ ..... 53
ዘመቻው ..... 63
ከዘመቻው መልስ ..... 79
በግጭት ውስጥ መኖር ..... 87
ያልታሰቡ ቀውሶች ..... 89
የጅጅጋው ውስብስብ ሕይወትና ቀጣዩ ሁኔታ ..... 105
እንደገና ወደ ዩኒቨርስቲ ..... 134
በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ማስተማር እና ተዛማጅ ተሞክሮዎች ..... 147
አዲሱ የአቅጣጫ ቅያሪ - ትልቁ አስደናቂ ክስተት ..... 154
ወደ መረዳቶች መምጣት ..... 174
የእግዚአብሔርን ኃይል ማግኘት ..... 182
መልስ ወደ አሥመራ፡- የተለወጠው ሰውዬ ..... 189
የጋብቻ ሕይወት ..... 193
ወዳጆችን በወንጌል መድረስ ..... 211
ወደ አሜሪካ መምጣቱ - ከፍታዎች እና ዝቅታዎች ..... 213
የወርልድ ቪዥን ተሞክሮዬ ..... 223
ወደ አሜሪካ መመለስ - መሰናከሉን ማሸነፍ ..... 232
ያልተለመዱ የፈተና ጊዜያትን መጋፈጥ ..... 244
የማጠቃለያ አስተያየት ..... 255
የግርጌ ማስታወሻዎች ..... 259

## መግቢያ

የሕይወቴን ታሪክ እንድጽፈው ያበረታቱኝ ሰዎች፣ ወዳጆቼን፣ የሥራ ባልደረቦቼን እና የገዛ ተማሪዎቼን ጨምሮ፣ በርካቶች ናቸው። "ለአንባቢዎቼ ምን ጥቅም ይተውላቸዋል፤ ደግሞስ እንዲያው በአጠቃላይ ታሪኬን በመጽሐፍ የማዘጋጀቱ ዓላማ ምን ይሆናል?" የሚሉትን ጥያቄዎች ሳወጣና ሳወርድ መቆየቴ ታሪኬን እጽፈው ዘንድ ለረጅም ጊዜ እንዳቅማማ አድርገውኛል። ዓመታት በነጎዱና ባሳለፍኳቸው ዘመናቴ ላይ አብልጬ ባሰላሰልኩ ቍጥር፣ ግራ አጋቢ ነገሮች፣ ጉዳቶች፣ እና ውጣ ውረዶች ሆነው በሕይወቴ ውስጥ ሲያጋጥሙኝ ለነበሩት ነገሮች ሁሉ አንድ ሁለት ብዬ በጽሑፌ ልተርክላችሁ የምችለው የትኛውም ነገር ቢኖር፣ የእግዚአብሔር ጸጋ፣ ታጋሽ ፍቅሩ፣ እና የጠበቀችኝ እጁ ገናና መሆኗን ብቻ ነው። ዛሬ ላለሁበት ለመድረሴ ምክንያት ሊሆን የሚችለው ዕድለኛ መሆኔ ብቻ ነው እንጂ፣ ጥበበ ማለት ተራ ከሆኑ ቤተሰቦች የተወለድኩ፣ አዳጋች በሆነ የሕይወት ተግዳሮት ውስጥ ያለፍኩ፣ ሕዝቤ እና በዘመኔ የነበረው ትውልድ ያሳለፈው ግጭቶች ውስጥ የኖርኩ፣ አሰቃቂ በሆኑ 17 የኮምዩኒዝም ዓመታት ችግሮች እና እሳቶች ውስጥ ያለፍኩ ሰው ነኝ። በውጤቱም፣ የሕይወት ታሪኬን በተቻለ መጠን ምንም ሳልደብቅ ለመንገር ራሴን አሳመንኩ።

በ13ኛው ምእተ ዓመት ከተነሡት ኢትዮጵያዊው ወንጌላዊ ከቅዱስ ተክለሃይማኖት ዘር በቀጥታ የተገኘን ነን ብለው ከሚያምኑ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ካላቸው ቤተሰቦች የተወለድሁ ብሆንም፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ በነበርኩበት ወቅት የእግዚአብሔርን መኖር ከጄ ጊዜዬን መስመር ባጣ አቅጣጫ ሄጄበታለሁ። እግዚአብሔርን የካድኩት እኔው ብቻ ሆኜ ብቀር ምን ነበረበት እያልኩ እስከመኝ ድረስ ከራሴ አልፌ በርካታ ወዳጆቼም እንዲሁ ፈጣሪን እንዲክዱ





አቋሜን አካፍያለሁ፣ በትምህርት ገበታም ላይ በግልጽነት የእግዚአብሔርን አለመኖር አስተማርኩ፣ እነዚህም ሳይበቁኝ ጭራሽ በሕይወቴ ዘይቤዬ ውስጥ 'ሃይ' ባይ ፈጣሪ እንደሌለው ሆኜ ተመላለስኩ። እኔ እንዲህ ዓይነት ሰው ልሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ግን ያገኘኛል ብዬ ባልጠበቅሁበት በጉምላክ ጫካ ውስጥ በፍቅሩ እና በጸጋው አገኘኝ፣ የራሱም አድርጎ አስቀረኝ። ይህም ጫካ የሚገኘው በደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ ክልል ራቅ ያለች መንደር ውስጥ ሲሆን፣ መንግሥት በገንዘብ በሚደግፋቸው የመልሶ ማቋቋም ዝግጅቶች ሽፋን የዩኒቨርስቲው ማኅበረሰብ ፖለቲካዊ ግዞትን ሲያሳልፍበት የቆየበት ስፍራ ነበር። በዚያን ጊዜ የዩኒቨርስቲ መምህር የነበረ አንድ ሰው በክርስቶስ ያለውን እምነት፣ በሕይወቱ ያጣጣመውን የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ እና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለውን የግል ግንኙነት መሰከረልኝ። ጌታን እንደ ግል አዳኜ ለመቀበል የወሰንኩት ዘግይቼ ይሁን እንጂ፣ በዚያ አስደናቂ አጋጣሚ ወቅት የተቀበልኩት ልቦናን የሚያበራ ማስተዋል የኋላ ኋላ ሕይወቴ ለተጓዘበት አስደናቂ የአቅጣጫ ለውጥ ወሳኝ ነገር ነበር።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ታሪኬን የማስቀምጥላችሁ አስቀድሜ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል ስላደረግሁት መሰጠት እና ከዚያም ቀጥሎ ስላለው የሕይወት ጉዞዬ ዘርዝሬ በመተረክ ቅደም ተከተሉን ጠብቄ ነው። ለማድረግ የፈለግሁት ግልጽ እና ሐቀኛ የሆነውን የሕይወቴን ቅጂ መስጠት እንጂ፣ ሂሳዊ አስተያየቶችን እና በሕይወቴ የተለያዩ እርከኖች ውስጥ የገጠሙኝን ክስተቶች ማብራራት አይደለም። የሕይወቴን ተሞክሮዎች ልክ ያን ጊዜ እንደ ነበረው አድርጌ ለማቅረብ፣ የነበሩኝንም ስሜቶች እና የዘመኑን አስተሳሰቦች በወቅቱ እንደ ነበርኩበት አድርጌ ለማቅረብ የቻልኩትን ያክል እጥራለሁ። እውነተኛውን የሕይወቴን ገለጣ አሁን ጊዜ ላይ ያለሁበት አተያዬ ሽፋፍኖ እንዲያመለክት ላለመፍቀድ የተቻለኝን ያክል ጥንቃቄ አደርጋለሁ። በማንበብ ላይ ያላችሁት የሕይወት ታሪኬ በእኔ ዘመን የነበረው ትውልድ ያለፈባቸውን ሁኔታዎች፣ በጊዜው የነበሩትን መደናገሮች እና ውስብስብ ጎዳናዎች እንዲያንጸባርቅ እፈልጋለሁ። ታሪኬ የእኔ ዘመን ላይ የነበረውን ትውልድ ታሪኮች ሁሉ ይወክላል ብዬ ለማመን ባልደፍርም፣ በርካታ ቍጥር ካላቸው ሊነገሩ ከሚገባቸው ተመሳሳይ መጠነ-ሰፊ ታሪኮች ውስጥ አንደኛው አነስተኛ የሥዕል መግለጫ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

ከሁሉ በላይ፣ መጽሐፉ እንዲገልጸው የምፈልገው ነገር ቃላት ሊገልጹት የማይችሉትን የእግዚአብሔር የመዋጀት ፍቅር፣ የማያልቀውን ምሕረቱን፣ እና የእርሱን የሚለውጥ ኃይል ነው። አንባቢዎቼ የተዘረጋውን የእግዚአብሔርን ክንድ በታሪኩ ውስጥ ፍንትው ብሎላቸው እንደሚያዩት ተስፋ አደርጋለሁ። በዚህም ምክንያት በሕይወቴ አንደኛው ነጥብ ላይ የተስፋ-ቢስነትን ስሜት ያሳለፍኩ እንደ መሆኔ፣ በዚሁ ዓይነት የስሜት ጥልቀት ውስጥ ላለ ሰው የእርሱን የመታደግ ኃይል እንደሚያገናዝብ ከልብ የሆነ ተስፋ አለኝ። ክብር እና ውዳሴ ለሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር እንዲሆን እፈልጋለሁ። ሰዎች ከስሕተቶቼ መማር ከቻሉ ወይም እግዚአብሔር በእኔ ሕይወት ከሠራቸው ነገሮች አንዳች ዓይነት መነሣሣትን ማግኘት ከቻሉ እሰየው ነው። ያንን እንደ አንደኛው የጥቅም ዘርፍ ልቈጥረው እችላለሁ።





# የየዋህነቱ ዘመን፡-

## *ለጋ ልጅነት*

የልደት ቀኔን አስቦ ለመዋል በዓል የምደግስበት አጋጣሚ መኖሩን እስከማላስታውስ ድረስ፣ የተወለድኩት መቼ እንደ ሆነ በትክክል አላውቅም። ዘግይቼም ቢሆን ግን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ በገባሁ ጊዜ የልደት ቀኔ መቼ ሊሆን እንደሚችል አስቤ መገመት ነበረብኝ። ፋኖን ቢራ[1] ተብሎ በሚጠራው የጉርሱም አካባቢ ከሌሎቹ ጋር ሲነጻጸር መካከለኛ ገቢ ከነበራቸው ቤተቦቼ የተወለድኩበት ቀን መስከረም 11 ቀን 1945 ዓ.ም እንዲሆን መረጥኩ። አባቴ እሸቴ ኃይሉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የትምህርት ትውፊት ውስጥ ገፍቶ የተማረ ሰው ነበር። በቁመቱ ረዘም ያለና ከሌሎቻችን ይልቅ ነጣ ያለ ገጽታ የነበረው ሲሆን፣ 'እሸቴ *ቃዲ*'፣ 'እሸቴ *ጠጁ*'፣ እና '*ደብተራ* እሸቴ' በሚሉት በርካታ ቅጽል ስሞቹ ይታወቃል።[2] እናቴ ቦጋለች ዋቅቶላ ሁልጊዜም ብልህ እና ደስተኛ ሴት ትሁን እንጂ፣ ከአባቴ ጋር ስትተያይ ብዙም ታዋቂ ያልሆነች፣ አንዳንድ ጊዜ የምትቆጣ እና የምትዋልል ነበረች። እርሷ ምንም ዓይነት መደበኛ የቀለም ትምህርት አልተማረችም፤ ለመማርም ጨርሶ ፍላጎት አሳይታ አታውቅም።[3] ይሁን እንጂ፣ የሙዚቃ ተሰጥዖ ስለ ነበራት ዝማሬዎችን ለማቀናበር፣ የሚመጥነውን ዜማ ለማምጣት እና ሳትዘጋጅም ቢሆን ያንን ለመዘመር ባላት ችሎታ እደነቅ ነበር። እድገቴ በታላቅ እኅቴ መሠረት እና ብዙ ጊዜ ቤተሰቡ ጥርኝ ብሎ በሚጠራውና ቆየት ብሎ ከዚህ ዓለም በሞት በተለየን በታናሽ ወንድሜ መላኩ መካከል ሆኜ ነው።

ያደግሁባት ከተማ መካከለኛ የቆዳ ስፋት የነበራት ስትሆን፣ እንደ እስቴንኮ እና ቁንድዶ ባሉ የሰሜን ምዕራብ እና ኢላለሚ ተብሎ እንደሚጠራው፣ በደቡብ እንደሚገኘው አካባቢ በውብ ተራሮች የተከበበች ነበረች። በከተማችን ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ሰዎች የተለያየ ቅይጥ የማኅበረሰብ ማንነት የነበራቸው ሰዎች ሲሆኑ፣ ይህም የሚያካትተው *ነፍጠኛ* ተብለው ይጠሩ የነበሩትን

አማራዎች፣ ኦሮሞዎችን፣ ሶማሌዎችን፣ አደሬዎችን (ሐረሬዎች)፣ እና አነስተኛ ቁጥር የነበራቸውን ጉራጌዎችን ነበር። ልጅ ሳለሁ ከሁሉም ቅይጥ ቡድኖች ውስጥ ጥቂት ጥቂት ጓደኞች ኖረውኝ አድጌያለሁ። በመሠረቱ፣ በቤታችን ቅጥር ግቢ ውስጥ የቆሎምቢ ቤተሰቦች ተብለው የሚጠሩ ሶማሌዎች ስለ ነበሩ አሁን ድረስ ማሪያማ ቆሎምቢ፣ ኡመር ቆሎምቢ እና የመሳሰሉትን ዓይነት ስሞችን አስታውሳለሁ። በተጨማሪም፣ 'ማድሬሳ' በሚለው መጠሪያው ይታወቅ የነበረውን ባህላዊ የሙስሊሞች ትምህርት ቤትም በግልጽ አስታውሳለሁ። አብዛኞቹ አደሬ ተማሪዎች ማንበብና መጻፍን ለመማር የሚመጡበት ይህ ትምህርት ቤት ከቤታችን በትይዩ ይገኝ እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል። አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎቹን እነበኝና በዙር ሲማሩ፣ ደግሞም ሉሀ ወይም ኪታብ ተብሎ ይጠራ በነበረ ከእንጨት የሚሠራ ቁራጭ ላይ የጽሑፍ ችሎታቸውን ሲለማመዱ እያየኋቸው ስላደግሁ ተማሪዎቹ የቁርዓን ክፍሎችን ለመቅራት በሚሞክሩበት ጊዜ ይፈጠር የነበረውን ጩኸታቸውን አሁን ድረስ አስታውሰዋለሁ።

በዚያን ጊዜ በእርግጥም የካህናት መንደር በነበረውና ቄስ ኣምባ ተብሎ በሚጠራው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤት ውስጥ የለጋ ልጅነት ትምህርቴን ተከታትያለሁ። መሪ ጌታ ወይም መምሬ ተብለው የሚታወቁት አስተማሪያችን መጠሪያ ስማቸው መንግሥቱ ነው። ለእኔ በጣም አሰልቺ እና ድግግሞሽ በመሆኑ ምክንያት ቄስ ትምህርት ቤት መሄዴን መቼም ተደስቼበት አላውቅም። ትምህርት ቤቱ ልክ እንደ መዋዕለ-ሕጻናት ዓይነት ሆኖ የሚያገለግል ቢሆንም፣ የአማርኛ ፊደልን እና መሠረታዊ የማንበብና መጻፍ ክህሎትን ተምረንበታል። የምንቆጥረውን ፊደል ለና አንዳንዶቻችን በእጃችን እንይዘው የነበረውን የመዋዕለ-ሕጻናት መማሪያ መጽሐፍ ያዘጋጅ የነበረው ተስፋ ማተሚያ ቤት[4] ነበር። መምሬ መንግሥቱ ሲበዛ ለአስተማሪነት ጥሪያቸው የተሰጡና ድካም የማያውቁ ሰው የመሆናቸውን ያክል፣ ኃይለኛነታቸውም የዛኑ ያክል ነበር ማለት ይቻላል። ከቆዳ በተሠራቸው አለንጋቸው ክፉኛ ስለሚቀጡን፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት ቤታችን ውስጥ መጥፎ የነበረው ጊዜ እጅህን አውጣ የምንባልበት ጊዜ ነበር። ያ ማለት አንዳንድ ደንቦችን ጥሰናልና ግርፊያ ይጠብቀናል ማለት ነበር።

ተማሪን ጎበዝ የሚያደርግ የተለየ መድኃኒት አላቸው የሚባልላቸውንና ደብተራ ሠይፉ በመባል የሚታወቁን ቄስ በልጅነት ዘመኔ አስታውሳለሁ።





ከአንዳንድ ተክሎች እና ፈሳሾች ተዘጋጅቶ ሊሆን የሚችለው የመድኃኒቱ ጥቅልል አብሾ በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ መድኃኒቱን ወስጄው ይሁን ወይም አይሁን በትክክል አላስታውስም። ነገር ግን ለአንዳች ምክንያት በአባቴ ተመክሬ ደብተራውን ልጎበኛቸው ሄጄ እንደ ነበረ ግን ውል ይለኛል። በሰፊው ከሚነገሩት ነገሮች አንዱ አብሾ የወሰዱ ሰዎች በመጠኑ ከሰከሩ በፍቱንነቱ ምክንያት ሲበዛ ብሩህ ያደርጋቸውና ባልተገራ ማንነት ውስጥ ይሆናሉ የሚለው ነበር።

ከከተማዋ ወጣ ብሎ በጃኮቢን ካቶሊክ ሚስዮናውያን በተገነባውና አባ ያዕቆብ ትምህርት ቤት ተብሎ ይጠራ ወደ ነበረው የቀለም ትምህርት ቤት ገብተው ይማሩ በነበሩት ተማሪዎች ሁልጊዜ እቀና ነበር። በቄስ ትምህርት ቤት ምን ያክል እንደ ቆየሁ እርግጠኛ አልሁን እንጂ፣ ዘግየት ብሎም ቢሆን አዲስ ወደ ሆነው የመንግሥት ትምህርት ቤት ገብቼያለሁ። ስለ ትምህርት ቤቱ የማስታውሰው የትምህርት ቤቱ ርእሰ-መምህር ስለ ነበሩት አባ ሙሴ (ሙሴ ለማ ተብለውም ይታወቁ ነበር) እና ከትምህርት ቤት ውጪ ለሰማይ የምንዘምር እስኪመስል ጮክ ብለን እንዘምር ስለ ነበረው መዝሙር ነበር። እነዚህም መዝሙሮች በአብዛኛው ንጉሥ ኃይለ ሥላሴን - 'ኃይለ ሥላሴ ሐዋርያ፣ ይኑርልን ለክብራችን' እያልን የምናወድስባቸው ነበሩ። ረጅም የሆነው የማያስደስት ቀን ማለቁን የሚነግረን የቀኑ ምርጥ ጊዜ ባንዲራን ለማውረድ ሥነ -ሥርዐት የምንሰለፍበት ነበር። ልክ ሥነ-ሥርዓቱ እንደ ተጠናቀቀ፣ ምንም እንኳን ውኃ የማምጣት፣ ቤት የማጽዳት፣ መላላኮችን የመፈጸም እና ከአጋባር የሚግጡ መንጎቻችንን የመሰብሰብ ዘወትራዊ ሥራዎች ያሉን ቢሆንም፣ ወደ ቤት እንሮጥ ነበር። አንዳንድ ጊዜ የዘይቱን ፍሬዎችን ለመልቀም ወደ ቃሊም እርሻ ተደብቀን መሄዳችንም አልቀረም።

አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ በአባ ያዕቆብ ትምህርት ቤት ውስጥ ከቆየሁ በኋላ፣ በደቡብ ምዕራብ የከተማይቱ ጥግ ወደሚገኘውና ከቤታችን በመጠኑ ራቅ ወዳለ ሌላ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብቼ መማር ጀመርኩ። ልጆች ሆነን እንዋኝ ከነበረበት ከራሚስ ሐይቅ አቅራቢያ በሚገኘው በዚህኛው ትምህርት ቤት መማር የጀመርኩት ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ ሲሆን፣ እስከ 6ኛ ክፍል ድረስ እዚሁ ቀጠልኩ። በጉርሱም ከተማ እከታተለው የነበረውን ትምህርቴን በ1955 ዓ.ም በተቀሰቀሰው የኢትዮ-ሶማሊያ ጦርነት

ምክንያት አቋረጥኩ።[5] ይሁን እንጂ፣ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ያጠናቀቅሁት ሐረር ውስጥ በነበረው የራስ መኮንን ትምህርት ቤት ውስጥ ነበር።

በሕይወቴ ላይ የማይፋቅ አሻራ ካኖሩብኝ ነገሮች አንዱ በጉርሱም ማሃደጌ ነው። አስደሳች ከምላቸው ትዝታዎቼ አንዱ በላብ ምክንያት እጁ ሁልጊዜ እርጥብ የነበረው ትንሳይ ባይሳ፣ ሚሊዮን እና ብርሃን እንደሻው፣ ስንታየው ሌሌ፣ ዘውዱ ይጥና፣ እና ሌሎችም በርካታ ጎረቤት የልጅነት ጓደኞቼ ጋር የነበረኝ ጓደኝነት ነው። እኔ የታወቀ ሊቅ የነበርኩበትና 'ውራ ነኝ' እና 'ቀስት ነኝ' በማለት የተጫወትንበት ከረምቡላ ጨዋታ ተወዳጅ ከነበሩት ጊዜ ማሳለፊያዎቻችን አንደኛው ነበር። ታዲያ ወደ ቤታችን አምሽተን ስንሄድ ስላመሸንና ስላልተላላክን፣ አሊያም የዘወትር ሥራዎቻችንን ቸላ ስላልን ወደ ቤት ለመግባት ፍርሃታችን እንዲህ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም። ኢስቲንኮ የተባለውን በሰሜን ምዕራብ የከተማይቱ አቅጣጫ የሚገኘውን የሚስብ ኮረብታ መውጣት ሌላኛው ተወዳጅ ጊዜ ማሳለፊያችን ነበር። በዚያ ሰጋ እድሜ ላለነው ሕጻናት ፖለቲካን ማውራቱ ለምን እንዳስፈለገ ባላውቅም፣ እስከ ተራራው ጫፍ ድረስ መውጣት መቻል እና ፖለቲካን ጨምሮ ስለ ሕይወትና ዓለም ከሞላ ጎደል ሁሉንም ነገር ያለማቋረጥ መወያየት የተዘወተረና ትኩረታችንን የሚስብ ጉዳይ ነበረ። በቅርብ ጊዜ ስለ ታተመ አማርኛ መጽሐፍ እንነጋገርና ራሳችንን እናስደስት የነበረ ሲሆን፣ አፈንጋጭ ደራሲ አቤ ጉበኛ የኃይለ ሥላሴን አመራር በጣም ስለሚተች፣ ከምንወዳቸው ደራሲያን መካከል አንደኛው ነበር። ለዚህም ነበር በጣም ተጽዕኖ ፈጣሪ የነበረውንና 'አልወለድም' የተሰኘውን መጽሐፉን በዚያ ዕድሜያችን ያነበብነው። አንዳንድ ጊዜ ሙዲር፣ ላፍቶ፣ እና ፉኛን ሁጁባ ወደ ተሰኙ አጎራባች የገጠር ሰፈራዎች ዘንድ እንዲሁ ለመጫወት እና ለጀብዱ ስንል እንሄድ ነበር። ወደ ላፍቶ የምንሄድበት ጉዞ የሚሊዮን እንደሻውና የብርሃን እንደሻው አጎት ከሆኑት ጋሼ አምበርብር በረደድ እርሻ የተለየ ፍሬ የነበረውን ዘይቱን በርከት አድርገን ወደ ቤት የምናመጣበት ስለ ነበረ ውጤት ያለው ጉዞ ነበር። እርሳቸው የእድሜ አቻቸው ከነበሩት ሰዎች የተለየ የሆነ የአኗኗር ዘዬን በመከተል ያልተለመደ ባሕርይ ያላቸውና፣ ከአካባቢው የኦሮሞ ገበሬዎች ጋር ቋንቋቸውን እየተናገሩ፣ ደግሞም የአኗኗር ሁኔታቸውን ተላምደው ከኖሩ ጥቂት ሰዎች አንደኛው





ናቸው። ደግ ሰው መሆን ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ሁልጊዜ በጥልቀት የሚያስቡና የሚያወሩትን ባንገነዘብ እንኳን የእርሳቸው አኩዮች የሆንን ያክል ሐሳባቸውን ያካፍሉን የነበሩ የሚያስደንቁ እና የሚማርኩ ሰው ስለ ነበሩ፣ ማናችንም ደፍረን ባንጠይቃቸውም እንኳን፣ እንዴት ይህንን ማድረግ ቻሉ እያልኩ ግን ሁልጊዜ አደነቃለሁ። የእርሳቸው ባሕርይ በመጠኑ ወጣ ያለ እና ከባህሉ የተለየ እንደ ነበረ እስከናውቅ ድረስ፣ ልክ ጓደኞቻቸው የሆንን ያክል በውይይት ያሳትፉናል። ዘይቱናችንን እና ሌሎች ፍሬዎችን ከእርሳቸው እስካገኘን ድረስ፣ ከእርሳቸው ጋር መሆን እና መጫወት ያስደስተን ነበር።

ሲበዛ በጥሩ ሁኔታ ቤተሰቡን ትንከባከብ የነበረችው እናቴ ከቤት ውጪ ሥራ ባይኖራትም፣ ሁለቱም ወላጆቼ ግን ታታሪ ሠራተኞች ነበሩ። እናቴ ቤቱን በጠቅላላ ታስተዳድር የነበረው እኛን በመመገብና ላሞችን በማለብ ጭምር ሲሆን፣ አባቴ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ቤት የሚገቡት አምሽተው ነበር። በሩን ከማንኳኳታቸው በፊት መቃረባቸውን ምልክት ለመስጠት ሁልጊዜም ቢሆን "እእህ" ይሉ ነበር። ምናልባት በእርሳቸው ደስተኛ አልነበረች ይሆናል ከማለት ውጪ ሊገባኝ በማይችል መልኩ - መጣ ደግሞ በሚል ስሜት 'ኤጭ እቴ' በማለት እናቴ ለምልክቱ ምላሽ ትሰጣለች።



የ‹‹ተወዳጇ እናቴ›› ፎቶ

ልጆች እንደ መሆናችን፣ አብዛኛውን ጊዜያችንን ያሳለፍነው ከእናታችን ጋር ሲሆን፣ አባታችን ጥሩ ሰው፣ በጣም ሥርዐት የነበራቸው እና በራሳቸው መንገድ ሃይማኖተኛ የነበሩ ሰው ነበሩ። ሁላችንም የክርስትና አባት የነበረንና ለመድኃኔዓለም ከገባው ስለት የተነሣ የተወለድን ልጆች ስንሆን፣ በሚታይ መልኩ አይግለጠው እንጂ፣ ይወድደን ነበር። በዘመኑ የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን የነበሩት ጋሽ ንጋቱ አዳኙን ጌታ ወክለው የክርስትና አባቴ የነበሩ ሰው መሆናቸውን ያወቅኩት ዘግይቼ ቢሆንም፣ የእኔ ክርስትና አባት ራሱ መድኃኔዓለም ነበር። ጋሽ ንጋቱ ዘግየት ብሎ ወደ ሐረር በምዘዋወርበት ጊዜ በሕይወቴ ወሳኝ የሆነውን ሚና ተጫውተዋል።

በቤተሰባችን ላይ አንዳች አውዳሚ የሆነ ነገር ያጋጠመው እኔ ገና የ3ኛ

ክፍል ተማሪ ሆኜ ወላጆቼ በተፋቱ ጊዜ ነበር። ወደ ጋብቻው መፍረስ ያመሩትን ሁኔታዎች አላውቅም፣ ነገር ግን የማስታውሰው ነገር በአባቴ እና እናቴ መካከል ፍቅር ጠፍቶ እንዳልነበረ ነው። ታላቋ እኅቴ እና ታናሹ ወንድሜ ከእናቱ ጋር ለመኖር መረጡ፣ ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ ላብራራው በማልችለው ምክንያት እኔ ከአባቴ ጋር መሆንን መረጥኩ። ይህ ምርጫ ደግሞ በሕይወታችን መፃዒ ጎዳና ላይ ግዙፍ ልዩነትን አበጀ። ብልህ ተማሪ የነበረችው እኅቴ ከፍቺው በኋላ ሌላ ባል ያላገባችውን እናቴን ለመርዳት ስትል ትምህርቷን አቋረጠች። ታናሹ ወንድሜ ትምህርቱን ወለም ዘለም እያለ ስለሚማር ወደ ኋላ ቀረና በሥነ-ሥርዓት ወደ ትምህርት ቤት በቋሚነት መሄድ ሳይችል ቀረ። ይህ ግዴለሽ አመለካከቱ ትምህርት ቤት በነበረባቸው ቆይታዎች ሁሉ አብሮት የዘለቀ ባሕርይ ስለ ሆነበት፣ ከሌሎች የሕይወት ጉዳዮችም ጋር በተያያዘ ከ9ኛ ክፍል አልፎ መማር አልቻለም።

ወላጆቼ እንዲለያዩ የማልፈልግ ልሁን እንጂ፣ የዛኑ ያክል ሁኔታውን ለመቀልበስና ለማስተካከል የምችልበት ኃይልም ሆነ ተጽዕኖ ፈጣሪነት ሳይኖረኝ በመቅረቱ ለመለያየት ያበቃቸው ነገር ምን እንደ ሆነ ለዘመናት ሳላውቅ እንደ ተለያዩ ቀሩ። ይሄ ነው ብዬ መናገሩ ቸገረኝ እንጂ በወላጆቼ ግንኙነት ውስጥ አንዳች የጎደለ ነገር እንደ ነበረ አውቄ ነበር። ቡና ሲፈላ እንደ ዘመኑ ልማድ አንዳንድ ጊዜ ቡና ከሚያጣጡ ጎረቤቶች ጋር በመሆን እናቴ እና አባቴ በጋራ ጊዜ ያሳልፉ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። ከዚህ መልስ አብረው ጊዜ ያሳለፉበት ሁኔታ ትዝ አይለኝም።


ታታሪው አባቴ

ቦጋለች ዋቅቶላ፣ ዋቅቶላ ዴሬ፣ ዴሬ ሞቲ፣ እና ሞቲ ኢብሳ እስከሚሉት ስሞች ድረስ መሄድ እንድንችል እናቴ የዘር ማንዘሮቿን ስሞች ቀደም ብላ አስተምራናለች። እርሷ የተገኘችው ከሸዋ ግዛት የሰላሌ ኦሮሞ ትውልድ ዘር እንደ ሆነ ዘግየት ብሎ ቢገባንም፣ ስለ ማኅበረሰብ መገኛዋ አንሥታም ሆነ አስተያየት ሰጥታ አታውቅም። ይህ መገኛዋ ያን ጊዜም ሆነ ኋላ ላይ ለእርሷ ትርጉም ያለው ነገር እንደ ነበረ ወይም እንዳልነበረ በእኔ በኩል ምንም የማላውቅ





ሲሆን፣ እርሷም እንዲሁ ሐረር ተወልዳ እዚያው ያደገች በመሆኗ ራሷን ሁልጊዜም ሐረሪ አድርጋ ነበር የምትወስደው። እርሷም የምታውቀው፣ እኔም የኖርኩበት ዓለም ያ ሲሆን፣ ሁለቱ ታናናሽ ወንድሞቿም በኦሮሞዎች እና ሶማሌዎች ተይዞ የነበረውና ጭናክሰን አቅራቢያ የሚገኘው ግሪ ቆጨር፣ በአጭሩ ጌሪ በሚሉት ትንሽ መንደር ውስጥ እንደሚኖሩና "የጌሪ ልጆች" እንደ ሆኑ በኩራት ይናገሩ ነበር። ሽማኔ የነበሩት አባቷ ‹‹አካኮ›› ብለን እንጠራቸው የነበረ ሲሆን፣ የእርሳቸው አባት ደግሞ በአገር ማቅናት ተግባር በመሠማራት እንዲሁም በዚያን ወቅት ቀጠናው ላይ ሰላም ለማምጣት በንጉሥ ዳግማዊ ምኒልክ ከተላከው የራስ መኮንን ጦር ጋር ነፍጠኛ[6] ሆነው መጥተው ነበር። አያቴ በርካታ የተቀቀለ የፍየል ሥጋ የምንበላበት የተለየ እራት ግብዣ በዓመት አንድ ጊዜ ያዘጋጃሉ። ከቀደምት አባቶቻቸው ለእርሳቸው በውርስ የተላለፈ ትርጉሙና ፋይዳውን ለእኛ ለሕጻናቱ ያላብራሩትን አንዳች ዓይነት ሃይማኖታዊ ሥርዐት እያካሄዱ እንደ ነበረ ገምቼያለሁ። ስለ አያቴ የማስታውሰው በስተርጅና እድሜያቸው ውስጥ ሰካራም የነበሩበትን የሕይወት ዘይቤያቸውን ብቻ ነው። ባሕርያቸው በጣም በመሠረታዊ ሁኔታ እንዲለወጥ ያደረጋቸው ነገር ምን እንደ ሆነ ባላውቅም፣ የአልኮል ቀበኛ ሆነው አንዳንድ ጊዜ እስኪያሳፍረኝ ድረስ በከተማይቱ ጎዳናዎች ላይ እንደ ጅል ይዘዋወሩ ነበር። እርግጠኛ መሆን ቢያስቸግረኝም፣ ከፊሉ የሰካራምነታቸው ምክንያት ከተማዋን ወርሮ የነበረው የውጭ አገር የኢንዱስትሪ የሆነው ጨርቃ ጨርቅ የእርሳቸውን የቤት የጐጆ ምርት ከፉኛ በመጉዳቱ ሳይሆን እንዳልቀረ ይሰማኛል። ከዚህ ሌላ ሚስታቸው፣ አያታችን ወርቂቱ ጊፍቱ እኛ ሳናውቃቸው በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ስለ ተለዩ፣ ኀዘን እና ብቸኝነትም ለወፈፌነት ባሕርያቸው አስተዋጽዖ ያደረጉ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ።

አባቴ ተወልደው ያደጉት ሃይማኖታዊ ፋይዳ ከነበራቸው የአካባቢው ወረዳዎች አንዱ ከሆነው ከቡልጋ ሲሆን፣ ቡልጋ በመካከለኛው ዘመን በሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ ለክርስትና መስፋፋት በእጅጉ አስተዋጽዖ ያደረጉት መነኩሴው ወንጌላዊ አቡነ ተክለሃይማኖት የተወለዱበት ስፍራ በመሆኑ ሃይማኖታዊ ጉልህነት ነበረው። ስማቸው በ13ኛው ምእተ-ዓመት ከመሠረቱት የደብረ ሊባኖስ ገዳም ጋር የሚያያዝ በመሆኑ፣ ተክለሃይማኖት የሚለው መጠሪያ በኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ዘንድ የቤተኞች መጠሪያ ነው። አባቴ ወደ

ሐረር የመጡት ገና ልጅ ሳሉ ቀኛዝማች ጀማነህን ተከትለው ሲሆን፣ እርሳቸውም ራስ መኮንን ሐረርን ያስተዳድሩ በነበረ ጊዜ ትልቅ ሹመት የነበራቸው ታዋቂ የምኒሊክ ባለ ሥልጣን ነበሩ። የእርሳቸው አጎት እንደ ነበሩ አንድ ወቅት ላይ ነግረውኝ የነበሩት አባቴ ገና ልጅ ሳሉ የቤተ ክርስቲያን ትምህርታቸውን ይከታተሉ በነበረ ጊዜ ከቡልጋ እንዳመጧቸው ይነገራል። በዚህ ሁኔታ ወደ ሐረር የመጡት አባቴ ወደ ጉርሱም ከመዘዋወራቸው በፊት አንዳንድ የጽሕፈት ሥራዎችን እየሠሩ በዚያው በሐረር ለጥቂት ዓመታት ሰንብተዋል።

ሁልጊዜም የቅዱስ ተክለሃይማኖት ትውልድ ዘር እንደ ሆኑ በኩራት የሚነግሩኝ አባቴ ምንም እንኳን በኋላ ላይ ከቀኛዝማች ጀማነህ ሴት ልጅ እትዬ ተዋበች፣ እና ከልጇ ከኮሎኔል ጌታቸው ጋር ቢያስተዋውቁኝም፣ ከዚያ በፊት በነበረው የልጅነት ዘመኔ የእርሳቸውን የትኞቸውንም የቤተሰብ አባላት አውቄም ሆነ ተዋውቄ አላውቅም ነበር። በዚህም ምክንያት አክስቴ ወይም አጎቴ ብዬ የምጠራቸውን የአባቴ ወገኖችን ለማግኘት ሁልጊዜም ስመኝ ኖሬያለሁ። በእነዚህ ዘመናት ውስጥ ታላቅ ሰው ስለ ነበረው የተክለሃይማኖት ታሪክ በእጅጉ ከመማረኬ የተነሣ ኢትሳ ተክለሃይማኖት ወደምትባለው ትውልድ አገራቸው እንዲወስዱኝ አባቴን ደጋግሜ ጠይቄያቸዋለሁ። እርሳቸው ግን በየዓመቱ ባዶ ተስፋን በመስጠትና በማዘናጋት ዓመታት አለፉ።

በመጨረሻም፣ የ፱ኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ ድሬ ዳዋን እና አዲስ አበባን የሚያገናኘውን ባቡር በመሳፈር በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤታችን ተመራቂ ከሆነውና ለቤተሰባችን በርቀት ይዛመድ ከነበረው ከጋሹ አገዛ ጋር በራሴ ተነሣሽነት ጉዞውን አደረግሁ። የኢትዮጵያን ዋና ከተማ፣ አዲስ አበባን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ያን ጊዜ ሲሆን፣ በስፋቷ እና ውስብስብነቷ ሲበዛ ግራ ተጋባሁ። በዚያ የአክስቴን ልጅ እና አክስቶቼን ከተዋወቅሁ በኋላ፣ ጉዞዬን ወደ ኢትሳ፣ ቡልጋ አደረግሁ። ኢትሳ ውስጥ የአባቴ ዘመዶች ስርጓጉጥ እና ዓለታማ የሆነን መሬት በሚያርሱበት ግብርና ከባድ ኑሮን የሚገፉበት፣ በጣም ርቃ ያለች ተራ መንደር ስለ ነበረች፣ አካባቢው ከጠበቅኩት እጅግ በጣም ያነሰ ሆኖ እንዳገኘሁት ተሰምቶኝ ተስፋ ቆረጥኩ። አባ ተክለሃይማኖት የወንጌል አገልግሎታቸውን መሥርተውበታል የተባለውንም ገዳም አየሁት፣ ነገር ግን አልማረከኝም ነበር። ሁሉንም ነገር በምናቤ የሣልኩት አተልቄ በመሆኑ፣





በገጠራማው ክልል የነበረኝ ልምምድ የሚያስደስት አልነበረም። ነገር ግን በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር አርቲስት በመሆን ይሠሩ የነበሩትን አክስቴን እትዬ ቦጋለች እና የአጎቴ ልጅ ጋሼ አበበን መተዋወቁ ደስታን የሰጠኝ እና ያጽናናኝ አንድ ነገር ነበር።

የሥራ መስካቸውን ለበርካታ ጊዜያት ይቀያይሩ የነበሩት አባቴ የመጨረሻው የሥራ ምደባቸው ለገንዘብ ሚኒስቴር የወረዳ ግብር ሰብሳቢ ሆነው የሠሩበትና በአካባቢው አጠራር በጅሮንድ የሚባለውን ሥራ ነበር። እጥባቂ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን እንደ መሆናቸው፣ በሕይወታቸው አንድም ቀን ቤተ ክርስቲያን ከመሄድ ቀርተው የማያውቁ በአካባቢው የራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በእጅጉ የተከበሩ ደብተራ ነበሩ። እኔም በእያንዳንዱ እሑድ ማለዳ ከእርሳቸው ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ። እንደ ጥምቀት ባሉ ሃይማኖታዊ በዓላት ላይ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው የነበራቸው ሚና ጎላ ያለ የነበረ ሲሆን፣ በቁመታቸው ረጅም በመሆናቸው ትልቁን ከበሮ ተሸከመው እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ንጉሥ ዳዊት ያሸበሽቡ ነበር። በየዕለቱ ቁርስን፣ እንዲሁም እንደ ሥጋ እና የወተት ምርቶች ያሉባቸውን ምግቦች በጾም ወቅት እንዳንመገብ በሚከለከለው ዐብይ ጾም ወቅት ላይ ከእርሳቸው ጋር አብሬ እጾም ነበር። የአባቴን እና የቀሳውስቱን ምሳሌ በመከተል በዐብይ ጾም የመጨረሻዎቹ ሦስት ቀናት ላይ ለተከታታይ ሦስት ቀናት ለመጾም ሞክሬ ነገር ግን አቅም ከማጣቴ የተነሣ በመጨረሻው ቀን የወደቅኩበትን ጊዜ አስታውሳለሁ። ምንም እንኳን አባቴ አክራሪ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን የነበሩ ቢሆንም፣ የእናቴን ሃይማኖታዊ እምነቶችና ልምምዶች በግልጽ ተቃውመው አያውቁም። እርሷም ብትሆን የበረታች የቤተ ክርስቲያን ተሳላሚ እና እውነተኛ አማኝ ሆና ሳለ፣ ምናልባት በውዴታዋ አሊያም ከእርሷ በፊት ከነበረው ትውፊት የተረከበቻቸው በመሆኑ ምክንያት በርካታ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ታከናውን ነበር። በመደበኛነት ግንቦት ወር ላይ ከምታከናውናቸው ሃይማኖታዊ በዓላት አንዱ አቴቴ ወይም ጨሌ[7] ብለን እንጠራው የነበረውን በዓል ነበር። በዓሉ ሁሉንም የቤተሰቡን አባላት እና ዘመዶች እንዲሁም ጎረቤቶች አንድ ላይ ይሰበስባቸው ስለ ነበር በጊዜው የሚደረጉትን ቡና የማፍላት፣ ገንፎ ወይም ቂንጬ የመብላት እና በኦሮምኛ ቋንቋ የመዝፈንን በርካታ የበዓሉ ገጽታዎችን ግልጽ በሆነ መልኩ አስታውሳለሁ። ልጆች እንደ መሆናችን፣ ስለ ሃይማኖታዊ ፋይዳው

የምናውቀው በጣም ጥቂት ቢሆንም፣ ምግቡ እና ኅብረቱ ያስደስተን ነበር። የልምላሜ አማልክት የሆነችው አቴቴ የምትመለከበት መሆኑ እየታወቀ አባቴ በዝምታ ብቻ ሳይሆን፣ በመቀበልም ጭምር ያለተቃውሞ ያስተናግዱት እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል። የተለያዩ ዶሮዎችን በሚታወቅ ቀለም እና ግልጽ የጥራት ደረጃ *(ገብስማ፣ ወሰራ፣ ቆቅማ፣ ቀይ ዶሮ፣* ወዘተ. . .) አድርጋ እናቴ የምትሠዋባቸው ሌሎች ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችም መስከረም እና ጥር ወር ላይ ይካሄዳሉ። ዶሮዎቹ ስማቸው ጠቋር አባ ቡሌ፣ ወሰን ጋላ፣ አዳል ሞቲ፣ ሼክ አምበሶ፣ ወዘተ. . .የሚባሉ ስሞች ላሏቸው መናፍስት የሚሠዉ ነበሩ። እንዲህ ባለው አንደኛው የአምልኮ ወቅት፣ ድምጿን ለውጦ በእርሷ የሚናገረው መንፈስ በጣም በመናደድ የሚጠይቀውን የማይፈጽም ከሆነ ልጆቹን እንደሚገድል እየዛተ አባቴ አንዳች ነገር እንዲያሟሉ ይጠይቃቸው የነበረ ሲሆን፣ አባቴም በበኩላቸው "እሺ የተባለውን አደርጋለሁ" በማለት ብቻ በቀላሉ ይስማሙ ነበር።

ከዚህ በቀመጠል በጉርሱም የነበረው ትምህርቴ የተቋረጠበትን እና ወደ ሐረር ለመምጣቴ ምክንያት የሆነውን ታሪክ እተርካለሁ። በሶማሊያና ኢትዮጵያ መካከል በ1971 ዓ.ም ጦርነት ሲቀሰቀስ፣ የኦጋዴንን ክልል ብቻ ሳይሆን፣ የጂጂጋና ጉርሱም ወረዳዎችንም ጭምር የሚያሰጋ ነገር ሆነ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሳለን እንኖር እና እናድግ የነበረው በግጭቶች በተጎዳ አካባቢ በመሆኑ፣ ጦርነት እንደሚነሣ መገመቱ አስቸጋሪ አልነበረም። እኔ እና እንደ ሚሊዮን እንደሻው ያሉት ሌሎቹ እኩዮቼ በኢስቲንኮ ተራራ ላይ ተቀምጠን ኢላለሚ ተራራን ብሎም ከዚያም በስቲያ ያሉትን ክልሎች አተኩረን የተመለከትንባቸውን ጊዜያት አሁን ድረስ አስታውሳለሁ። በሩቅ ያሉትን ደመናዎች እናይና ጭጋጉን በተመለከትን ቍጥር ጦርነት እየቀረበ እንደ ነበረ ተናግረን እናውቃለን። ወደዚያ ድምዳሜ እንዴት እንደ መጣን አሁን ድረስ አላውቅም፣ ነገር ግን በሰማይ ላይ የዳመናትን አቀማመጥ በመመልከት ያንን የመሰሉ የየዋህነት ትንበያዎችን ማድረግ በዚያን ጊዜ በጣም የተለመደ ነገር ነበር። በኢትዮ-ሶማሊያ ድንበር ላይ የነበረው ጦርነት በአብዛኛው በሶማሊያውያን ነዋሪዎች ተይዘው ወደ ነበሩት ወደ ጉርሱም እና ዙሪያ-ገብ አካባቢዎቹ ተዛመተ። ከተማዋ በወቅቱ ሽፍታ ብለን በምንጠራቸው ሶማሌዎች የተከበበችበትን ሌሊት አስታውሳለሁ። እኔ በሚሊዮን እንደሻው ቤት ውስጥ





ባለችው የጥናት ቤት ውስጥ ነበርኩ። ሌሊቱ ሊጋመስ አካባቢ ቀስ በቀስ እየጨመረ የሚሄድ እና በጉልህ መሰማቱን የቀጠለ ሁካታ መስማት ጀመርን። በዚህን ጊዜ ከተማይቱ በሶማሌዎች እንደ ተከበበችና የምንሰማውም ሁከት እየገፉ በመምጣት ላይ ባሉት ሶማሌዎች እና ያንን ሁኔታ በሚከላከሉት ጦር ሰራዊት እንዲሁም በነፍጠኞች መካከል የሚደረገውን የተኩስ ልውውጥ እንደ ሆነ በዙሪያችን የነበሩት ሽማግሌዎች አስታወቁን።

ከልጅነቴ ጀምሮ የምታወቀው በትንሽ በትልቁ የሚፈራ ልጅ እንደ ሆንኩ ስለ ነበረ፣ ሊጎዳን ከሚችለው ነገር ራሳችንን የምንጠብቅበት መጠለያ ስፈልግ ከጣራ ላይ የሚፈስስ የዝናብ ውኃን ለመያዝ ከቤት ውጪ የቆመ በርሜል አገኘሁ። የበርሜሉን ግማሽ ያክል መጠን ውኃ እንደ ሞላው ባለማወቅ ዘልዬ ወደ ውስጡ ስገባ ከተቀየጠው አስቂኝ እና አስፈሪ ስሜቶቼ የተነሣ በድንገት ጮህኩኝ። ሊነጋጋ ሲል የተኩሱ ድምፅ እየቀነሰ ቢሄድም፣ ጀት አውሮፕላኖች በሰማይ ላይ ሲበርሩ አይተን ስለ ነበር መጀመሪያ ላይ የሶማሊያ አውሮፕላኖች መስለውን እንደምንሞት ፈርተን ነበር። ነገር ግን ቆየት ብሎ አንዳንድ የመታደግ ዘመቻን እንዲፈጽሙ ከኢትዮጵያ አየር ኃይል የተላኩ እንደ ሆኑ አወቅን። ሁሉም ነገር ጸጥ ማለቱን ስናውቅ፣ ምን ተከናውኖ እንደ ነበር ለማየት በጥንቃቄ ፈራ-ተባ እያልን እየዳኸን ወደ ከተማ ሄድን። ሰንደቃ ተብሎ በመጠራት የሚታወቀው በአብዛኛው በሶማሌዎች ወደ ተያዘችው አነስተኛ የገበያ የሱቅ ሠፈር ወዳሉባት አጎራባች ስፍራ ሄድን። የአካባቢው ሶማሌዎች ከተማይቱን ጥለው በመውጣታቸው እስኪገርመን ድረስ ሱቆቻቸውና መኖሪያ ቤቶቻቸው እየተዘረፉ ነበር። ሽሽታቸው ሆነ ብለው ያደረጉት ይሁን ወይም ቀደም ብለው ያሰቡበት ይሁን፣ አሊያም ከመልሶ ማጥቃት ፍርሃት የተነሣ ይሁን በትክክል እርግጠኛ አይደለሁም። በዝርፊያው ተግባር ውስጥ እኔና ሌሎች ሕጻናት ስንሳተፍ፣ ከሶማሌዎቹ ሠፈር ማር የያዘ ሣጥን አገኘሁ። እኔም ሆንኩ ሌሎች እያደረግነው በነበረው ነገር ጨርሶ ደስተኛ አልነበርኩም። በእርግጥ፣ ያላግባብ የወሰድኩትን ማር ስላልወደድኩት ከመብላት ይልቅ ሽጬው ወይም ወዲያ ጥዬው ሊሆን እንደሚችል አገምታለሁ።

ጦርነቱ በሶማሌዎች መሸነፍ ያበቃ ቢሆንም እንኳ፣ ከተማይቱ ከዚያ በኋላ እንደ ቀድሞዋ መሆን አልቻለችም። "ሽፍታ" በሚለው የዘልማድ መጠሪያቸው የሚታወቁት ሶማሌዎች የተለመደውን የጦርነት ዓይነት ቢሸነፉም፣ በደፈጣ

ውጊያ በማንሰራራታቸው፣ ገጠራማው ክልል የጦርነት ቀጠና መሆኑ ቀጠለ። ጉርሱም የአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ጦር መቀመጫ ስለ ነበረች፣ አብዛኞቹ የ18ኛው ክፍለ ጦር አባላት ወደ ጦር ግንባር ተወስደው ነበር። የመጋላ ነዋሪዎች 'ካምቦ' ወይም "ወረሽዋ ካምፕ" ብለው በሚጠሩት አካባቢ በሁሉም የጉርሱም ወረዳዎች መስፋፋታቸውን ቀጥለው የነበሩትን ዐማፂያን እንዲደመስሱ የተላኩ በርካታ ወታደሮች ሰፍረዋል። ወታደሮቹ መቀጣጫ ከሆነው ወታደራዊ ዘመቻ ሲመለሱ በምርኮ የወረሷቸውን ከብቶች አንዳንዶቹም የታረዱትን ይዘው ይመጡና ሥጋዎቹንም ለሕዝቡ በነጻ ያድሉ ነበር። ለቤተሰባችን ጥቂት ሥጋ ልቀበል ወደ እነዛ ቦታዎች በመሄድ አሜሪካውያን እያሹ የሚልኩትን የጣሳ ሥጋ በካምቦ ከሠፈሩት ወታደሮች በርካሽ እየገዛሁ በገበያ ስፍራ እሸጥ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ከፍተኛ የሆነ ትርፍ ስለማገኝበት እነዚያን የቆርቆሮ ሥጋዎች በመሸጥ ከማገኘው ገቢ ጥቂት ልብሶችን እንኳን ገዝቼያለሁ።

ጥሩ ለላደረግሁም ከምልባቸው የሕይወቴ አጋጣሚዎች አንደኛው በከረምት እረፍት ወቅት የአጎቴ ልጅ ወደሚኖርበት እና የሐረርጌ ዋና ከተማ ወደ ነበረችው ሐረር ዘመዶቼን ለመጠየቅ እሄድ ዘንድ የቆረጥኩበት ሲሆን፣ አጋጣሚውም የወደፊት ሁኔታዬን የሚወስን ጉዞ ሆነ። ከተማዋ ከጉርሱም 70 ኪሎ ሜትር ብቻ የምትርቅ ብትሆንም፣ ከእናታችን ወገን የሆኑትን ዘመዶቼን ለማየት ዕድሉን አግኝቼ አላውቅም ነበር። አባቴ ወደ ሐረር እንድሄድ ፈቃደኛ ያልነበሩ ቢሆንም፣ በመጨረሻ አሳመንኳቸውና አነስተኛ የልብስ እጥበት ንግድ ሥራ ከነበራቸው ጎረቤታችን ከጋሽ መኩሪያ ጋር እንድሄድ ፈቀዱልኝ። ጋሽ ዶቢ በሚለው ቅጽል ስማቸው ይበልጥ ይታወቁ የነበሩት ጋሽ መኩሪያ እኔን ወደ ሐረር የመውሰዱን ኃላፊነት ተረከቡ። መሐሪ ካሳ በሚባል የታወቀ ሰው በምትሾፈረው ኩሪየራ አውቶቡስ ከእርሳቸው ጋር ተቀመጥኩ። ምንም እንኳ ታዋቂ ያደረገውን ነገር በተመለከተ ምንም ፍንጭ ባይኖረኝም፣ ስለዚህ ሹፌር ድፍረት የሞላበት ጀብደኝነት ብዙ እሰማ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ ማምሻውን 11:00 ሰዓት አካባቢ አውቶቡሱ ከሩቁ ሲመጣ ባየን ቍጥር "መሐሪ ካሳ ለነፍሱ አይሳሳ" እያልን ሰላምታ እንሰጠው ነበር።

የምንጓዝበት አውቶቡስ በጉርሱም እና ባቢሌ መካከል ባለችው ዳካታ ተብላ በምትጠራው አካባቢ ስትደርስ የተኩስ ድምፅ ሰማን። መጀመሪያ ላይ





የባረቀ መሣሪያ ወይም ያኔ ጠማሻ የምንለው እንደዚያ ያለ ነገር መሰሎኝ ነበር። በመቀጠልም ሰዎች ሲጮኹ ሰማሁ። ከዚያ በኋላ ያወቅኩት ነገር ከጎኔ ተቀምጠው የነበሩት ጋሽ መኩሪያ እንደ ተገደሉ ነበር። "ጋሽ መኩሪያ" በማለት ደጋግሜ ብጮህም መልስ አልሰጡኝም። ከዚያም ጭንቅላታቸው ከፊት ለፊታቸው ባለው መቀመጫ ላይ ዘንፈል ብሎ፣ አፋቸውም በሰፊው ተከፍቶና ምላሳቸውም አፈንግጦ ወጥቶ ደም ሲፈስው አየሁ። ሞት ምን እንደ ሆነ አይቼ የማላውቅ ትንሽ ልጅ በመሆኔ አንዳች አስጨናቂ ነገር በጋሽ መኩሪያ ላይ እንደ ደረሰባቸው አወቅሁ። ጥይት የገባበት የሚታይ ቀዳዳ እያለም ቢሆን ሞተዋል ብሎ ለመረዳት ለእኔ ከባድ ነበር። አስጨናቂውን እይታ በመመልከት እና ሊመጣ ያለውን አደጋ በማሰብ ጮህኩኝና በአውቶቡሱ መቀመጫ ሥር ተደብቄ በጊዜው አውቀው በነበረው ምርጥ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ጀመርኩኝ። ጎራ በሚባል ቦታ የክርስቲያኖች እና የሙስሊሞች የጸሎት ቤት ላቋቋመውና የሚሰብ ስብዕና ለነበረው የጎራው በረኛ ወይም ሼክ መንግሥቱ ተሳልኩኝ። ልጆች ሳለን የምራችንን ለሆነ ለምናደርገው ወይም ለማናደርገው ነገር በስሙ የምንምልለት ከኃይለ ሥላሴ ቀጥሎ ሼክ መንግሥቱ ነበሩ። እርሳቸው ይገኙበት ወደ ነበረው ስፍራ እናቴ ወስዳኝ ታውቃለች። በስለቴ ውስጥ ለሼኩ እንዲህ አልኩኝ፣ "ዛሬ ካዳንከኝ፣ አንድ ጠርሙስ አረቄ አመጣልሃለሁ።" ያለችኝን ትንሽ መንፈሳዊ እውቀት ተመርኩዤ ወደ እግዚአብሔር የቀረብኩበት ጊዜ ያቺ ዕለት ናት። አልፎ አልፎ የሚተኮስ መትረየስ ቢኖርም፣ ወደ አቅራቢያዋ ባቢሌ እስክንደርስ ድረስ የአውቶቡሱ መስኮቶቹ እንደ ተዘጉ ጉዟችንን ቀጠልን። ተዓምራት ብዬ የጠራሁት የዚያ ቀን አስገራሚ ነገር ልክ ወደ ከተማዋ ስንገባ ሞተሩ መጥፋቱ ነበር። መኪናው ሲቆም፣ በምሥጢር ከተደበቅሁበት ቦታ መውጣት ባለመፈለግ ከመኪናው መቀመጫ ሥር እንደ ሆንኩ ማልቀሴን ቀጠልኩ። በመጨረሻም፣ እድሜያቸው በገፉ የተወሰኑ ሰዎች ተጎትቼ እንድወጣ ከተደረገ በኋላ፣ አጥብቀው በመያዝ አጽናኑኝ። ባጋጠመኝ አሰቃቂ ሁኔታ እና ግራ መጋባት ውስጥ ቀጣዩ እርምጃዬ ወደ ጉርሱም መመለስ ይሆን አሊያም እንደ ተመኘሁት ሐረር መሄድ እንደ ሆነ እርግጠኛ አልነበርኩም። የትኛውን እንደ መረጥኩ በእውነት ባላስታውስም፣ ያ ሕልም የመሰለ ክስተት ግን የትውልድ ስፍራዬ እና የሊጋ ልጅነት ጊዜዬን ባሳለፍኩበት በጉርሱም እንዳልቆይ ለመወሰኔ ሰበብ ሆነ።

ወደ ጉርሱም ከተመለስኩ በኋላ እናቴ አቅፋ ልቅሶ በተሞላበት ደስታ የተቀበለችኝ ትርዒት አይረሳኝም። በርካታ ሰዎች "እንኳን እግዚአብሔር አተረፈህ" ሊሉኝ መጡ። ያ አሳዛኝ አጋጣሚ ከፈጠረው ቁስል በቀላሉ አላገገምኩም። ቆየት ብሎ ከእናቴ ጋር ወደዚያ የታወቀ የጸሎት ቤት በእግር በመሄድ ድንግል ማርያም በምትነግሥበት የሐምሌ 16 ቀን የተሳልኩትን ፈጽሜ ለሼክ መንግሥቱ አንድ ጠርሙስ አረቄ አስረከብኩ። ዕለቱን በየዓመቱ ለማስታወስ እናቴ የተለየ ስለት ከመግባት ባለፈ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይህንኑ ቃሏን ጠብቃ ፈጽማዋለች። የ1956 ዓ.ም ጦርነት ጦሱ ከፉኛና አስደንባሪ ስለ ነበረ፣ የተወለድኩበትን ከተማ ጉርሱምን ትቼ ወደ ሐረር መጣሁ።





# በሐረር የነበረኝ የትምህርት ቆይታ

## በመስጠትና የገንዘብ ድጎማም በማድረግ የሐረርን ኑሮ ተያያዝኩት

የክርስትና አባቴ፣ ጋሽ ንጋቱ፣ ረድተውኝ ወደ ሐረር ከተዛወርኩ በኋላ፣ በራስ መኮንን መለስተኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ለመማር ተመዘገብኩ። በጉርሱም ካጋጠመኝ ነገር የተነሣ ሐረር እንደ ገባሁ ሰሞን አብራኝ ወደዚያው ሄዳ ከነበረችው ከእናቴ ጋር እዚያ ቆየሁ። ከተማዋ ተከብባ በነበረ ጊዜ እናቴ ከጉርሱም እስከ ሐረር ድረስ የነበረውን ረጅም መንገድ ከእኅቴ እና ወንድሜ ጋር በእግሯ ስትወጣው፣ በወቅቱ ከነበረው አደጋ የተነሣ ያንን ጉዞ በድንገት የሚያደርጉ ሌሎች በርካታ ቤተሰቦችም ጭምር አብረዋቸው ይሰደዱ ነበር። እናቴ በ1940ዎቹ ውስጥ ሶማሌዎች ወደ ጉርሱም ገብተው ሠፈራዎቹን በእሳት ሲያቃጥሉና ሰላማዊ ዜጎች ሲሞቱ ልክ እንደዚሁ ተሰድዳለች። በጥልቅ ትውስታቸው ውስጥ ሶማሌዎቹ በፈጸሙት ጥቃት ከተማይቱ ስትወድም እና ስትቃጠል የነበረውን ሁኔታ የግሪ ቃጠሎ[8] በማለት በሩቁ ያስታውሱታል፤ ያው ዓይነት ሁኔታ እንዳይደገምም ይፈራሉ።

በዘመኑ የአካባቢው ነጋዴ የነበረው የእናቴ ታናሽ ወንድም፣ አበበ ዋቅቶላ፣ የሚኖሩበትን ቤት መስጠትና የገንዘብ ድጎማም በማድረግ እገዛ እያደረገላቸው እናቴ እና ከእርሷ ጋር የቀሩት ልጆች ሐረር ውስጥ ተቀምጠው የሐረርን ኑሮ ተያያዝኩት። በዚያ፣ እናቴ እንጀራ በመሸጥ ኑሮዋን ትገፋ ስለ ነበር፣ የጋገረቻቸውን እንጀራ እና ዳቦዎች ሸዋ በር ተብሎ በሚጠራው የገበያ ስፍራ በመሸጥ በትንሿ የንግድ ሥራዋ ላይ ተሳትፌያለሁ። ይሄ ደግሞ በጣም በጠዋት ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዴ በፊት ገበያ ሄዶ መቀመጥን፣ እንዲሁም ደግሞ ከትምህርት ቤት መልስም እንዲሁ ማድረግን የሚጠይቅ ሥራ ነበር። በጣም አሰልቺ የነበረ ልምምድ ቢሆንም፣ ሌላ ምርጫ ባለመኖሩ ተቀበልኩት። በገበያው ስፍራ ላይ ሰለሞን ጢቂሹ የሚባለውን ትንሽ ልጅ ተዋወቅኩትና ባለን

የጋራ ተሞክሮዎች እንዲሁም የሚያግባቡን ነገሮች ላይ ተመሥርቶ ከእርሱ ጋር ዘላቂ የሆነ ጓደኝነትን አጸናሁ።

በአንዳች ምክንያት፣ እናቴ በጣም የምትወደውና የምታደላለት ታናሹ ወንድሜ ገበያ ሄዶ እንጀራ መሸጥ አይወድም። ወላጆችን በሥራ በመርዳታችን እኛ የምናገኛቸውን 'ተባረክ' ወይም "ትምህርትህን ይግለጥልህ" የሚሉ ምርቃቶችን እንዲያገኝ በመፈለግ በእርሱ ላይ ብዙ ጫና አታደርግበትም። በመጠኑ ቁጥብ ከነበርኩት ከእኔ በተለየ እርሱ በመጠኑ ዐመፀኛ መሆን ይቀናው ነበር። ልፈጽማቸው ከሚያስደስቱኝ ነገሮች መካከል አንደኛው ለጎረቤቶቼ መላላክ ሲሆን፣ ከዚያም የተነሣ "እንዴት ያለ የተባረከ ልጅ ነው" እየተባልኩ ጥሩ ስም እና ዝና ላገኝ ቻልኩ።

እናቴ ጉርሱም ሳለች ነጋዴዎች ከአምራች ገበሬዎች ቡና በቀጥታ በሚገዟቸው ጊዜ ይንጠባጠቡ የነበሩትን የቡና ፍሬዎች በመልቀም፣ አጥቤ ለአንዳንድ የሱቅ ባለቤቶች እሸጥና ከተፋታች በኋላ ምንም ገቢ ላልነበራት እናቴ ጠቅላላውን ገንዘብ እሰጣት እንደ ነበረ አስታውሳለሁ።

የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል ተማሪ የነበርኩባቸው የትምህርት ቆይታዎቼ ሲበዛ ዘግናኝ፣ የሚያደክሙና አሰልቺ የሥራ ድግግሞሽ የሞላባቸው ነበሩ። ለመሠረታዊ ፍላጎቶቼ ይሄ ነው የሚባል አንዳችም እገዛ ያላደረገልኝ አባቴ ክረምት ላይ እረፍት ስሆን ልጠይቀው በሄድኩ ቍጥር ሞቅ ያለ አቀባበል ያደርግልኛል፤ እንዲሁም ልለየው ጊዜው ሲደርስ ጥቂት ጥሬ ገንዘብ ይሰጠኛል። እህል ነጋዴው የእናቴ ታናሽ ወንድም በሞላለት ጊዜ አልፎ አልፎ በገንዘብ እና በዓይነት አንዳንድ እገዛዎችን ለእናቴ ሲያደርግላት ይቆይና ያንን ባላደረገ ጊዜ ደግሞ እንጀራ እና ሌሎችንም ነገሮች በመሸጥ ጉድለቱን ሸፍና ታሳድገናለች። እኅቴ መሠረት የጤፍ እና ማሽላ ዘር ከሚሰጣት ከአጎቴ ተቀብላ በሸዋ በር ገበያ በመሸጥ ለእናቴ ከፍተኛ ድጎማ ታደርግ ነበር።

እንዳለመታደል ሆኖ፣ እኅቴ በአጎራባቻችን ይኖር ከነበረ አንድ ፖሊስ ጋር በፍቅር መኮብለሏ ሲደረስበት በጣም ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ አጋጠመን። ማንም ሰው ይሄ ይሆናል ብሎ ስላልጠበቀ፣ ዜናው በደረሰ ጊዜ በጣም አስደንጋጭ ሆነብን። ለተወሰነ ጊዜ ከእኛ አካባቢ ተሰወረችና ኋላ ላይ ከሐረር ብዙም በማትርቀው የንግድ ከተማ ድሬዳዋ ውስጥ ለጨዋ ቤተሰብ አሳፋሪ





የሆነውን የቡና ቤት አሻሻጭነት እየሠራች እንደምትኖር ሰማን። በተወሰነ ጊዜ አንድ ጊዜ ጫማዎችን እና ልብሶችን ይዛልን እየመጣች የምትጠይቀን ቢሆንም፣ አብዛኛውን ጊዜ እነዚህን ለመግዛት ገንዘብ ከየት እና እንዴት እንደምታመጣ፣ ሆኖም ግን ባለችበት ሁኔታ ውስጥ ደስተኛ ሳትሆን የቀረችው ለምን እንደ ሆነ ለራሴ እጠይቅ ነበር።

ሌላኛው ተስፋ አስቆራጭ ነገር በወንድሜ ላይ የደረሰበት ነገር ነበር። የሣንባ ነቀርሳ የነበረባቸው ጠያቂዎቻችን በመጡ ጊዜ ተጠግቷቸው ይሁን፣ አሊያም በሽታው ያላቸው ሰዎች ካስተረፉት ምግብ በመመገቡ ምክንያት እንደ ሆነ ባይታወቅም፣ የበሽታው ተለካፊ ሆነ። እናቴ ከእኛ ጋር ትኖርበት የነበረውን ቤት በባለቤትነት የያዘው አጎቴ እንግዶችን እንድናስተናግድበት ይፈልግ ነበርና እርሱ ያለውን ከማድረግ ውጪ ምንም ምርጫ አልነበረንም። አጎቴ ሲበዛ ደግ ሰው የነበረ ቢሆንም፣ በድንገት እንግዶችን በላያችን ላይ ሲያመጣብን ግን ምቾት አይሰማኝም ነበር። በአንደኛው ሌሊት ላይ አጎቴ ከጉርሱም የመጣ በሣንባ ነቀርሳ በሽታ የሚሠቃይ እንግዳን አመጣ። እንግዳው ደጋግሞ እንደሚያስል በማስተዋል ያንን ሰው ብርቀውም፣ ታናሹ ወንድሜ ግን ግዴለሽና የማይፈራ ስለ ነበረ ሳይርቀው ቀረ። ይህም ብቻ ሳይሆን፣ የሣንባ ነቀርሳ በሽተኞች ከሚታከሙበት ሆስፒታል የተራረፉ ምግቦችን ይዞ መምጣት ሲጀምር፣ ይህንን በማድረጉ እናቴ ፈጽሞ ልትገሥጸው አልሞከረችም። ካመጣቸው ምግቦች ጥቂቶቹን ብቀምስም፣ ቢርበኝ እንኳን ያን ያክል ለምግቡ እንዳልሳብ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ አደርግ ነበር።

ቆየት ብሎ ወንድሜ ሣንባ ነቀርሳ እንደ ተጋባበት ስለ ታወቀ፣ ረጅም ጊዜ ለወሰደ ሕክምና በሆስፒታል ተኝቶ ሰነበተ። በሕይወት እንዲኖር እፈልግ ነበርና መድኃኒቶቹን በመደበኛነት እንዲወስድ በብርቱ ብመክረውም፣ ልብ ብሎ ሊሰማኝ አልቻለም፤ መድኃኒትን በመደበኛነት ያለመውሰድን ውጤት የማታውቀው እናታችንም ብትሆን ልትቆጣጠረው አልቻለችም ነበር። ከዚህ በታች በምዘረዝረው ታሪክ እንደ ተቀመጠው፣ በመጨረሻ ላይ በሽታው የወንድሜን ሞት አስከተለ።

## ትምህርትና የልጅነት ሕይወት

በዚያን ዘመን እጅግ በጣም ወደተከበረው የመድኃኒዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የገባሁት የ8ኛ ክፍል ትምህርቴን እንዳጠናቀቅሁ ሲሆን፣ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በገባሁበት የመጀመሪያው ቀን የተሰማኝን ደስታ አስታውሰዋለሁ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ መሆን ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ነገር ከመሆኑ የተነሣ፣ ጉርሱም በነበርኩ ጊዜ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይማሩ የነበሩ የአጎት እና አክስት ልጆች እንዳሉን ለጓደኞቼ ስናገር ኩራት ይሰማኝ ነበር። ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሌለባቸው እንደ ጅጅጋ፣ ኮምቦልቻ እና ግራዋ ዓይነት የሐረርጌ ከተሞች የመጡ 35 የተለያዩ ተማሪዎች ባሉበት የ9ኛ ቢ ክፍል ውስጥ ተመደብኩ። ገና ትንሽ ልጅ ሆኜም የትምህርትን ፋይዳ በእጅጉ የማደንቅ ተማሪ በመሆን በትምህርት ደረጃዬ ከአንዱ እርከን ወደ ሌላኛው መሸጋገሬን አስብ ነበር እንጂ፣ በዚያኛው የሕይወቴ እርከን ላይ ምን ማድረግ እንደ ነበረብኝ ገና እርግጠኛ አልነበርኩም። በእነዚህ ጊዜያት በየትኛውም አንድ የተለየ የትምህርት ዓይነት ላይ ፍቅር እንዲያድርብኝ ያደረገ ሁኔታ አልነበረም። የኢትዮጵያውያን ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች አገልግሎት (ኢዩተአ) ከሚባለው ተቋም የመጡት የታሪክ እና የመልክዐ-ምድር አስተማሪዎቼ ምናልባት አንዳች ዓይነት መልካም አሻራ ሳይተዉብኝ አልቀሩም ብዬ እስካምን ድረስ፣ የታሪክ ትምህርትን ያስተማሩኝ ጋሽ ሥዩም አንዳች ዓይነት እኔን የመማረክ ኃይል ነበራቸው። እርሳቸው፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የዝግመተ-ለውጥን ንድፈ ሐሳብ ለተማሪዎች ሲያስተዋውቁ ደስታም ድንጋጤም ተሰምቶኝ ነበር። በልቤ እና በአእምሮዬ ይመላለስ የነበረው የሁሉም ጥያቄዎቼ እናት ገና ከመነሻውም ቢሆን ሰው የተገኘው ከዝንጀሮዎችና ጦጣዎች ነው ብሎ አንድ አበሻ እንዴት በድፍረት ሊያስተምር ይችላል የሚለው የነበረ ሲሆን፣ ከዚህ ቀደም እንዲህ ያለ ነገር ሰምቼም ስለማላውቅ ንድፈ-ሐሳቡ ለእኔ በጣም እንግዳ፣ ያልተለመደና አቋሙን ያልለየ ሆነብኝ።

በዚህኛው የሕይወቴ ክፍል ላይ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ የመሆኔን ኩራት እንዲሁም በሸዋ በር ገበያ ውስጥ ሰው ሁሉ የሚመለከተው እንጀራ ሻጭ የመሆኔን እፍረትም እኩል ለኩል አስተናግጃለሁ። ጊዜው መቼ እንደ ነበረ ይጥፋኝ እንጂ፣ የክርስትና አባቴ ከሆኑት ከጋሽ ንጋቱ ጋር ለመኖር በሄድኩ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆኖ እንጀራ ከመሸጥ እፍረት ጊዜያዊ የሆነ እፎይታን አግኝቼ ነበር። ከጋሽ ንጋቱ ጋር በከረምሁበት ጊዜ እናቴ ቤት ከነበረው ምግብ





እጅግ በጣም ይሻል የነበረውን ምግብ እየበላሁ ቆይቼ አሁን ድረስ ግልጽ ብሎ በማይገባኝ አንዳች ምክንያት ወደ እናቴ ቤት ተመልሼ ገባሁ። የአጭር ጊዜ ቆይታ ይሁን እንጂ፣ እንደ ክርስትና አባቴ ሁሉ ከአጎቴ አበበ ዋቅቶላ ጋር ለመኖር እቤቱ የሄድኩበትንም ጊዜ አስታውሳለሁ። የበለጠ እያደግሁ ስሄድ በነበረኝ የሕይወቴ ክፍል ውስጥ ጠቃሚ ሚናን የተጫወተው አጎቴ ደግ ሰው የነበረ ቢሆንም፣ ልጅ በነበርኩበት በዚያን ጊዜ ግን በእኔ አልተማመነብኝም፣ ወይም ቢያንስ ለዚያች የሕይወት እርከን የመማሬን ዋጋ አላከበረውም ነበር። አንድ ጊዜ ለ9ኛ ክፍል ትምህርቴ የሚሆን መማሪያ መጽሐፍ እንዲገዛልኝ ጠይቄው፣ "በጋላ ልጅ ላይ ገንዘብን ማውጣት ተገቢ አይደለም"[9] በሚለው ምላሹ በጣም አንቋሸሸኝ። ምናልባት ከልቡ የተናገረው ነገር ላይሆን ይችላል፣ አሊያም በአልኮል መጠጥ ኃይል ውስጥ ሆኖ የተናገረው ነገር ሊሆን ይችላል በማለት ራሴን እያጽናናሁ ያንን ዘለፋ ውጬ ልመናዬን ከመቀጠል ውጪ ምንም ምርጫ አልነበረኝም። እንደ ታዳጊ ልጅ ግን እንደዚያ ያሉ ቃላትን ከሚያከብሩት ሰው መስማት የሚጎዳ ነገር ነበር።

ከአዲሱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሕይወት አዳዲስ ጓደኞችን ማፍራትና ጉርሱም ሳለሁ እንደማደርገው ወደ ጥናት ቤት የመሄድ ልምምዴን በመቀጠል፣ ከበርካታዎቹ ጋር እንዲሁ ለማድረግ መሞከር ጀመርኩ። አንዳንዶቹ የጥናት ቤቶች የጎረቤት ያክል የቀረቡ፣ ሌሎቹ ደግሞ ራቅ ብለው የሚገኙ ሲሆኑ፣ የማዘወትራቸው ሁለቱ ቤቶች የሰለሞን ጢቂሹ እና ከጉርሱም የመጣው ጓደኛዬ የግርማ ቃና ቤት ነበሩ። ከሰሎሞን ጋር የነበረኝ የጥናት ግንኙነት በመላው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤታችን ቆይታ ውስጥ ለዓመታት ዘልቆ ሁለታችንም በርካታ የሚያወላዱ ሁኔታዎች ቢገጥሙንም፣ ኋላ ላይ ወደ ዩኒቨርስቲ መግባት ቻልን።

ከሳይንስ ትምህርት በላይ በአርት (የማኅበረሰብ ጥናት) ላይ የተሻለ የሠራሁ በሚመስለኝ መልኩ የ9ኛ ክፍልን አጠናቅቄ ወደ ቀጣዩ እርከን ስዘዋወር 10ኛ ዲ ክፍል ውስጥ ተመደብኩ። በዚያ፣ እንደ ማሞ አስፋው፣ ፎዚያ አቡብካሪ፣ ዓለሙ ዘገየ እና የመሳሰሉት ዓይነት ብሩህ ጭንቅላት የነበራቸው ተማሪዎች ነበሩበት። በጥሩ ሁኔታ አጠናቅቄ ተገኘሁ እንጂ፣ በዚያ ነጥብ ላይ ስለ ወደ ፊት ዕቅዴ ምንም ፍንጭ አልነበረኝም። የጋራሙለታ ወረዳን የሚያስተዳድሩት ሰው ልጅ እንደ ነበረው እንደ ቴዎድሮስ ታምራት ካሉ ልጆች ጋር የመሠረትኩት ጓደኝነት ትልቅ በረከት እና መነሣሣትን ያገኘሁበት ነበር።

እርሱ በጣም ያነብብ ስለ ነበረ ያ ሁኔታ የእርሱ የቅርብ ጓደኞች በነበርነው ላይ የሚተላለፍ ተጽዕኖ አሳድሮብን ወደ ቤተ መጻሕፍት እየሄድኩ መጻሕፍትን መዋስ ጀመርኩ። አንድ ወይም ሁለት መጻሕፍትን በሣምንት ጊዜ ውስጥ ጨርሰን እንነጋገርባቸው በነበረበት ሁኔታ ንባብ የትርፍ ጊዜ መደሰቻችን በሆነልን አዲስ ጓደኛማቾች ዙሪያ የፉከከሩ ወላፈን ከፍተኛ ቢሆንም፣ ማናችንም ብንሆን ቴዲን መብለጥ ሳንችል ቀረን። እናነብባቸው የነበሩ መጻሕፍት *‹‹አራውንድ ዘ ወርልድ ኢን ኤይቲ ዴይስ››*፣ *‹‹ዘ ሰርቲ ናይን ስቴፕስ››* እና *‹‹ምንቴዙማስ ዶውተር››* የተሰኙትን ነበር። ከማዘጋጃ ቤቱ አቅራቢያ በሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ከተከፈተ በኋላ፣ ሰለሞን እና እኔ ቀበኛ አንባቢዎች ሆንን። በዚህ ጊዜ እንደ *‹‹ሬድ ባጅ ኦቭ ከሬጅ››* ያሉትን ጨምሮ ሌሎችም በርካታ ስለ አሜሪካ ሕይወት እና ታሪክ የሚያወሩ በአሜሪካውያን ደራሲያን የተጻፉና የበለጠ ኮስታራ የሆኑ መጻሕፍትን በንባባችን ውስጥ አካተትን። ቤተ መጽሐፉ እንደ ፒንግ ፖንግ ያሉ መጠነኛ የመዝናኛ መገልገያዎች የነበሩት በመሆኑ፣ ሰሎሞን እና እኔ ከንባብ በኋላ የጠረጴዛ ቴኒስ በመጫወት ጊዜያችንን እናሳልፋለን። ስለ ዓለም ጥሩ የሆነ መረጃና አስደናቂ እውቀት የነበራቸው ጥበቃ ሠራተኛው አባባ ምሕረቴ እኛን በደግነት የሚያስተናግዱ ግሩም ሰው ነበሩ።

በአሥረኛ ክፍል ትምህርቴ ውስጥ ጥቂት የሚሰቡ ልምምዶች የነበሩኝ ሲሆን፣ በትምህርቴ ጥሩ ሠርቼ ሦስተኛ በመውጣት አጠናቀቅሁ። ዘና ባለ ሁኔታ የማስተማር ዘይቤያቸው ትኩረቴን የሳቡት፣ የሰዋሰው ደንቦችን እና ሕግጋትን ያን ያክል የማያጠብቁት እና በንባብ እንዲሁም ውይይቶች እንድንሳተፍ ያደርጉን የነበሩት የአማርኛ መምህራችን ጋሽ ታደሰ ገብረሐና በጣም ፈጠራ ያለበት ስብዕና ስለ ነበራቸው በአንዳንድ መንገዶች የተለዩ ሰው ሆኑብኝ። በዚያን ዘመን የነበረችኝ ብቸኛ ጫማዬ በወቅቱ የማደርጋት ነጠላ ጫማ ሆና ሳለ፣ በዘፈቀደ የምኖር ወይም ከባህሉ በተጻራሪ ጫማዎችን እንዲሁ አጥልቄ ወደ ትምህርት የምገባ ልጅ አድርገው ሳያስቡኝ አይቀርም ብዬ እስከገምት ድረስ ከዕለታት በአንደኛው ቀን በዛችው የተለመደች ጫማ ሆኜ ወደ ክፍል ስገባ በእርሳቸው ክፍለ-ጊዜ ትምህርቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ጫማዬን እንዳወልቅ አዘዙኝ። ምናለ ያለሁበትን ሁኔታ ባወቁ ብዬ ብመኝም፣ ያሉኝን





አክብሬ በመፈጸም ከዚያች ትንሽ ድንጋጤ ጋር ትምህርታቸውን በደስታ አጣጣምኩት። እርሳቸውም ጥሩ መጣጥፎችን እንድጽፍ ያነሣሡኝ የነበረ ሲሆን፣ አንድ ወቅት ላይ ሰዎች በረሃብ እየሞቱ ጨረቃን ስለ መጎብኘት እና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮችን ስለ ማባከን ከንቱነት እየጻፉት ለነበረው ድርሰት የተውጣጣ መጣጥፍ ልናበረክትላቸው የበኩሌን ማዘጋጀቴ ትዝ ይለኛል። ወድደውት ስለ ነበረ አዎንታዊ የሆነ ግብረ-መልስ ሰጥተውኝ በዚያ ያልበሰለ ዕድሜ ላይ ያ ሁኔታ በጣም ከፍ አድርጎ ያነሣኝ ነገር በመሆን ሰነበተ።

ሌላኛው የትምህርት ስኬቴን በጠቅላላው የለወጠው አስተማሪ የገጠመኝ እዚሁ 10ኛ ክፍል እያለሁ ከኤርትራ የመጣ ሳይሆን አይቀርም ብዬ የምገምተው ጋሽ ኢሳይያስ በኢዩተአ መርሐ-ግብር እኛ ትምህርት ቤት ውስጥ በሒሳብ አስተማሪነት ሲመደብ ነበር። ከእርሱ በፊት ከቍጥሮች እና ፊደሎች ጋር መጫወት ምንም እስከማይስበኝ ድረስ የሒሳብ ትምህርት፣ በተለይም ሁሌም የምታገልበት ጂኦሜትሪ፣ ለእኔ ምንም ትርጒም ሰጥተውኝ አያውቁም ነበር። ሒሳብን ቀላል እና ለመረዳትም ሆነ ለመከተል ምክንያታዊ እንዲሆን እስኪያደርገው ድረስ ወጣት የነበረው ይህ አስተማሪ ለሒሳብ ተዘግቶ የኖረ የመሰለውን አእምሮዬን በተወሰነ መልኩ ከፈተው። ይህንን መገለጥ አንድ ጊዜ ካገኘሁ በኋላ፣ እስከ መጨረሻው የሁለተኛ ደረጃ እና የኮሌጅ ዓመታት ትምህርቶቼ ጥሩ ውጤት የማመጣ ጎበዝ የሒሳብ ተማሪ ሆንኩ። በመጀመሪያ ዓመት ትምህርቴ በሒሳብ የ‘ኤ’ ውጤት፣ በሁለተኛ ዓመት ትምህርቴ ደግሞ ለመልክዐ-ምድር አጥኚዎች በሚሰጠው ትሪጎኖሜትሪ የ ‘ኤ-’ ውጤት አገኘሁ።

ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ዜና ይዘው ይመጡ የነበሩት ከኢዩተአ መርሐ-ግብር የተመደቡልን የታሪክ መምህሬ ጋሽ ሥዩም በአእምሮዬ ውስጥ ጥቂት መርዝ ጨምረውብኝ የፖለቲካ ሐሳቦች ቀስ በቀስ እየሳቡኝ እንዲሄዱ አደረጉ። መንግሥትን በግልጽ ይተቹ የነበሩት ጋሽ ሥዩም *‘በሬለት መርገጥ’* የተሰኘ የኃይለ ሥላሴን አስተዳደር የሚያጣጥልና በጣም በምጸት የሚያቃጥል ረጅም ግጥምን ጨምሮ ሌሎችንም የተከለከሉ ጽሑፎችን በክፍል ውስጥ ያነቡልናል፤ ከክፍል ውጪ ደግሞ በክፍል ከሆነው ይልቅ እርሳቸውን መስማቱ ስለሚያስደስተን አዘውትረን እንገናኛለን። ቀላል

የማይባል ጊዜዋን የአውሮጳውያንን ታሪክ በማስተማር የምታሳልፈው ዘዴኛና ኮስታራ አስተማሪ ሆና ታሪክን በ10ኛ ክፍል ያስቀሰመችኝ አሜሪካዊቷ ሚስ ሮሲኒ ስትሆን፣ ከእርሷም በዓለም ታሪክ ላይ የ16ኛው ክፍለ ዘመን የስፔናውያን ድልን፣ የሮም ካቶሊክ የእምነት ምርመራን፣ የፕሮቴስታንት ተሐድሶን፣ ደም-አልባውን አብዮት ዓይነት አዳዲስ ሐሳቦችን ተማርኩ። ብዙም ሳይቆይ የቃላት ክምችቴን የምገነባበትን አዳዲስ ቃላት ላሰባስብ እንጂ፣ ከእርሷ የወሰድኩት ትምህርታዊ መነሣሣት በጣም ጥቂት ነበር።

እንደ ግርማ መኮንን፣ ሚሊዮን፣ ፎዚያ እና ሌሎችም እሳት የላሱ ተማሪዎች ወደ ነበሩበት 11ኛ ክፍል መግባቴን ልክ እንደ ትልቅ ምዕራፍ በምቆጥርበት መልኩ በ11ኛ ዲ ክፍል ውስጥ ተመደብኩ። የተማሪን ዕጣ ፈንታ የሚወስነው ዓመት 12ኛ ክፍል የሚገባበት ዓመት በመሆኑ፣ የእንጋፋነት እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪነት የቀረብኩ መሆኔን በሚነግረኝ ስሜት ውስጥ ፍርሃት እና ደስታ ተቀላቀሉብኝ። አጭር እና በእድሜዬ በአንጻሩ ገና ልጅ የምመስል በመሆኑ፣ ልክ እንደ አየር ኃይል ወይም ወታደራዊ አካዳሚ ላሉ አንዳች ዓይነት ሙያዎች ለመመልመል ልበ ሙሉነት ተሰምቶኝ አያውቅም። ስለ ሆነም ብቸኛው ተስፋዬ እና ከዚህ የምወጣበት መንገድ ዩኒቨርስቲ መግባት ነበር። በውጤቱም ምንም እንኳን ትኩረቴን ለመሳብ የሚሞክሩ ሌሎች ነገሮች ቢኖሩም፣ ወደዚያው አልም ጀመር።

በእኔ እድሜ ከነበሩ ሌሎች ተማሪዎች ጋር ስተያይ በመጠኑ ዓይናፋር የነበርኩ ይመስለኛል። በሰዎች ፊት በነጻነት ለመሳቅ ምቾት ተሰምቶኝ እስከማያውቅ ድረስ ከንፈሬን በትክክል እንዳልከድን በማድረጓ በመጠኑ የምታስቸግረኝ ገጣጣ ጥርስ ነበረችኝ። አጭር ከመሆኔ ጋር ተዳምሮ የጥርሴ ሁኔታም ልበ ሙሉነትን እንዳጣ እና ለዓመታት ያጠመደኝ አስተማማኝ ስሜት የማጣት ሁኔታ ውስጥ እንድገባ የራሱን አስተዋጽዖ አድርጓል።

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጨረሻው ዓመት ትምህርት ላይ ስደርስ ፖለቲካ በሚጨምር መጠን ይማርከኝ ጀመር። ከሕዝብ ቤተ መጻሕፍት በርከት ያሉ የታሪክ መጻሕፍትን ባነበብኩ ቍጥር፣ ለፖለቲካዊ ሐሳቦች የበለጠ እየተጋለጥኩ በመምጣቴ አዳዲስ አስተሳሰቦችን፣ እና ንቃቶችን በአእምሮዬ ውስጥ ስለ ቀሰቀሱት የግሪክ ዲሞክራሲ፣ ፊውዳሊዝም፣ የኢንላይትንመንት ሐሳቦች፣ የፈረንሳይ አብዮት፣ የአሜሪካ አብዮት እና የመሳሰሉት በመጠኑ





ማንበብ ጀመርኩ። ይሄ በአዲስ አበባ ከነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጋር አብሮ የሚሄድ ስለ ነበረ፣ ከኢዩተአ መምህራን ወይም ከአካባቢው የተማሪዎች ኅብረት ባፈነገጠ መረጃ ወይም ከአጭር ጊዜ የማነባቸው ነገሮች፣ ብቻ አዲስ አበባ ውስጥ ባሉ ዩኒቨርስቲ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩት ተማሪዎች ባስነሡት ዐመፅ ላይ የበለጠ ፍላጎት አደረብኝ። በዘመኔ የነበሩትም እንዲሁ ዓይነት ወጥመድ ውስጥ የገቡ ይመስሉ ነበር። ምንም ዓይነት የሚያነሣሣ ሐሳቦች ከንባቤ ባገኝ ቃላቱ ባይገቡኝም እንኳን፣ በተወሰነ መልኩ ተማሪዎች ለዐመፅ እንዲነሣሡ ለማድረግ ስል በጥቁር ሰሌዳው ላይ ዘርዝሬ በመጻፍ አደባባይ መውጣቴ ቢቀር እንኳን፣ ቢያንስ በክፍሌ ውስጥ ሆኜ በተወሰነ መልኩ በድራማው መካከል ላይ ራሴን አኖርኩ።

ከየትኛው ምንጭ እንዳገኘሁት ባላስታውስም፣ ደግሞም የአባባሉን ጥልቀትና ሙሉ ፋይዳውን አውቄው የነበረ ስለ መሆኑ ብጠራጠርም፣ "ያለ ተግባር የሆኑ ሐሳቦች ያለ ዝናብ የሆኑ ዳመናዎችን ይመስላሉ" ብዬ ጽፌ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። የአባባሉ አጠቃቀሜ ግን በሌሎች የኢትዮጵያ ከፍሎች እየተስፋፋ የነበረውን የተማሪዎች እንቅስቃሴ መደገፌን በሚያሳይ መልኩ ረብሻን ለማስነሣት ስለ ነበረ፣ ከአኩዮቼና የክፍል ጓደኞቼ የበለጠ እውቅና በማግኘት በሚታይ መልኩ የበለጠ ገፋሁበት። ተማሪዎችም ክፍል ያለመገኘት አድማ በማድረግ የመሬት ላራሹን ጨምሮ ለውጥ እንዲደረግ ይጠይቁ ነበር።

አንድ ጊዜ ብሪታኒያዊቷ እንግሊዘኛ አስተማሪ ሚስስ. ፌርን በትምህርት ቤታችን ውስጥ የክርክር መድረክ አዘጋጀች። ለክርክር የቀረበው ጥያቄ፣ "የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለማቀፋዊ ድርጅት እንደ መሆኑ የተቋቋመለትን ዓላማ አሳክቷል ወይስ አላሳካም?" የሚል ነበር። እኔና አቡበከር (ኋላ ላይ የታወቀ የሕጻናት ስፔሻሊስት የሆነ) እርሱ በአዎንታዊው መከራከሪያ እኔ ደግሞ በአሉታዊው የቆምን ብቸኞቹ ተከራካሪዎች ሆነን ተገኘን። ክርክሩን በተሰጠው ጊዜ መጨረስ አልቻልኩም እንጂ፣ መከራከሪያዎችን ቅርብ ጊዜ ከወሰድኩት የዓለም ታሪክ ኮርስ በመውሰድ፣ ሶቭየት ሃንጋሪን የወረረችበትን ገጠመኝ፣ የኮንጎን ቀውስ፣ እና የመንግሥታቱ ድርጅት ሊያስቆማቸውም ሆነ ሊቀንሳቸው ያልቻላቸውን ሌሎች በርካታ የዓለም ግጭቶችን በማጣቀስ የአድማጮቻችንን ቀልብ እና ጭብጨባ አገኘሁ። ሚስስ ፌርን የምትወደው ተማሪዋ ስለ ሆንኩ፣ የእውነት እኔ እንዳሸንፍ ፈልጋ ንግግሬን በጊዜ እንድጨርስ

ሦስት ምልክቶችን ሰጠችኝ። ነገር ግን ሆነ ብዬ ማስጠንቀቂያዎቿን ችላ በማለቴ በመጨረሻ "ወድቋል" የሚለውን ቃል ተናገረች። ለእርሷም መልሼ "አይገደኝም" ማለቴን አስታውሳለሁ። የእኔን የመከላከያ ሐሳቦች ወደውት የነበሩ የሚመስሉትን መላ አድናቂዎቼን ስላተረፍኩ ክርክሩን ብሸነፍም፣ ቀኑን በማሸነፍ ትኩረቶችን ሁሉ የሳብኩት ዋና ማዕከል እኔ ሆንኩ!

11ኛ ክፍል ሳለሁ በጣም እውቀት ያላቸው እና በጣም የሚያነሣሡ ግሩም አስተማሪዬ ከነበሩት የመልክዐ-ምድር አስተማሪዬ ጋሽ አየለ መሸሻ ጋር በተያያዘ እስከ ዛሬ ድረስ በግልጽ የማስታውሰው አንድ አስደሳች አጋጣሚ ተከሰተ። እርሳቸው በቃል የሚጠና መረጃዎችን ከሞሉብን ከየትኛቸውም ሕንዳውያን መምህራኖቻችን በበለጠ ስለ ዓለም መልክዐ-ምድር፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ ስለ አፍሪካ እና ኢትዮጵያ፣ ብዙ አስተማሩንና አንድ ቀን ለሁሉም የ፲ኛ ክፍል ተማሪዎች ጥያቄ አቀረቡ። መልሱን ማናችንም ብናገኘው የቆርቆሮ ሰርዲን እንደሚሸልሙን ቃል ገብተው ስለ ነበር፣ ማንም ሰው በትክክል ያልመለሰውን ጥያቄ እኔ በመመለሴ ቱናውን ሸለሙኝ። ክፍለ-ጊዜው ሲጠናቀቅ በደስታ ሰክሬ ምን ማድረግ እንዳለብኝ የማላውቀው አንዱ ጥበበ ከሰርዲኑ መካፈል በፈለጉ በርካታ ጓደኞቼ ተከበብኩ። ከአብዛኞቻችን ጋር ሲተያይ በአንጻሩ ባለጠጎች ከነበሩ ቤተሰብ የመጣውና ብስክሌት የነበረው፣ ኋላ ላይ ግን በአለማያ ኮሌጅ ትምህርቱን ከማጠናቀቁ በፊት የሞተው፣ አፈወርቅ ለማ ከሌሎቹ ይልቅ ትኩረቴን ሳበው። ወደ መኖሪያ ቤቱ በብስክሌቱ እንደሚወስደኝና ለሁለታችንም ዳቦ ገዝቶ ሰርዲኑን እንደምንበላበት ስለ ነገረኝና ሐሳቡ ድንቅ በመሆኑ፣ ወደ እርሱ ቤት ሄደን በዚያ ምሽት ጥሩ ፌሽታ አሳለፍን። ያ አጋጣሚ በተወሰነ መልኩ ጥበበ ጎበዝ ተማሪ ነው የሚለውን የእኔን ምስል የሚያጠናክር ስለ ነበረ፣ በእጅጉ አነሣስተውኝ የነበሩትን ጋሽ አየለን ሁልጊዜም ቢሆን አመሰግናቸዋለሁ። ቆየት ብሎ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አግኝቻቸው ታሪኩን አጫውቻቸዋለሁ። ፒኤች.ዲ ዲግሪያቸውን በአሜሪካን አገር አግኝተው በዩኒቨርስቲው ውስጥ ፕሮፌሰር ሆነው ሳያቸው ደስ ብሎኝ ነበር።





## የቀድሞ የዩኒቨርስቲ ሕይወት

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በጥሩ ውጤት አጠናቀቅሁና በአገሪቱ ካሉት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ቁንጮ የሆኑትን ተማሪዎች በመሰብሰብ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተማሪዎች እንዲሆኑ ለማሠልጠን ወደተቋቋመው የልዑል በዕደ ማርያም ቤተ ሙከራ ትምህርት ቤት ገባሁ። የቤተ ሙከራው ትምህርት ቤት ይገኝ የነበረው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ የስድስት ኪሎ ግቢ ውስጥ ሲሆን፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚያስተምሩትን አስተማሪዎች ለማሠልጠን በከፍተኛ ሁኔታ ለሚመጥኑ መምህራን ማሠልጠኛነት የተዋጣለት እና በጥሩ ሁኔታ የተነደፈ መርሐ ግብር በመሆን ሲያገለግል ቆይቷል። መጀመሪያ ላይ የሳይንስ ተማሪ የነበርኩ ሲሆን፣ በፊዚክስ ትምህርቴ ላይ ከፍተኛ የሆነ ችግር ስላሳለፍኩ፣ ቆየት ብሎ ወደ አርት ትምህርት ቀየርኩኝ። ሕንዳዊቷ የፊዚክስ አስተማሪዬ ጥሩ ነበረች፣ ሆኖም የማስተማር ዘይቤዋ አስቸጋሪ በመሆኑ በእርሷ ክፍል ለመቆየትና በርትቼ ለማጥናት ጥረት ባደርግም፣ ትምህርቱን ምንም ያክል ልረዳው እንደማልችልና ለርእሰ-ትምህርቱ ልዩ ተፈጥሯዊ ችሎታ እንደሌለኝ እያረጋገጥሁ፣ በአንጥልጥል ነጥብ የማለፊያ ውጤቱን አገኘሁ። በመጨረሻ፣ የትምህርት ቤቱ ርእሰ-መምህር ከነበሩትና ተከታታይ ምክክር አብሬያቸው ካደረግሁት ከሚ/ር ግሪስዴል ጋር ለመገናኘት በመወሰን ወደ አርት ክፍል እንዲያዘዋውሩኝ ጠየቅኋቸው። ውጤቴ ጥሩ እንደ ሆነ በማሰብ እንድገፋበት በመምከራቸው ስለ ቀጠሉበት፣ አንድ ቀን ወደ ቢሯቸው ሄድኩና ፈንቅሎ በወጣ እንባ እየታጠብኩ እንዲረዱኝ አለቀስኩ። ከዚያም እርሳቸው የልመናዬን የምርነት በመረዳት በመንፈቀ ዓመቱ የመጨረሻው ሩብ ላይ ወደ አርት ክፍል አዘዋወሩኝ፤ እኔም ለአዲሱ ሽግግር እንደ ባሪያ ተግቼ መሥራት ነበረብኝ።

በጊዜው ፖለቲካ ጉልህ በሆነ መልኩ ተራማጅ እና ሲበዛ ታዋቂ አስተማሪ ስለ ነበረ የሚስብ እንዲሁም የሚማርክ ኃይል የነበረውን የታሪክ አስተማሪ ገብሩ ታረቅን[10] ተዋወቅሁ። እርሱ፣ የታሪክ መምህር እንደ መሆኑ፣ በጣም እውቀት ያለው እና በጋለ ስሜት ሐሳቡን የሚያስተላለፍ ሰው ስለ ሆነ የእውነት አነሣስቶኛል። ስለ ማርክሲዝም የማውቀው ጥቂት የነበረ ቢሆንም፣ ታሪክን የሚያቀርበው ከግራ የፖለቲካ እይታ አኳያ እንደ ነበር ግልጽ በሆነልኝ መልኩ በሕይወቴ ውስጥ ግዙፍ የሆነ ምልክትን ትቶብኛል። ምናልባት ታሪክን

በጥንቃቄ ስለ ማጥናት ያስተዋወቀኝ እና ታሪክን ተራማጅ በሆነ አስተያየተ እንድመለከት ያደረገኝ ሰው እርሱ ሳይሆን አይቀርም። የእርሱን ክፍል የተቀላቀልኩት በትምህርት ዓመቱ ማብቂያ ላይ ስለ ነበረ፣ ስለ እኔ ብዙ የማያውቀው ገብሩ፣ በመጨረሻው ፈተና ወቅት የሚያስደምም መጣጥፍ በመጻፍ ስላስደነቅሁት፣ ይህ እንግዳ የሆነ ተማሪ ማን ይሆን በማለት ጥቂት ካጠየቀ በኋላ አገኘኝ። ወደ ቢሮው ጠራኝና የሚያስደንቅ መጣጥፍ እንደ ጻፍኩ ከነገረኝ በኋላ፣ ዓመቱን ሙሉ የት እንደ ነበርኩ ሲጠየቀኝ፣ ሁኔታዬን አብራራሁለትና ኩራት በሚሰማው ደስታ ተለየሁት። ምናልባት ታሪክን እንዳጠና በጣም ተጽዕኖ ካደረጉብኝ ሰዎች አንዱ እርሱ ነበር።

በአንድ ግቢ ውስጥ እየኖሩ እና በጋራ እያጠኑ የነበሩ ትልልቅ ሰዎችን ለማግኘት ዕድል ያገኘሁበት የመጀመሪያው ቦታ የቤተ ሙከራ ትምህርት ቤቱ ሲሆን፣ በዚያ የነበረኝ ተሞክሮ በጣም ከፍ ያለ ፋይዳ ነበረው። የሐረር ሰው እንደ መሆኔ አብዛኞቹ የሐረር ሰዎች የነበራቸውን ዓይነት የተጫዋችነት ስሜት ስላልነበረኝ፣ ጥቂት የስብዕና ችግሮች ነበሩብኝ፣ ከዚያም ያለፈ የማንነት ቀውስ በሕይወቴ አጋጥሞኛል ለማለት እችላለሁ። በአስቸጋሪ ሁኔታ ካደግሁበት አነስተኛ ገቢ ከነበረው ቤተሰብ የመጣሁ በመሆኔ፣ እንዲሁም ቀደም ባሉት ጊዜያት በቤታችን ውስጥ የተሟላ ምግብ ያልነበሩባቸው ጊዜያት ስለ ነበሩ፣ የቤተ ሙከራው ትምህርት ቤት ስለ ቀጣዩ ምግቤ በማልጨነቅበት መልኩ ከዚያ ሁኔታ ገላገለኝ። መንግሥት የመኖሪያና የምግብ ወጪያችንን ስለ ሸፈነ ትምህርታችንን የምንማረው ምንም ሳንከፍል ሲሆን፣ ከሌሎች ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጋር በቀን ሦስት ጊዜ ምግብ እየተሰጠን ምግባችንን በራስ መኮንን አዳራሽ ካፍቴሪያ ውስጥ በአንድ ላይ እንበላ ነበር። በየትኛውም መስፈርት ጥሩ ምግብ ናቸው የምንላቸውን፣ በተለይም ደግሞ የቁርስ ምግቦችን እንደሰትባቸው ነበር። ለቁርስ፣ አራት ባለ ከብ ዳቦዎች ከሚቀባቡ ነገሮች እና ከቅቤ ጋር ይሰጠንና ምሳ ሲደርስ ደግሞ ቆንጆ ምግብ ይቀርብልናል፣ እራትም እንዲሁ። ማክሰኞዎች እና ሐሙሶች ላይ የምንናፍቃቸው የዶሮ ወጥ ምግቦች ይቀርቡልን የነበረ ሲሆን፣ ረቡዕዎች እና አርቦች ላይ ምሳዎቻችንን እንደ ሙዝ እና ብርቱካን ካሉ ፍራፍሬዎች ጋር ጭምር ይዘጋጁሉ። በዩ ብለን የምንጠራው ታዋቂው በየነ በካፍቴሪያው ውስጥ ከሚሠሩት ቅጥረኞች ሁሉ በላይ ጎልቶ ይታይ የነበረ ሰው ሲሆን፣ እርሱ ሁልጊዜ ትልቁን መስተንግዶ ለቤት ተማሪዎች ይሰጥ ወይም





ምርጥ የሚባለውን ፍራፍሬ ለእነርሱ ይመርጥላቸው ነበር። የእኔን ድርሻ በሚሰጠኝ ጊዜ ከሌሎች ለይቶ ትንሽ ምግብ በሣህኔ ላይ የሚያኖረው ገና ልጅ እና በቁመቴም አጭር ስለ ሆንኩ ይሆንን ብዬ እስከጠይቅ ድረስ ሁልጊዜ እንደሚያሳንሰብኝ አስተዋልኩ። አንዳንድ ጊዜ ትንሿን ብርቱኳን ይመርጥና በትሪዬ ላይ ያኖርልኛል። አንድ ቀን ብርቱኳኑን እፊቱ እስከወረውርበት ድረስ በጣም ተናድጄ ነበርና የጥበቃ ሠራተኛው መጥቶ እጄን በመያዝ ወደ አስተዳዳሪው ዘንድ ወሰደኝ። አስተዳዳሪው በጣም ትሑትና ሩኅሩኅ ሰው ስለ ነበር፣ የእውነቱን ሆኜ በፊቱ እያለቀስኩ ለምን እንደዚያ እንዳደረግሁ አስረዳሁት። በተረጋጋ መንፈስ እያባበለ ቍጣዬን አበረደውና አዲስ የምግብ ትሪ እንዳገኝ አደረገ።

የቤተ ሙከራ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአጠቃላይ በአንዳች ዓይነት የመረሳት ሁኔታ ውስጥ ስለ ነበርን፣ አንዳንድ ዓይነት የማንነት ችግሮች ነበሩብን። እኛ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ እንጂ፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እንኳን አልነበርንም። ይሁን እንጂ፣ የኅብረቱን መሪዎች በመምረጫ ዘመቻው ውስጥ ድምፅ መስጠት ካለመቻላችን በስተቀር፣ ትምህርቱንና ማኅበራዊ ሕይወቱን ጨምሮ በዩኒቨርስቲው ድባብ ውስጥ በጣም በፍጥነት ሰጥመን ስለ ነበረ፣ በሌሎች ዩኒቨርስቲዎች ካሉ ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ዕድሎች ነበሩን። ስለዚህም የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች በሆንንበት ጊዜ ላይ በጀማሪነት አዲስ ከሚመጡት ይልቅ እኛ የበለጠ ስለ ተዘጋጀን፣ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዩኒቨርስቲውን በቀጥታ ከተቀላቀሉት ጓደኞቻችን በበለጠ እኛ የበለጠ ብልህ የሆንን ያክል እናስመስል ነበር።

የቤተ ሙከራው ትምህርት ቤት ተማሪዎች የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ (ቀኃሥዩ) የፈጠረው ፖለቲካዊ ድባብ በከፍተኛ ሁኔታ የተጋባባቸው ነበሩ ማለት ይቻላል። በእርግጥ፣ አብዛኞቹ የቤተ ሙከራው ትምህርት ቤት ተማሪዎች በራስ መኮንን አዳራሽ ውስጥ የሚካሄደውን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ኅብረት (የዩተኅ)" ስብሰባ በነጻነት ይካፈላሉ። ግቢውን በሞላው የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ፣ በተለይም በየዩተኅ የምርጫ ቅስቀሳ፣ በፕሬዘዳንቱ፣ ጸሐፊው እና ሌሎች የጉባዔው አባላት ሹመት ሥነ-ሥርዓት ላይ መገኘት እንደ ትልቅ ክብር የምንቆጥረው ነገር ነበር። ተሰጥዖ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች በጣም በእንደበተ-ርቱዕነት፣ ምሁራንን ከየትኛውም መስከ በመጥቀስ

ንግግር ሲያደርጉ መስማት የሚያስንቅ ነገር ነበር። እንደ ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት፣ ጌታቸው ማሩ፣ ገብሩ መርሻ፣ ዳዊት፣ ጸጋዬ፣ ጸሎቴ፣ እና ሌሎችም ዓይነት ተማሪዎች በመኖራቸው ሁልጊዜም ቢሆን፣ "ልክ እንደ እነርሱ ለመሆን አቅሙ አለኝን?" ብዬ ራሴን እጠይቅ ነበር።

አብዛኛውን ጊዜ ቀልብን የሚገዙ ንግግሮችን የሚያደርጉትና ትልቅ የጭብጨባ ድጋፍ ከአድማጮቻቸው የሚያገኙት እንደ ዶ/ር እሸቱ ጮሌ እና ፕሮፌሰር እንድርያስ ያሉ ተራማጅ የፋኩሊቲ አባላት ለመከፈቻ ሥነ-ሥርዓቶች ተጋባዥ ተናጋሪዎች ይሆኑ ነበር።[12] ታዋቂ ዘፋኝ የሆነውና ዘፈኖቹ በድምፀታቸው ተራማጅ እንደ ሆኑ የሚቈጠርለት አለማየሁ እሸቴ ለክስተቱ በሚያስደስት ዓይነት ሁኔታ አንዳች ድምቀት እንዲሰጠው በተደጋጋሚ ተጋብዟል። በቀሪው ዘመኔ ላይ እንድጠቀምባቸው ብዬ አንዳንድ ቃላትን እና ተራማጅ፣ ደግሞም አብዮታዊ የሆኑ ሐሳቦችን በራሴ ሥራዎች ስብስብ ውስጥ ሠነድ እያደረግሁ ለማስቀመጥ ትጉሕ ነበርኩ። ምንም እንኳን አንድ ጊዜ ግነት የተሞሉ ንግግሮችን እንደተናገረው ገጣሚው ገብሬ መድኅን ያሉ ሰዎች የነበሩ ቢሆንም፣ የቤተ ሙከራ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ድምፃቸውን አውጥተው ለመናገር ግን ድፍረቱ የነበራቸው አልፎ አልፎ እንደ ነበር ይታወቃል። የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች በነበርንበት ጊዜ ከቤተ ሙከራው ትምህርት ቤት የመጣነው በተማሪዎቹ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተንበት መጠነኛ የሆነች አብዮተኝነት ስሜት ለቀሩት ጀማሪ ተማሪዎች እናሳያቸው ነበር።

ታኅሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም ላይ ከስድስት ኪሎ ግቢ ብዙም ሩቅ ባልሆነው የአፍንጮ በር አካባቢ በደኅንነት ሰዎች የተገደለውና የዩተኅ ፕሬዘዳንት የነበረው የጥላሁን ግዛው አሟሟት የቤተ ሙከራ ትምህርት ቤት ቆይታዬ ውስጥ ከማልረሳቸው ገጠመኞቼ አንደኛው ነበር። የመገደሉ ጭምጭምታ ተሰምቶ ዜናው በመላው ግቢ በተሰራጨ በቀጣዩ ቀን የዩኒቨርስቲውን ግቢ የከበቡትን የፖሊስን ትኩረት ወዲያውኑ የሳበ ግዙፍ የተማሪዎች ሰልፍ ተደረገ። የሟቹ ፕሬዘዳንት አስከሬን እንዲመጣና በአዲሱ የአርት ሕንጻ ፊት ለፊት እንዲቀመጥ ተደርጎ ተማሪዎች በመሞቱ ያለቅሱለት ነበር። ከኤርትራ መጥቶ በሕግ ትምህርት ቤት ውስጥ ይማር የነበረው ኀይቶም ከልቡ በሆነ ኀዘን ሲያለቅስ ማየቴን እና በተለያዩ ፖለቲከኞች ተከታታይ ንግግሮች ሲደረጉ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። በድንገት፣ በዋናነት ከአጥሩ ጎን ቆመው የነበሩት ጠባቂዎች





እንዲሁም ሌሎች የደኅንነት ኃይሎች ግቢውን በመውረር፣ የሟቹን አስከሬን ወስደው ከተማሪዎች ጋር መጋጨት እንደ ጀመሩ የጦር መሣሪያ ቶኩስ እና የተማሪዎችን ጩኸቶች ሰማሁ። ተማሪዎች በየአቅጣጫው መሮጥ ሲጀምሩ፣ እኔ እና በተፈጥሮው ሲበዛ ጥንቁቅ የሆነው የልጅነት ጓደኛዬ በለጠ ወደ ቤተ ሙከራው ትምህርት ቤት ማደሪያ ክፍሎች ሮጠን አፍንጮ በር ትይዩ ያለውን ትልቁን ግድግዳ ዘለልነው። ያንን እንዴት እንዳደረግነው ባላውቅም፣ ወደ ፒያሳ መሮጣችንን ግን ቀጠልን። ኋላ ላይ ነገሩ ሲረግብ ወደ ግቢ ተመልሰን አንዳንድ ተማሪዎች እንደ ተገደሉ፣ ሌሎቹ ከፉኛ እንደ ቆሰሉ፣ ወደ እስር ቤት የተወሰዱ ሌሎችም እንደ ነበሩ ሰማን።

ቆየት ብሎ እንደ ተሠዉት እንደ ማርታ እና ዋለልኝ ያሉ ሰዎች ጎን ለጎን እንደ ሰማዕት የተቈጠረው ጥላሁን ግዛው የተፈጸመበት ግድያ በተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ትልቅ የታሪክ ለውጥ ካደረጉና መነሣሣቶችን ከፈጠሩ ቅጽበቶች አንዱ ሆነ። በመሆኑም፣ በእያንዳንዱ የተማሪዎች ሰልፍ ላይ የሚሰማው የለቅሶ መዝሙር፣ 'ማርታ ለምን ለምን ሞተች፣ ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ፣ በኃይል በትግል ነው ነጻነት የሚገኘው' የሚለው ሆነ።

የብሔር ብሔረሰቦችን ጉዳይ ከተራማጅ የማርክሲስት እይታ አኳያ በድፍረት ለውይይት ያመጣው የመጀመሪያው ተማሪ የሚያስደንቅ ተናጋሪ የነበረው ዋለልኝ ሲሆን፣ 'የሕዝቦችን በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል' ለሚለው አቋሙ በግልጽ ተሟግቶለታል። ይህ የሚያስደነግጥ ጉዳይ ከተጨቆኑ ሰዎች ጋር በተያያዘ አንዳች ዓይነት ነጻነትን እንደሚቀሰቅስ አብዮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ በእውነት ለመረዳቴ እርግጠኛ አይደለሁም። በኢትዮጵያ ዐውድ ውስጥ ሊኖረው የሚችለውን ኮስታራ ትርጉም አላወቅሁም ነበር። ምናልባት ለእርሱ እንዲያው ዝም ብሎ ያቀረበው የመሟገቻ አባባል ነበር ወይም በቀላሉ ማርክስ ወይም ኤንግልስ ወይም ስታሊን የተናገሩትን እያስተጋባ ሊሆን ይችላል፣ አሊያም ደግሞ ግልጽ የሆነ አጀንዳ የነበራቸው ሰዎች መጠቀሚያ ወይም ቃል አቀባይ ሆኖ የተሰማራበት ነበር ማለት ይቻላል። ከእነዚህ ሊሆኑ ከሚችሉ ነገሮች ውስጥ እርሱ የትኛው እንደ ሆነ ለይቼ ማወቅ ባልችልም፣ ሐሳቡ ተራማጅ ሐሳብ እንደ ሆነ ተደርጎ ተወሰደ፣ ደግሞም ሐሳቡን የተናገረውና የተሟገተለትም እንዲሁ ተራማጅ ተደርጎ ተቈጠረ። እስከማስታውሰው ድረስ፣

ሐሳቡ በተማሪዎች ጉባዔ ላይ በሕዝባዊ ሁኔታ ተግዳሮት ያልቀረበበት መሆኑ ሳያንስ፣ እንደውም ቆየት ብለው በመጡት ዓመታት ላይ የበለጠ አዝማሚያን አገኘ።

ከመላው ዩኒቨርስቲ ልምምዴ እና የምሥረታ እውቀት የመቅሰም ሕይወቴ መካከል ምርጥ የምለው ነገር በመጀመሪያ ዓመት የትምህርት ሕይወቴ ውስጥ የአርት ፋከልቲን መቀላቀሌ ሲሆን፣ እንደ የታሪክ ምሁሩ ዶ/ር ቫንዳል፣ የማኅበረሰብ ጥናት ምሁሩ ማራ ላርሰን፣ ካናዳዊው የኢየሱሳዊያን (ጀሲዩስቶች) ፈላስፋ ዶ/ር ከላውዴ ሰመር፣ ፕሮፌሰር ሳቫርድ፣ ዶ/ር ዱሪ እና በከፍተኛ ደረጃ ሙያተኞች የሆኑ ከአገራቸው የወጡ እና ተወላጅ የሆኑ መምህራን ሥር ቁጭ ብዬ የተማርኩ በመሆኔ ዕድለኛ ነበርኩ። አዳዲስ ሐሳቦችን ለመማር በጣም ጉጉ የነበርኩ ታታሪ፣ ጊዜዬን በጥንቃቄ እጠቀም የነበርኩ ሥርዓት የያዘ ወጣት እና ትኩረቴን በጥሩ የጠበቅሁ ተማሪ ነበርኩኝ። ወደ ካፍቴሪያ የምሄደው ለመስተናገድ የመጀመሪያው ሰው እንድሆን ከመከፈቱ በፊት ሲሆን፣ ከእራት በኋላ፣ ወደ ስድስት ኪሎ ኬኔዲ ቤተ መጻሕፍት በመሄድ ከምላ ጎደል እስከ 5 ሰዓት ከምሽቱ ድረስ አጠናና ወደ ማደሪያዬ ቁልቁል በእግሬ እሄድ ነበር። የተመደብኩት በ45 ኤፍ አስፋወሰን አዳራሽ ሰለሞን ጢቂሶ፣ ማህፉድ፣ እና ፍስሐ ከሚባሉ ሌሎች ሦስት ተማሪዎች ጋር ነበር። የክፍል የቤት ሥራዎቼን ዕለታዊ በሆነ መልኩ አጠናቅቄ እንደሆን፣ የሁሉንም ክፍሎች ዕለታዊ ገለጻዎች ከልሼ እንደሆን በማጣራት እና በትክክል እርግጠኛ ባልነበርኩባቸው ርእሶች ላይ ተጨማሪ ንባቦችን በማድረግ ከእያንዳንዱ ትምህርታዊ ገለጻ በፊት ሁልጊዜ ቀድሜ በማንበብ እዘጋጅ ነበር።

በዚያን ዘመን ከፈተና በኋላ የውጤት መግለጫችንን በደብዳቤዎች መቀበላችን የተለመደ እንደ መሆኑ፣ የእኔን ስቀበል፣ በተሟላ ውጤት አልፌ ነበርና "የማዕረግ ተማሪ" በመባሌ በጣም ተደንቄ ያየሁትን ማመን ሳልችል ቀረሁ። የማስታውሰው ነገር በጀማሪ ተማሪዎች ሕንጻ ላይ ትሠራ ወደ ነበረችው ጸሐፊ ሄጄ የተቀበልኩት ደብዳቤ የእኔ እንደ ሆነ ወይም እንዳልሆነ መጠየቄን እና ደብዳቤውም ትክክል መሆኑን እንዳረጋገጠችልኝ ነበር። በርትቼ ሠርቼ እንደ ነበረና በቤት ሥራዎቼና አጋማሽ ፈተናዎቼ ጥሩ ውጤቶች እንደማገኝ አውቅ ነበር፣ ነገር ግን ከጄኔራል ዊንጌት፣ ሴንት ጆሴፍ፣ እና ናዝሬት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ካሉ በርካታ ተፎካካሪ ተማሪዎች መካከል በጥሩ ሁኔታ





በእውነት ከፍ አድርጎኝ ስለ ነበረ፣ በራስ መተማመኔን እና ያለኝን የራስ ምስል የበለጠ ጨምሮልኝ ራሴን የተለየ ሰው አድርጌ አየሁት። የሚያሳዝነው፣ ያ ሁኔታ የኋላ ኋላ ወደ አንዳች ዓይነት የተሳሳተ መንጠባረር ዳብሮ የሄደ መሆኑ ነበር።

ከእኔ ክፍል ጎን በክፍል 45 ውስጥ መኖር ከጀመረውና የዩተጎ ጸሐፊ ከነበረው አማረ ዓይነት የተለያዩ ተራማጅ የአመለካከት አቅጣጫዎች ከነበሯቸው ተማሪዎች ጋር መጣመር ስለ ጀመርኩ፣ በጀማሪ ዓመት የሁለተኛ መንፈቅ ዓመት ትምህርቴ ላይ የፖለቲካ መዳበሮች ቀስ በቀስ ሕይወቴን ተቆጣጠሩት። አንዳንድ የማርክሲስት ሥነ-ጽሑፎችን አነብብ የነበረ ሲሆን፣ በዋናነትም የማነባቸው የማዎን መጽሐፍ (ከሊቀመንበሩ ማዎ ዜ ቱንግ)፣ እና የተለያዩ መጣጥፎችን ከፔኪንግ ቅኝቶች ነበር። ቀስ በቀስ ከማነባቸው ነገሮች ተጽዕኖ እያደረብኝ ስለ ሄድኩ፣ ምንም እንኳን እንዲያው ዝም ብዬ የደጋገምኳቸው ሆኖ ሳለ ከሥነ-ጽሑፉ የወጡ አንዳንዶቹን ሐሳቦች በሕዝባዊ መድረኮች ላይ ልክ በጥንቃቄ ያጠናኋቸው ያክል ወርወር አደርጋቸው ጀመር።

ለየዩተጎ ጉባዔ የመጀመሪያ ዓመት ዘመቻ በተደረገበት ወቅት፣ አማረ ራሱን ከዕጩዎች እንደ አንዱ አድርጎ አቀረበ። በዙሪያው ለነበርነው ተማሪዎች ልክ እንደ መሪ እየሆነልን የነበረ ሲሆን፣ ያስተላለፋቸውን አብዛኞቹን ሐሳቦች ከማዎ ሥነ-ጽሑፎች በመሰብሰብ ለምርጫው ያደርጋቸው የነበሩትን ዝግጅቶች፣ በተለይም ለዘመቻው የሚያዘጋጃቸው ንግግሮች በውስጤ ተቀርጸውብኝ እስከ ዛሬ በግልጽ እስከማስታውሳቸው ድረስ ድጋፋችንን ሁሉ ሰጠነው። እስከማስታውሰው ድረስ፣ አማረ ያን ያክል የሚሰብ ተማሪ አልነበረም፣ ደግሞም ጥሩ ውጤቶችን አምጥቶ የማያውቅና መካከለኛ ገቢ ከነበራቸው ቤተሰቦች የመጣ ይመስል የነበር ሲሆን፣ አብዛኞቹ አጃቢዎቹ ሚካኤል አንዶም፣ ፀሐይ አምደብርሃን፣ እና መስፍን ለማ የሚባሉ ከሴንት ጆሴፍ ትምህርት ቤት የመጡ ነበሩ።

ከትክክለኛው የዘመቻ ንግግር የሚያቀርብበት ቀን በፊት ያደርገው የነበረውን ልምምድና ዝግጅቶች አስታውሳለሁ። እኩዮቹ ልክ እንደ ታዳሚዎች በማስመሰል በፊቱ ተቀምጠን ረዥም ኃይለ ቃል የተሞላበትን ንግግሩን በማድመጥ ጭብጨባችንን ከለገስነው በኋላ፣ አስቀድሞም የተሰጡንን ግልጽ የሆኑ ጥያቄዎች እንድንጠይቀው፣ ከዚያም ልክ የእውነት የሆነ ያክል መልሶችን

እንዲሰጠን መጠበቅ ነበረብን። ጀማሪ ተማሪዎችን ወክሎ ለጉባዔ ምርጫ ንግግር ሲያደርግ የሆነው ነገር ይኸው የነበረ ሲሆን፣ ያንኑ ያሰላሰለውን ንግግር አቀረበና እኛ ደጋፊዎቹ (በተለያዩ ጠርዞች ራሳችንን ያስቀመጥን ነበርን) በልምምዱ ወቅት እንሥተናቸው የነበሩትን እነዛኑ ጥያቄዎች ጠየቅን፤ እርሱም ትልቅ ጭብጨባን አግኝቶ በዚያን ቀን አሸናፊ ሆነ። ትልቅ በሆነው ተሳትፎ ውስጥ በእንዲህ ያለ ዝግጅትና ብልሃት፣ ወደ ነውጠኛው የተማሪዎች እንቅስቃሴ እና ኋላ ላይ ደግሞ ወደ አገሪቱ ከፍተኛ ደረጃ ፖለቲካ ተወነጨፈ።[13]

የመጀመሪያውን መንፈቅ ዓመት ሳያልፉ ቀርተው በሰላም ዩኒቨርስቲውን የለቀቁ በርካታ ጓደኞች ስለ ነበሩ፣ የጀማሪ ዓመት ሁለተኛው መንፈቅ ዓመት የሚቆረቁር ጊዜ ነበር። የእነርሱ መሰናበት በሽሙጥ አጠራር ይታወቅ የነበረው "የገናው ምርቃት" በሚል ሲሆን፣ ያንን ጸንተው የዘለቁትም እየተሽጋገሩ ገፍቶ የመሄድን ሸክም እና ትምህርትን ለመከታተል የነበረውን የከረረ ነገር ተሰምቷቸው ቆይቷል። ከዚህ ዳራ በተቃራኒ፣ ፖለቲካው በርከት ያለ ቍጥር ባላቸው ተማሪዎች ላይ ጎጂ የሆነ የጥቃት ወረራን ስለ ፈጸመባቸው፣ ከስድስት ኪሎ የመጡ ተማሪዎች እንደ ቀስቃሽ ሆነው ይመጡና ለዩተጎ ጉዳይ እንድንቆም ያበረታቱናል። ከሁለተኛው መንፈቅ-ዓመት መጠናቀቅ ጥቂት ቀደም ብሎ፣ የተማሪዎቹ እንቅስቃሴ የዩተጎ አንዳንድ የግቢ እና የብሔራዊ ችግሮች በመንግሥት እና በዩኒቨርስቲው አስተዳደር እንዲፈታ ተራማጅ የሆነ አቋም ያዘ። ተማሪዎቹ ሕዋስ በሆነላቸው የዩተጎ በኩል አንዳንድ ጥያቄዎችን አቅርበው ጥያቄዎቻቸው ባልተመለሱላቸው ጊዜ በክፍል ውስጥ ላለመገኘት አድማ ማድረግ ጀምረው አስተዳደሩ በተማሪዎቹ ከቁብም ያልገባ ማሳሰቢያዎችን አንዱን በሌላው ላይ እየደራረበ አወጣ። ሁላችንም ወደየመጣንባቸው ክፍላተ አገራት መመለስ እስኪኖርብን ድረስ በተማሪዎቹ እና በአስተዳደሩ በኩል የነበረው እሰጥ-ገባ በስተመጨረሻ የጀማሪዎች መርሐ-ግብር ለጊዜያዊነት እንዲዘጋ አደረገ። ይህንን በማድረጋችን እኔ ወይም የቀሩት ጓደኞቼ ምን እንዳሳካን በእውነት ባላውቅም፣ እኔ ወደ ሐረር ሄድኩና ለጥቂት ወራት የማርክሲስትን ሥነ-ጽሑፍን እያነበብኩ እና ከአንዳንድ ተራማጅ ተማሪዎች ጋር እየተገናኘሁ ቆየሁ። ትምህርት እንድናቋርጥ እና ተሰጥቶን የነበረውን ዕድል እንድናጣ ያደረገን ሰበብ ለብዙዎቻችን፣ ቢያንስ ለእኔ እንኳን፣





ግልጽ ሳይሆን እስኪቀር ድረስ በአግባቡ ከተብላላ የማስተዋል ውሳኔ ይልቅ በዋለለ አስተሳሰብ የነበርን እውነተኛ አማኞች የነበርን ያክል ነበር። ተግባሮቻችን ትርጉም-አልባ እና ውጤት-አልባ እንደ ሆነ ለሚታያቸው ለወላጆቻችን አሳሳቢ ሸክሞች መሆናችን ሳያንስ፣ ሁላችንም ትምህርት ለማቋረጣችን ምክንያት አድርገን የነገርናቸው ነገር ዩኒቨርስቲው የተዘጋው በረብሻ ምክንያት እንደ ሆነ ነበር፤ ይኸው ነው! ከዚያ ባለፈ፣ ለትምህርቱ መቋረጥ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ቢሆን ወይም ከዚያ ውጪ ለነበረው የገንዘብ ፍላጎታችን እገዛ ያደርጉ ለነበሩት ወላጆቻችን እንኳን ይህ ነው የሚባል ዝርዝር ማብራሪያን አልሰጠናቸውም። ዘግየት ብሎ በመንግሥት ትብብር "የአጭር መርሐ-ግብር" ተብሎ የታወቀውን ሁኔታ የዩኒቨርስቲው አስተዳደር አመቻችቶ በማዘጋጀት የመጀመሪያ ዓመት የትምህርት መርሐ-ግብራችንን ማጠናቀቅ ቻልን። በዚህ ፕሮግራም ብዙዎቹ ጓደኞቻችን ተባረሩ ደግሞም ተራፊዎቹ ደግሞ ውጤቶቻችን በብዙ ተበላሸብን።

ቅጣቱ የሚፋለሙለት ጉዳይ እንዳላቸው እንዲሰማቸው በማድረጉ ምክንያት ተማሪዎችን ባሉበት የማቆየቱ እርምጃ የበለጠ ተራማጅ እንዲሆኑ የሚያደርግ ያልታሰበበትን ውጤት ይዞ መጣ። ተልዕኮ እና አንድነት እና የጋራ ዕጣ ፈንታ ዓይነት ስሜቶችን ጨምሮ እየሰጠን የማርክሲስት ሥነ-ጽሑፎችን ከበፊት ይልቅ በበለጠ ወኔ ስናነብብ ቆይተን ለቀጣዩ የትምህርት ዘመን በመጣንበት ጊዜ፣ የዩኒቨርስቲው ድባብ በከፍተኛ ሁኔታ ተለወጠ፣ ከፍተኛ ቍጥር ያላቸው ተማሪዎች የበለጠ በከባድ ሁኔታ በግቢ ፖለቲካ የሚሳተፉ ሆኑ። ይህም "ለውጥ ተቃዋሚዎች" ብለን እንጠራቸው ከነበሩ ለተራማጅ ሐሳቦች በቀላሉ ከማይረቱት እና የድሎት እና ሕይወትን በደስታ ለማጣጣም የፓርቲ ድግስ እንዲሁም ግልጽ የፍቅር ሕይወት ከሚመሩ ዳር ከያዙ "ሆን ብለው ሰው ከሚሸሹ" ዓይነቶቹ ጥቂቶች በስተቀረ ሁላችንን ያዳረሰ ጉዳይ ሆነ።

የመጀመሪያ ዓመት ትምህርቴን እንደ ጨረስኩ፣ ፈጽሞ ባልተዘጋጀሁለት ሁኔታ አውራ የትምህርት ጥናቴ እንግሊዘኛ እንዲሆን መመደቤ ሲነገረኝ፣ ያለኝን ጥሩ ውጤት እንደ ማሳመኛ በመጠቀም ውሳኔውን አስቀለበስኩት። ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ የልጅነት ጓደኛዬ ስለ ሆነ ከበለጠ መንግሥቱ ጋር ላለኝ ለዚያው ጓደኝነት ስል የመልክዐ-ምድር ጥናትን አውራ የጥናት አቅጣጫዬ አድርጌ መረጥኩ። ከአንድ መንፈቅ-ዓመት በኋላ፣ ጠቅላላው

ድምር ውጤቴ (ጂፒኤ) ከፉኛ እስኪጎዳ ድረስ ካርቶግራፊ የሚባለውን የትምህርት ዓይነት በመውደቅ፣ በጂኦሎጂ እና ሜትሮሎጂ የትምህርት ዓይነቶች ላይ ጥሩ ውጤት ባለማምጣት በጭራሽ ለመልክዐ-ምድር ጥናት የሚሆን ፍላጎት እንደሌለኝ አስተዋልኩ። ደካማ ውሳኔ እንደ ወሰንኩ አስተዋልኩኝና አውራ የትምህርት ዓይነቴን እንድቀይር የትምህርት (የኢዱኬሽን) ፋኩሊቲን ጠይቄ ከተወሰኑ ውጣ ውረድ የበዛባቸው ውስብስብ አሠራሮች በኋላ አውራ የጥናት ዓይነቴ የታሪክ ትምህርት እንዲሆን ተፈቀደልኝ። በሁለተኛው ዓመት የሁለተኛ መንፈቅ-ዓመት ትምህርቴ ላይ ታሪክን እንደ አውራ የትምህርት ዓይነት ብወስድም፣ ተማሪዎቹ ቀድመውኝ በመሄዳቸው ሽግግሩ ፈጽሞ የሚያስደስት አልነበረም። ግዙፎች አድርጌ የምቆጥራቸው እንደ ቤዱ፣ ጌታቸው፣ ኢዮብ ጠና፣ ኤለም፣ እና የመሳሰሉት ጥሩ ተማሪዎች የነበሩ ሲሆን፣ በእነርሱ ዓይን እንደ ድንክ እንድታይ የሚያደርግ ሁኔታ ይሰማኝ ነበር። በተጨማሪም፣ በቤተ ሙከራ ትምህርት ቤት ታሪክ ካስተማሩኝ ጋሽ ገብሩ ጋር ተቃራኒ የነበረው ዶ/ር ሰርገው የተባለ መምህር በጣም ዝግተኛ እና የማስተማር ዘይቤውም የተለየ በመሆኑ ጨርሶ አልሳበኝም ነበር። ምንም እንኳን በመስኩ፣ ማለትም በጥንታዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ላይ እውቀት የነበረው ሰው ቢሆንም፣ ለተማሪዎቹ ምንም ቁብ የማያሳይ እና ለሚያስተምረውም ርእስ የነበረው የጋለ ስሜት ጥቂት ነበር። የትምህርት ተስፋ መቁረጦቼ እየጨመሩ ሲሄዱ፣ ወደ ፖለቲካው የበለጠ እየሰጠምሁ በመሄድ አደንቃቸው የነበሩትን ተናጋሪዎች አመስላቸው ጀመር። በዩተንጎ ይዘጋጁ በነበሩ ብዙ ሕዝብ በሚገኝባቸው ስብሰባዎች ላይ ንግግር ማድረግ ስጀምር፣ አንደኛው ንግግሬ በሐረር መድኃኒዓለም ትምህርት ቤት ያስተምር የነበረ የቀድሞ የዩኒቨርስቲ ተማሪን ሞት ለማስታወስ ስድስት ኪሎ ግቢ ውስጥ በተዘጋጀው የተማሪዎች ስብሰባ ላይ ያደረግሁትን ንግግር እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። ቆሜ የጋለ ስሜት የነበረውን ንግግር ስለ አሟሟቱ ሁኔታ ከተናገርኩ በኋላ፣ ስሙ በወደቁ ጀግና የአገር ልጆች ተርታ እንዲጨመር በመግለጽ አጠናቀቅሁ። መኮንን ሐጎስ በመንግሥት ላይ ከፈጠረው አደገኛ ስጋት የተነሣ ሐረር ውስጥ በደኅንነት ሰዎች ተገድሎ የነበረ ዝነኛ የአብዮት ሰው ነበር። አብዛኞቻችን በዚያን ጊዜ ለመልካም ጉዳይ ነው ብለን እናምንበት ለነበረው ነገር ወጣት ሆኖ የሞተውን ለማሰብ በሕዝብ ፊት ስለ ቆምኩ እና ንግግር ስላደረግሁ በዚያን ቀን በተማሪዎች





እንቅስቃሴ ውስጥ ስፍራ አገኘሁ። ንግግሬ አንዳች ዓይነት ውጤት ነበረው፣ ነገር ግን የተናገርኩት ከሙሉ ልቤ ለሙቱ ተሟግቼለት ይሁን ወይም ወደ ዩተንጎ ፖለቲካ ለመካተት ስል ይሁን መለየት ያልቻልኩበት ጥያቄ ተፈጥሮብኛል።

በመላው የሁለተኛው መንፈቅ ዓመት ጊዜያት ውስጥ ግቢው የቀጠሉ ሰልፎች፣ ስብሰባዎች እና በተማሪዎቹ ኅብረት የተዘጋጁ ሰልፎች እየተከናወኑበት በተማሪዎች ፖለቲካ ይቃኝ ነበር። ግርማቸው እና ጌታቸው ማሩ በፊት ለፊታቸው ምንም ዓይነት ጽሑፍ ሳይኖር ትኩረት የሚስብ ንግግር ያደርጉ የነበሩና በእውቀታቸው፣ እንዲሁም ነውጠኛ ተራማጅ በመሆናቸው አሁን ድረስ የምደነቅባቸው ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ኅብረቱ ፕሬዘዳንት እና ጸሐፊ አድርጎ መረጣቸው፤ እኔም ነውጠኝነታቸው የተለየ መስመርን በያዘ ስል እመኝ ነበር።

ለተማሪዎች፣ ለአስተዳደሩ እና ለመንግሥት የብጥብጥ ዓመት የነበረው 1964 ዓ.ም የተማሪዎቹ ኅብረት ቀደም ካለው ዓመት ጀምሮ በአስተዳደሩ ተገድቦበት የነበረውን ነጻነት ለመመለስ ተከታታይነት ያላቸውን ጥረቶች ያደረገበትና ድርጅቱ ለተወሰኑ የግቢ ተያያዥነት ያላቸው ችግሮች የተፋለመበት ሆኖ ቆይቷል። በዚያ ላይ ደግሞ፣ ዓመቱ እየገፋ በሄደ ቊጥር የ “መሬት ላራሹ” ጉዳይ በጩኸት እየገፋ መሄድ በጀመረበት ሁኔታ የማያቋርጥ ተዐቅቦ በተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ስለ ነበረ፣ ያልተረበሸ የትምህርት ቆይታ በሳምንት ውስጥ የሚኖረን ከስንት አንዴ ነበር። በእርግጥ፣ በአንደኛው ኢጋጣሚ ላይ ለረጅም ጊዜ አክፍል ላለመገኘት አድማ አድርገን፣ መደበኛ የትምህርት ሂደቱን እንድንቀጥል በተደጋጋሚ ከአስተዳደሩ የሚመጣልንን ማስጠንቀቂያ ቸላ አልነው። በመጨረሻ፣ ሹማምንቶቹ ዩኒቨርስቲውን ዘጉትና አዲስ አበባ ጥቂት ከቆየን በኋላ በድጋሚ ወደ ክፍላተ-አገሮቻችን መመለስ ግድ ሆነ። በአዲስ አበባ ለቆየነው ለአንዳንዶቻችን ከዩተንጎ ከሆኑ አንዳንድ አብዮተኛ ተማሪዎች የተሠራጩ ምግብ የምናገኝባቸው ኩፖኖች ተሰጥተውን፣ አራት ኪሎ ባለው የዘውዲቱ ሆቴል ቢያንስ በቀን አንዴ ምግብ ለማግኘት ኩፖኑን እንጠቀምበት ነበር። ዘውዲቱ ሆቴል ከተማሪዎች እንቅስቃሴ ጋር ምን የሚያገናኘው ነገር እንደ ነበር ምንም ፍንጭ ባይኖረኝም፣ አዲስ አበባ በቆየሁበት ጊዜ፣ ጓደኞቼ እና እኔ ገንዘብ ከማጣት የተነሣ እራታችንን አንዳንድ ጊዜ እያለፍነው፣ ወደ አካባቢው ሻይ ቤት በመሄድ በጊዜው ‘ጮርናቄ’ ተብሎ የሚጠራውን ብስኩት ለበርካታ ጊዜ በመመገብ ሰንብተናል። የድርጅቱን

ማሳሰቢያዎች አክብረው ትምህርት የቀጠሉ ጥቂት ተማሪዎች ስለ ነበሩ፣ መማር ያቆምነው እነርሱን "አከሻፊዎች" ብለን ስንጠራ፣ ለራሳችን ግን ክብር የሚያስገኘውን "አብዮተኞች" የሚለውን ስም ሰጠን።

## በተንሳፋፊ ዓለም ውስጥ መኖር

በሕይወት ውስጥ ተልዕኮዬ ምን እንደ ሆነ በትክክል ባለማወቅ ከዩኒቨርስቲ ስላቋረጥኩ፣ ይኸው የ1964ቱ የትምህርት ሂደት መቋረጥ መደበኛ የሆነውን የሕይወቴን ዱካ በመረበሽ አስከፊና አደናጋሪ የሆነ ውጤት ነበረው። አብዛኛውን ጊዜዬን በአካባቢዬ በሰፋት ይወሰድ የነበረውን ጫት እየቃምኩ እና በጓደኞች አማካኝነት ከአንደኛው እጅ ወደ ሌላኛው ይዘዋወሩ የነበሩትን የማርክሲስትን ሥነ-ጽሑፍ እያነበብኩ በሐረር አሳለፍኩ። ቶሎ በመመረቅ ደሃዋን እናቴን መርዳት የምፈልግ፣ በትምህርቴ ስኬት ለማግኘት የምሻ እና ሥነ-ሥርዓት የነበረኝ ወጣት ልጅ ብሆንም፣ በድንገት መላው የግል መሻቶቼ ያን ጊዜ ጉዳይ ብለን ወዳልነው ነገር መስመር የያዘ መሰለ። ፋይዳውን ተገንዝቤውም ቢሆን ወይም ባይሆን ጉዳይ ያልነው ነገር አእምሮዬን ተቆጣጥሮት ስለ ነበር ቀስ በቀስ በእርሱ ተወሰድኩኝ። የበለጠ ተራማጅ የሆኑ ሥነ-ጽሑፎችን ከየትኛውም የሶሻሊስት ዓለም አነብብና ከዚያም የተነሣ በዩኒቨርስቲ እንዳየኋቸው ግዙፍ አብዮተኞች በጋለ ስሜት እናገርባቸው ነበር። ከትምህርትና ሥራ ጉዳዮች ይልቅ በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የበለጠ በሚወያይ የ‹‹በርጫ›› ቡድን ውስጥ ተቀላቀልኩ።[14] እንዲህ ዓይነቱ ቡድን በብዙዎቹ የእኛ ትውልዶች ሙሉ ለሙሉ ሳናስተውለው፣ በዋናነት ለማጥናት እና የትምህርት ጉዳዮችን ለመወያየት እንሰባሰብባቸው ለነበሩት ጥንታዊ የጥናት ቤቶቻችን ትልቅ ቅያሪ ሆኖ ተገኘ። ለጋራ ድጋፍ እና መተናነጽ የሆኑ ማኅበራት በተመሠረቱ ጊዜ የነበራቸው ሐሳብ በከፍተኛ ሁኔታ አንዱ ሌላውን በትምህርት እንዲበልጥ እና በትምህርት ቤትና ሕይወት ላይ ስኬታማ እንዲሆኑ ከማበረታታት አኳያ ነበር። አዲሶቹ ማኅበራት ግን ያለጥርጥር ታዳጊዎች ለነበርነው ለእኛ ሙሉ ለሙሉ ልንገነዘብ ከምንችለው በላይ የሆነ የአብዮታዊ ሐሳቦች መንሸራሸሪያ እና መዘዋወሪያ መድረክ ሆነው የበለጠ ፖለቲካዊ ይዘትን ተላበሱ። ድህነት ይሁን ብልጥግና ብቻ በአንዳች መንገድ በሐረር ትውፊት መሠረት ለ‹‹በርጫ›› በዓል የሚሆነንን ጫት መግዣ ብር አናጣም ነበር። ቀድሞ በለመድነው የጥናት ቤት ለምናገኘው የትምህርት ጥቅማችን





እንደምናውለው ከሚያስቡት ወላጆቻችን ገንዘብ እናገኝ እንጂ፣ አንዱ ከስተት ወደ ሌላው ሂደት እየመራ የወሰደኝ ሠንሰለት ተደርጎ ካልተገለጸ በቀር በዚህ በአዲሱ የሕይወት ዘይቤዬ ውስጥ እንድዋጥ ለማድረግ ወሳኝ የሆነውን ሚና በመጫወት ተጽዕኖ ያሳደረብኝን በሐረር የሚገኝ አንድ ነጠላ ሰው አላስታውስም።

ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳየው፣ ጀማሪ ተማሪ ሆኜም ቢሆን ከስድስት ኪሎ ይመጡ የነበሩና ታዋቂ የነበሩ "ፖለቲከኞች" ወይም የፖለቲካ አቀንቃኞች ሆነው "የተሳቡ ቡድኖች" በትምህርት ብርቱ የነበሩትን ተማሪዎች ወደ አብዮታዊው ሠፈር ሊያስገቧቸው ያጠምዷቸው እንደ ነበር አስታውሳለሁ። አንዳንዶቹ እኔንም አግኝተውኝ የነበረ ሲሆን፣ አብዛኛውን ጊዜ የእነዚህን ፖለቲካዊ አቀንቃኞች ውትወታ መቋቋሙ ከባድ ነገር ነበር። ተካ አማረ ከሚባል የምጣኔ ኃብት ትምህርት ዓይነትን ያጠና ከነበረ ተመራቂ ተማሪ ጋር ዘላቂ የሆነ ፖለቲካዊ ግንኙነትን ፈጥሬ ነበረና አንድ ቀን ስድስት ኪሎ በኬኔዲ ቤተ መጻሕፍት ፊት ለፊት ስንገናኝ፣ አንደኛው በክዋሚ ንኩማ ‹‹*ኒዎኮሎኒያሊዝም፡- ዘ ላስት ስቴጅ ኦቭ ኢምፔሪያሊዝም*›› የተሰኘውን መጽሐፍ እና ሌላኛው ደግሞ በሌዎፖልድ ሴዳር ሴንጎር የተጻፈውን መጽሐፍ ከቤተ መጻሕፍት እንዲያወጣልኝ ጠየቅሁት። መጽሐፎቹን አወጣልኝና እነዚህን መጻሕፍት ለማንበብ ለምን እንደ ተሳብኩ ሲጠይቀኝ፣ ስለ ማርክሲዝም እና ሶሻሊዝም ብዙ ማወቅ እንደምፈልግ እና ከዚህም የተነሣ በጉዳዩ ላይ የበለጠ መወያየት እንድችልና በተማሪዎች እንቅስቃሴም ላይ የበለጠ አብሬ መሄድ የምችል እንድሆን ፈልጌ እንደ ሆነ ነገርኩት። የዋህነቴን በማስተዋል በማርክሲዝም ላይ ከዚያ በላይ የበለጠ ኮስታራ የሆኑ መጻሕፍት እንዳሉ ነግሮኝ ከዚያ አጋጣሚ በኋላ ራሴን እንደ ደቀ መዝሙር የምሰጠው በጣም ገር እና ሐቀኛ ሰው ሆኖልኝ የረጅም ጊዜ ጓደኛዬ፣ በማርክሲዝም ዓለም ውስጥ ደግሞ አሠልጣኜ እንደ ሆነ ቀረ። እርሱ በሕዝብ ዘንድ ሳይታዩ ለተማሪዎች እንቅስቃሴ ጉዳይ ራሳቸውን ከሰጡ ጥቂት ሰዎች አንዱ በመሆን እውነተኛ የሆነ ከጥሩ እምነት የመነጨ አብዮትን የሚወክል ሰው ሆኖ አገኘሁት።

ከሽሜ ጋር ኋላ ላይ የቀይ ሽብር[15] የመጀመሪያዎቹ ሰለባ የሆነው ተካ አማረ ተገቢ የሆነ የማርክሲዝምን አጠናን የማውቅበት ምሪት ሰጠኝ። ሽሜ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ ጥሩ ጓደኛዬ የነበረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን በከፍተኛ ውጤት ጨርሶ ወደ ዩኒቨርስቲ የገባ በጣም ድንቅ

ተማሪ ነበር። በ1964 ዓ.ም ሽሜ የሕክምና ተማሪ በነበረ ጊዜ ከተካ[6] ጋር ላስተዋውቃቸው ዕድል አግኝቼ ሽሜን ለተካ በማስተዋወቄ ኋላ ላይ ለተፈጠረው ነገር ወሳኝ የሆነውን ሚና እንደ ተጫወትኩ ሲገባኝ አሁን ድረስ እጸጸታለሁ። ተካ መጥፎ ሰው ስለ ሆነ ሳይሆን፣ የእነርሱ መገናኘት እና የመሠረቱት ጥብቅ የሆነው ፖለቲካዊ ጓደኝነታቸው ወደ ሽሜ ሞት ስላመራ ነበር።

አንብቤያቸው በነበሩት መጻሕፍት እና ባሰባሰብኳቸው አብዮታዊ ሐሳቦች ብዛት እስኪደመም ድረስ ሽሜ በሕይወቴ ውስጥ የነበረውን ለውጥ እና ሕይወቴ ምን ያክል ተራማጃዊ ባሕርይን እንደ ተላበሰ አየ። በእኔ አቅጣጫ እንዲንቀሳቀስ እንድረዳው በቁም ነገር ሲለምነኝ ያሠለጠነኝ እና ጥሩ መጻሕፍትን ያቀረበልኝ ጥሩ ጓደኛ እንዳለኝ ነግሬው ከውትወታው የተነሣ ከተካ ጋር አስተዋወቅሁትና ፈጣን ጓደኛሞች ሆኑ። ሁለቱም በጣም እውነተኛ እና ቁጥብ ሰዎች በመሆናቸው፣ እርስ በርሳቸው የተኮራኮሙ ይመስለኛል። ሽሜ በእውነት በማርክሲዝም ሐሳብ ውስጥ ለመግባት ጓጉቶ የነበረ ይሁን ወይም ተካን እንዳስተዋውቀው ገፋፍቶት የነበረው ነገር ምን እንደ ሆነ በትክክል እርግጠኛ አይደለሁም። ብቻ በእርግጠኝነት የማውቀው ነገር ልክ በትምህርቱ እንደ ሆነው ሁሉ፣ በሁሉ ነገሮች ላይ እርሱ የበላይ መሆን የሚፈልግ ሰው እንደ ነበረ ነበር። ፖለቲካ ለእርሱ አዲስ መድረክ ሆኖ በዚያ ላይ ፍላጎት ቢያሳይም፣ አብሮ ተጓዥ መሆን ግን አልፈለገም። እርሱ ልክ እንደ እኔ ከድሃ ቤተሰብ ስለ መጣ፣ ለሁለታችንም ታዋቂ የነበረው "የጭቁኖች ሕዝባዊ ጥያቄ" በብርቱ የሳበን ነገር ነበር።

አንዳንድ ተራማጅ የሆኑ ተማሪዎች ለሁለት ዓመት ያክል ትምህርታቸውን እንዳይቀጥሉ ታግደው ሳለ፣ ትምህርት የተቋረጠበት የአንዱ ዓመት በንጥልጥል መቆየት ተጠናቅቆ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ሲመለሱ፣ እኔ ግን ሳልመለስ ቀረሁ። በውጤት መግለጫዬ ላይ ከተረጋገጠው ጥሩ ውጤቶቼ የተነሣ እና በጣም ጥሩ በሆነ መልኩ ከተካሄደው ቃለ መጠይቅ የተነሣ ሥራ ተሰጥቶኝ በትምህርት ሚኒስቴር ሥራ ያመለከትኩበትን አንድ ዓመት በምርጫዬ ጨመርኩበት። እንግሊዘኛ እንዳስተምር በተመደብኩበት ሐረርጌ ክፍለ-ሐገር ውስጥ የተለየ ኃላፊነት ተሰጠኝ፤ በዚያ አጋጣሚ ደደር ውስጥ በሚገኘው የግራዝማች አበራ ግዛው ትምህርት ቤት ውስጥ በታሪክ ትምህርት የማስተማር ሥራ ላይ ተሠማራሁ።





በ7ኛና 8ኛ ክፍል ውስጥ የታሪክ አስተማሪ መሆኔ በአካባቢው ውስጥ ራሴን ተራማጅ አብዮተኛ በማድረግ የተማሪዎች እንቅስቃሴ አምባሳደር እንድሆን ራሴን የማስማማቱን ዕድል ሰጠኝ። በቤተ ሙከራው ትምህርት ቤት ታሪክን ያስተማሩኝን እና ወዲያውም በትምህርት ቤቱ ውስጥ በጣም ታዋቂነትና ከበሬታ ያገኙትን ጋሽ ገብሩን አስመስዬ ታሪክን ማስተማር ጀመርኩ።

በእውነትና ከቅን ልብ በመነጨ አብዮትን የሚያካሂደውን ሽመልስ የተባለውን ሰው የተዋወቅሁት በዚህ ትምህርት ቤት ነበር። (ይሄኛው ሰው ከላይ ሽሜ ስለው የነበረው ሳይሆን፣ ሌላኛው ሽመልስ ነው)። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ከተዋወቅኋቸው ሁሉ በጣም ያነበበው እና በጸና አስተሳሰቡ ማርክሲስታዊ ግለሰብ የነበረው ሽመልስ የበለጠ ታዋቂ የነበረው ሽመልስ ማዎ በሚለው ቅጽል ስሙ ሲሆን፣ ገጣሚ፣ አርቲስት እና ስብዕናውም - በተለይም ለዛ ያለው ጨዋታው - የሚወደድ ሰው አድርጎታል። በጦር ሳይሆን፣ በአእምሮ እና ፍልስፍናዊ አመሉ ምክንያት የእኔ የትግል ጓድ ተደርጎ በእውነት ሊገለጽ የሚገባው የመጀመሪያው ሰው እርሱ ነው። እርሱ በጣም ውስብስብ የነበረ ሰው ሲሆን፣ የእኔን የወጣትነት ማርክሲስታዊ እይታ በጣም ጥልቀት ባለው እና የሚሰረስር በሆነ የገዛ ራሱ አስተዋይነት ይሞግተው ስለ ነበር የማርክሲሳዊ ሥነ -ጽሑፎችን አብረን የምናነብባቸውን እና ጠለቅ ያለ እውቀት በሌለኝ የዲያሌክቲካል እንዲሁም ሂስቶሪካል ማርክሲዝም ላይ ሰፊ ውይይት የምናደርግባቸው ‹‹በርጫ›› ወቅቶችን ከእርሱ ጋር መካፈሌ የእውነት ያስደስተኝ ነበር።

እንደ ገገማዋ ኢሉ ካሉት በስተቀር የቀሩት የደደር ሠራተኞች ራሳቸውን "አብዮተኛ" ብለው የሚጠሩ ከታሪክ በስተጀርባ የሚገኙ የደደብ ወግ አጥባቂዎች ጥርቅም አድርገን ስለምንቈጥራቸው ከእነርሱ ጋር ለመቀራረብ እንቸገራለን። ስሞቻቸውን የማላስታውሳቸው ከአሜሪካ የመጡ የፒስ ኮር (የሰላም ጓድ) ሁለት አስተማሪዎችን ገጠሬዎች ብለን እንጠራቸዋለን፣ ደግሞም ጓደኞቻችንም እንዳይሆኑ ዕድል እንነፍጋቸዋለን። በእርግጥ በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አላዋቂነት ለማጋለጥ ስል አጓጉል የሆኑ ጥያቄዎችን እያሣሣሁ ለእነርሱ ያለኝን ንቀት በማሳየት ሲሳቅባቸው እና ሲያፍሩ መመልከቱ ያስደስተኝ ነበር። በመደብ ትግል ጉዳዮች ላይ ውይይቶችን የምፈጥርባቸው እና ሆን ብዬ እነርሱን

ተሰፋ ለማስቀረጥ ወዳልተፈለገ ውይይት የምመራበት ጊዜያት ቢኖሩም እንኳን፣ ወደ ቤታቸው ለቡና ሊጋብዙን እና አልፎ አልፎ ምግብ አብረን እንድንበላ እስኪጠሩን ድረስ ደግ እና ትሑታን ነበሩ። ያን ጊዜ ለማድረግ አሰቤው የነበረው ምን እንደ ነበር በእውነት ባላውቅም፣ ለአጉል እና ቅያሜን ፈጣሪ ባሕርዬ ይቅርታን እንድጠይቃቸው ባገኘቸው ስል እመኛለሁ።

ሽመልስ እና እኔ ከትውልድ ከተማዬ ከጉርሱም የመጣውና ተሸመ የሚል መጠሪያ ኖሮት ከሌላ ትምህርት ቤት በተዘዋወረው፣ እንዲሁም በተለየ ባሕርይው በሚታወቀው አንጋፋው ዐማፂ ታጅበን። እርሱ የቤተ ሙከራው ትምህርት ቤት ተማሪ እና እንግሊዘኛን አውራ የጥናቱ ዘርፍ አድርጎ የተማረ ባለ ብሩህ ጭንቅላት ሲሆን፣ ትምህርቱን ሲያቋርጥ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል። የእርሱ ሐሳብ በኢዱኬሽን ፋኩልቲ ከሚቆይ ይልቅ በቂ ገንዘብ አጠራቅሞ ወደ ሕግ ትምህርት ቤት በመዛወር በመጨረሻም አስተማሪ ላለመሆን ሲል ለዩኒቨርስቲው መክፈል የሚያስችለውን ገንዘብ ለማዘጋጀት ነበር። በዚያን ዘመን፣ ከቤተ ሙከራ ትምህርት መርሐ-ግብር ከመጣችሁ እና አውራ የትምህርት ዓይነታችሁን ከፋከሊቲ ኦቭ ኢዱኬሽን ወደ ሌላ መቀየር ከፈለጋችሁ ዝውውራችሁን ለማስጸደቅ የተወሰነ ያከል ገንዘብ እንድትከፍሉ ትጠየቃላችሁ። ተሸመ የጎደለው ነገር ምን እንደ ሆነ ከፋኛ ሲገባው ሕይወቱ የሄደችበትን የተሳሳተ አቅጣጫዎች በመገንዘብ ወደ ዩኒቨርስቲ በመመለስ ትምህርቱን አገባዷል።



በአቦራ ግዛው ትምህርት ቤት ከተማሪዎች ጋር





ውይይታችንን ሁልጊዜ የሚገዛው የፖለቲካ ጉዳይ በሆነበት መልኩ ሦስታችን በአንድ ላይ ሆነን ‹‹በርጫ››፣ ከዚያም በኋላ አብረን ‹‹ጨብሲ›› እያደረግን በከተማይቱ ውስጥ ታዋቂ የሆነ የሥስቶቹ አብዮትን እቀጣጠልን። በየትኛውም የግብረ-ጉበ መሠረት መገዛት የማንፈልግ ሰዎች መሆን ስለ ጀመርን፣ ልክ አቅጣጫቸውን እንዳጡ መርከቦች በጣም ግድ-የለሽ ሕይወት እንኖር እና አብዛኛውን ጊዜ ሕይወታችንን ትልቅ በሆነ አስጊ አደጋ ውስጥ በሚጥል የጀብደኝነት ተግባራት ውስጥ እንገባ ነበር። በሌሊት ጭፈራ ቤቶች ለማሳለፍ፣ ገንዘባችንን ለመበተን እና ሙትት ያሉ ሰካራሞች ሆነን ለመመለስ ፒጆ መኪና የምንከራይበትን ወይም እንደ መድኃኒት ቤት ባለቤቱ ተሰፋዬ ያሉትን የመኪና ባለቤቶች ጠይቀን ድሬዳዋ ድረስ የምንነዳባቸውን አጋጣሚዎች አስታውሳለሁ። በዚያ የኮሮኮንች ዚግዛግ መንገድ በተለይም በደንገጎ መስመር ሰክሮ መንዳት ለአደጋ የሚያጋልጥ ነገር እንጂ አስደሳች ባይሆንም፣ ደጋግመን፣ ደጋግመን አድርገነዋል።

እያደረግሁ ከነበረው ነገር ጋር በሚረብሽ መልኩ ውስጣዊ ግጭቶች የነበሩኝ ቢሆንም፣ በውጫዊ ማንነቴ በማደርገው ነገር የምደሰት እየመሰልኩ እነዚያን የግል ስሜቶቼን ከማንም ጋር አልነጋገርባቸውም ነበር። ነገር ግን በውስጤ፣ “ትምህርትህን ያቋረጥከው ለዚህ ብለህ ነው? ከትምህርት የታገድከው ለዚህ ነው? የምትፋለምለት ጉዳይ የታለ?” እያለ በመጠየቅ ጭቅጨቃውን የቀጠለ ውስጣዊ ድምፅ ይነዘንዘኛል። ኋላ ላይ በፖለቲካ የሕይወቴ ረብሻ ጠፍቶ በቀረው የዕለት ሁኔታ መመዝገቢያ ላይ የግል ስሜቶቼን እየጻፍኩ እደብቃቸው ነበር። ይህ የውስጥ ግብረ-ገባዊ ድምፅ የሚኖረው የሕይወት ዘይቤ ውስጣዊ ድምፁን ትኩረት እስኪነፍገው ወይም እስኪደብቀው ድረስ ለወራት እና ወራት ቀጠለ።

1965 ዓ.ም ላይ፣ በከተማው ውስጥ ሦስታችን ትልቅ የተማሪዎች ተቃውሞ አደራጀን። በሐሳቦቻችን በብርቱ ተጽዕኖ ያደረግንባቸውን ተማሪዎች መረጥንና ለአካባቢው የሥልጣን ንጥቂያ ረብሻ እናዘጋጃቸው ዘንድ ቀንና ሌሊት ሠራን። ዒላማችን ከታዋቂው የቃሉ ቤተሰብ የሆኑትን ኦሮሞ የአውራጃው አስተዳዳሪ ደጃዝማች ሐሰን ኢድርገን ማዕከላዊውን መንግሥት እና የአካባቢውን አስተዳደር የሚተቹ በርካታ በራሪ ወረቀቶችንና ማስታወቂያዎችን በመጻፍ በምሥጢር ለተማሪዎቹ እንዲሠራጩ አደረግን።

በሚቀጥለው ቀን ሠልፉ እንደ ታቀደው ቢካሄድም፣ ሠልፈኞችን ለመበተን ዱላ እና ሌሎች መሣሪያዎችን በያዙ የፖሊስ ሹማምንት ሠልፉ ታገደ፣ ገበያ ላይ የነበሩትም ነጋዴዎች ዘወር ለማለት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። ፖሊስ በመጨረሻ ላይ ተማሪዎቹ የተባረሩበትን እና በየአቅጣጫው እንዲሮጡ የተገደደበትን አስለቃሽ ጋዝ እና ጥይት ሲጠቀም አንዳንዶቹ በእግራቸው ወደ መንደሮቻቸው አመለጡ፣ አንዳንዶቹ ከተማው ፊት ለፊት ያለውን ዌቢ ተራራ ወጥተው እዚያ ተጠለሉ። ሠልፉን የነደፍነው ዋና አርቃቂዎች በዝምታ ድራማውን ስንመለከት፣ ደግሞም እንዳንለይና እንደ ጠንሳሾች እንዳንከሰስ ራሳችንን ስናርቅ ከቆየን በኋላ ፍጻሜው ላይ ሁለት የሚሆኑት ምርጥ ተማሪዎቻችን ተተኩሰባቸው ቀላል ጉዳት እንደ ደረሰባቸው ሰማን። በከተማው ሁሉ፣ በደህንነት ኃይሎች ሳይቀር እንደ ተራማጅ ስለምንታወቅ ተማሪዎቹ ዐመፁን በራሳቸው እንደማያደርጉት የማያጠራጥር ነገር ቢሆንም፣ እንዴት እንደ ሆነ በማናውቀው መልኩ ተረፍን።

ሽሜ እና እኔ ሁልጊዜም ቢሆን ፈጽሞ ጨዋነት የጎደለውን ነገር በግልጽ እያደረግን ከማኅበረሰቡ በተለየ የባህሉ ተቃራኒዎች ሆነን መታየት እንፈልግ ነበር። አንድ ቀን ሐረር ውስጥ ባለው መድኃኔዓለም ትምህርት ቤት የቀድሞ የአማርኛ አስተማሪዬ የነበሩትና የሚለዩንን የትምህርት ቤት ርእሰ-መምህር ጋሽ ታደሰን በሚያከብር የሽኝት ዝግጅት አስተባባሪነታችን ውስጥ ሁለታችንም ተከሰስን። ሁሉን ነገር ጥራት ባለው መልኩ አዘጋጅተን፤ ነገር ግን ሠራተኛው ሁሉ እና የአውራጃው ትምህርት ቤቶች ኃላፊ ከመመጣታቸው በፊት ትሕትና በጎደለው መልኩ የትኛውንም ዓይነት ብልሹ ባሕርይ ማሳየት ስለ ጀመርን፣ ድግሱ እንደ ታቀደው መካሄድ ሳይችል ቀረ። የተጋበዙት እንግዶች መጥተው ቦታቸውን ከያዙ በኋላ ምግብና መጠጥ እያቀረብን እያለ ብዙም ሳይቆይ “ኢምፔሪያሊዝም የመሰናከያ ዓለት ነው”፣ “ፊውዳሊዝም ይውደም” እና “*ኮቡምፐራዶር ቡርዧዚ ይውደም!*” የሚሉ የእርግማን ንግግሮችን በመሰንዘር የፓርቲውን መንፈስ ሆን ብሎ ለማበላሸት እየጮኽን መፈክሮችን ማሰማት ጀመርን። ድግሱ እንደ ተጠበቀው እንዲሄድ ጨዋነታችንን እንድንጠብቅ በተደጋጋሚ ተጠየቅን። ነገር ግን ግንፍልነታችንን ልንቆጣጠር ባለመቻላችን እንግዶቹ ተራ በተራ እየለቀቁ ሲሄዱና መላው ድግስ ወደ ፍጹም አሳፋሪ ጥፋት ሲቀየር ለቅንጣትም ግድ አላለንም ነበር። እንደ ኢሉ ባሉ እኛን በሚመስሉ ሰዎች ታጅበን በዚያው ቆየንና ከሞላ ጎደል እስከንሞት ድረስ ቢራ መጠጣት





ጀመርን። ነገሮችን ለማስተካከል ምን ማድረግ እንዳለብን ባናውቅም፣ በሚቀጥለው ቀን በባለፈው ሌሊት ስላደረግነው ነገር በጣም አፍረን የምንገባበት ጠፋን። የትዳር አጋራቸው ፍሬዝ ጥሩ ጓደኛችን ወደ ሆኑት የአውራጃው ትምህርት ቤቶች ኃላፊ ጋሽ ሰኑ ቢሮ ለመሄድ ሁለታችን ወሰንንና በባለፈው ሌሊት ስለ ሠራነው ዘግናኝ ስሕተት አምነን ይቅርታ ጠየቅናቸው። እርሳቸው፣ ያን ጊዜ እስከንገረም ድረስ በቸርነት ይቅርታ አደረጉልን፣ ሲበዛ ደግ ሰው ሆኑልን። የቀረው ሠራተኛ በእኛ ይቆጣል ብለን ገምተን የነበረ ቢሆንም፣ ከዚያ ይልቅ፣ አንዳንዶቹ የሥራ ባልደረቦቻችን በእኛ ላይ ሲስቁ እና ባለፈው ጥፋታችን ሲደሰቱ የነበረ ያክል ሆነው በማግኘታችን በጣም ተገረምን። ብቻ፣ ሁላችንም በተንሳፋፊ ዓለም ውስጥ እየኖርን እንደ ነበርን እነዚህ ሁኔታዎች ጠቋሚ ናቸው።

በአጠቃላይ፣ የደደር ልምምዴ ለአእምሯዊ እድገቴ መዳበር ምንም ስላልጨመረልኝ፣ በሕይወቴ በእጅጉ ጊዜዬን ያባከንኩበት ነበር። ለፍትሕ ጉዳይ በተሠቃዩት እና ለፖለቲካዊ እምነታቸው መሥዋዕት በሆኑት አብዮተኞች መሠረት ላይ ራሴን ሳኖረው የኩራተኝነት ስሜት እንደ ነበረኝና የአብዮተኞቹን ደረጃ ለመቀላቀል የሞራል መሠረት እንዳገኘሁ አሁን ተሰማኝ። ራሴን እንደ ተራማጅ የማርክሲስት ታዋቂ ሰው አድርጌ የእውነት እንድቆጥር በቀላሉ ዐውድ የሚሆንልኝ ነገር አኑሮልኛል። ይህም ደግሞ ልሸከመውና ሊመጡት ላሉት ዘመናት ልገልጠው የምፈልገው ምስል ነበር። በእርግጥ የበለጠ የማርክሲስት ሥነ-ጽሑፍን አንብቤ በዩኒቨርስቲው ውስጥ የተማሪዎች እንቅስቃሴ የሚያነሷቸውን አንዳንድ የአካባቢው እና ዓለማቀፍ ጉዳዮች የበለጠ እና አብዝቼ የምወያይ ሆኜ ስለ ነበር፣ ከዩኒቨርስቲ ውጪ በሁለት ዓመት ልምምዴ የበለጠ ተራማጃዊ ሆኜ ወጣሁ።

## ከደደር ወደ ዩኒቨርስቲ

ደደር ውስጥ ለአንድ ዓመት ያክል ካስተማርኩ በኋላ፣ በኤሮግራም ደብዳቤዎች ከምገናኛቸው የክፍል ጓደኞቼ አንድ ዓመት ወደ ኋላ ብቀርም፣ ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ ጊዜው እንደ ሆነ ተሰማኝ። እኔ እና የቅርብ ጓደኞቼ ጥሩ የትምህርት ውጤቶች ያሉኝ ጎበዝ ተማሪ እንደ ነበርኩ እናውቅ

ነበር። እንደ ሰይፈቷ ያሉ ያለማቋረጥ ትምህርቴን እንድቀጥል የሚለምኑኝ አንዳንዶቹ ጓደኞቼ በሕይወቴ የተሳሳተ ዱካ ላይ የነበራቸውን ጭንቀት ይገልጡልኝ ስለ ነበር፣ ወደ ዩኒቨርስቲው ተመልሼ እንድገባ ለማመልከት ወሰንኩ። በዘመኑ በኢትዮጵያ ባሕር ኃይል ውስጥ የታወቁ ሰው ለነበሩት ለጄኔራል ታዬ ሴት ልጆች እንደ አስጠኚ ሆኜ በትርፍ ጊዜዬ እየሠራሁ ከፊል የሆነውን የማገኘውን ገንዘብ ለእናቴ እልክ ነበር።

በ1966 ዓ.ም የታሪክ ትምህርት ክፍልን በ2ኛ መንፈቅ ዓመት ልማር ወደ ዩኒቨርስቲ ተመልሼ ገባሁ። ይሁን እንጂ፣ ይህ ጊዜ የታሪክ ተማሪ የነበረው ጌታቸው በጋሻው በሚያስደንቅ ሁኔታ የዩተኅ ፕሬዘዳንት ሆኖ በማሸነፍ፤ አቦማ ምትኩ ደግሞ ጸሐፊ ሆኖ በመመረጥ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ከአዲሶቹ የአብዮት ትውልዶች ጋር ወደ መቋጫው መድረስ ጀመረ። ጌታቸው በንግግሩ ለዘብ ያለውንና አነስተኛ አሳማኝነት የነበረውን፣ እንዲሁም ለስለስ አድርጎ ይናገር የነበረውን፣ ሆኖም ብስለት ያላጣውን የሽመልስ ማዘንጊያን ንግግር በልጦት ሄደ። የውስጥ አድናቂነቴን እስኪያገኝ ድረስ ሌሎች የነበራቸው የማርክሲሳዊ አሳማኝ ሐሳብ ሰውን በሚማርክ እና ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እርሱ አልነበረውም።

በታዳሚነት ከተገኘሁባቸው በርካታ የዘመቻ ንግግሮች መካከል ከተለየ ጎራ የነበረው አንደኛው ዕጩ ንግግር ያደረገበትን አስታውሳለሁ። ያሸበረቀና እግሩ አካባቢ ሠፋ የሚል ሱሪ ይለብስ የነበረ፣ ጸጉሩንም ደግሞ አፍሮ አድርጎ ያበጥር የነበረ ወጣት ሲሆን፣ በጊዜው የእርሱን የሕይወት ዘይቤ የምንገልጸው በተለምዶው አጠራር "ጆሊ" እያልን ነበር። ከሴቶች ጋር ብዙ የሚጫወትበት ዝንባሌ እንደ ነበረው ጭምጭምታ የሚሰማበት ይኸው ወጣት የገዛ ራሱን የሚያስደምም ንግግር በሐሳባዊ አሳማኝነት ሳያዘጋጅ ደጋግሞ አቅርቧል። ማንነቱን አመሳስሎ በመደበቅ እና አብዮተኛ የመምሰል ሙከራ ሳያደርግ ለዕጩነቱ ሲቆም የነበረውን ተደማጭነት ባደንቅለትም፣ ለጥያቄዎች እና ለውይይት መድረኩ ክፍት ሲሆን፣ ጥያቄ ለማንሣት የመጀመሪያው ሰው የምሆነው እኔው ነበርኩ። የሰጠኝን ምላሾች ባላስታውስም፣ ጥያቄዬን የማበጀው ልክ እንደዚህ ነበር፦ "ጆሊ ሰዎችን በተመለከተ ያለህ መረዳት ምንድን ነው?" እና "በጆሊዎች ላይ ያለህ አቋም ምንድን ነው?" ጥያቄዎቼን የቻለውን ያክል በሐቀኝነት ከመለሰልኝ በኋላ፣ ልክ ክፍለ ጊዜው እንደ





ተጠናቀቀ፣ ጥሩ ጓደኛዬ የነበረውና አሁን በሕይወት የሌለው ቱሃ እውነተኝነት የሌለውን ጥያቄ በማንሣቴ ገሠጸኝ፤ ትክክል ነበር። ምንም እንኳን የእርሱን አይታ ለማወቅ የፈለግሁ ብሆንም፣ የውስጥ መነሣሣቴ ግን ዕጩውን ቀለበት ውስጥ ለማስገባት ነበር።

ተማሪዎቹ ለሳምንታት ክፍል ያለመግባትን አድማ በመምታት ሙቀቱና ግፊቱ መነሣቱን ስለ ቀጠለ፣ ብዙም ሳይርቅ መንግሥት መሻሻሎችን ሳይሆን፣ ሥር-ነቀል የሆነ መዋቅራዊ ለውጦችን እንዲያደርግ የተማሪዎቹ እንቅስቃሴ በመጠየቅ ተራማጅ በሆነ አቅጣጫ የተለጠጠ አቋም ያዘ። እየገነፈለ ያለው የተማሪዎች ተቃውሞ በሌሎች የማኅበረሰቡ ዘርፎች ውስጥ እየተጋባባቸው በመሄዱ፣ ወዲያውኑ የሁሉም ዓይነት ሰፊ አድማስ ያላቸው ተቃውሞዎች ከሕዝባዊ ዘርፎች ሲቀጣጠሉ አየን። አድማዎች በአስተማሪዎች፣ የታክሲ ሹፌሮች እና ሌሎች ሠራተኞች ጭምር ይደረጉ ነበር። ይህ ሁከት በዝግታ ትልቁን ረብሻ እየተቀላቀለ በነበረው ባልተጠበቀው የጦር ሠራዊቱ እንቅስቃሴ የታጀበ ስለ ነበር፣ ትምህርቴን ለመቀጠል ወደ ዩኒቨርስቲው የመጣሁት በተሳሳተ ጊዜ ላይ ነበር ብዬ እስካምን ድረስ ግራ ተጋባሁ፣ ደግሞም በተቀየጡ ስሜቶች ተሞላሁ። እየተከናወኑ በነበሩት ለውጦች እና የእነርሱም ተሳታፊ በመሆኔ ብደሰትም፣ ትምህርት በራሱ ያለውን ክብደት ለመወጣት አስቸጋሪ እስኪሆንብኝ ድረስ ከዓመት በላይ እጠጣና ባልተገራ የተድላ ሕይወት እኖር ነበር።

በትክክል ልገነዘበው ካልቻልኩት ነገር የተነሣ በተፈጠረብኝ ግራ መጋባት ሥራዬን በይፋ በሆነ መልኩ እስካቆም ድረስ በማስተማር የሥራ መስኬ ላይ ለመቀጠል ወሰንኩ። ውሳኔውን ካደረግሁ በኋላ፣ በአንደኛው ቀን "ዕጣ ፈንታዬ ተማሪ እንድሆን የተቀረጠ ሳይሆን፣ በሌላ ቦታ ነው" የሚለውን መልእክት ለአንደኛው ጓደኛዬ[17] ተውኩለትና የአውቶቡስ ቲኬት ቆርጬ ከአውቶቡስ ተራው አቅራቢያ በሆነ ቦታ ወደ ሐረር ለመሄድ ቀላል እንዲሆንልኝ መርካቶ ውስጥ ቤርጎ ያዝኩ። ይህንን ሳደርግ፣ ውሳኔዬን እንድቀይር ለማድረግና በትምህርቴ እንድቆይ ለማድረግ መላውን ቀን እና ሌሊት አብሮኝ ካሳለፈው ጓደኛዬ ጋር በችግር ያጠራቀምኳትን በቂ ያልሆነች ገንዘብ እያባከንኩ መላውን ሌሊት ስንጠጣ አደርን። በሚቀጥለው ቀን ሆቴሉን ለቀቅቀን ወጣንና ታክሲ ይዘን ወደ አውቶቡስ ተራ ከሄድን በኋላ ሻንጣዬን ለሹፌሩ ረዳት ሰጥቼ

ለጉዞው ተመቻችቼ ነበር። ያለማቋረጥ ይነዘንዘኝ የነበረው ጓደኛዬ ሰይፉ ሳያንሰኝ አውቶቡሱ ከመንቀሳቀሱ ጥቂት ቀደም ብሎ አንዳች ነገር መታኝና በድንገት "አልሄድም" አልኩኝ። ረዳቱን ሻንጣዬን እንዲያወርድልኝ ጠየቅሁት፣ እርሱም በብስጭት የተባለውን ሲፈጽምልኝ፣ ታክሲ ይዘን ወደ ስድስት ኪሎ ግቢ ተመለስን። ጥሩም ይሁን መጥፎ ብቻ በዚያ ማለዳ ያደረግሁት ውሳኔ ከዚህ በታች እንደ ተተረከው በሕይወቴ ላይ ከፍተኛ ውጤት ሊፈጥር ቻለ። [18]

ያለመታደል ሆኖ፣ በዩኒቨርስቲው ውስጥ የነበረው የፖለቲካ ሁኔታ ከፊት ይልቅ የበለጠ እየከፋ ስለ ሄደ፣ መደበኛ የትምህርት ስርጭቶችን ለመከታተል የሚበጅ ድባብ አልነበረም። የወሎ ክፍለ-ሐገር የረሃብ ሁኔታ የተማሪዎቹ እንቅስቃሴ ዋናው የሚታየው ነገር ቢሆንም፣ ኋላ ላይ ለተሳካው ለዩተን ወደ ነበረበት መመለስ ተማሪዎቹ መታገላቸውን አጠናክረዋል። በአገሪቱ ላይ የበለጠ ሥር-ነቀል ለሆነ ለውጥ በትምህርት ገበታ ላይ ላለመገኘት ማደማቸውን እና ሠልፍ ማድረጋቸውን ተማሪዎቹ ሲያፋፍሙ እየተገለጠ ባለው አስቻጋሪ ሁኔታ መሃከል፣ መንግሥት ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያዎችን ካወጣ በኋላ ተቋሙን ዘጋው። የዩተን ሁሉም ተማሪዎች በፈቃዳቸው ትምህርት እንዲያቋርጡ ያቀረበውን የመፍትሔ ሐሳብ በአብዛኞቹ ተማሪዎች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ልክ በ1964 ዓ.ም እንደ ነበረው ዓይነት ሁኔታ ውስጥ በድጋሚ ተጣልን። የዛኑ ያክል ሌሎች በርካታ ተማሪዎች ትምህርት ለማቋረጥ ፈቃደኞች ባይሆኑም፣ የድሬዳዋ ልጅ የሆነው የቀድሞው የቤተ ሙከራ ተማሪ ጅብሪል ግን ወረቀቶችን በእሳት በማያያዝ ከስተቱ አዲስ ክፍለ-ዘመን መበሰሩን የሰማ ያክል ሲፈነድቅ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። በእንቅስቃሴያችን ጥቅም እና ጉዳት ላይ ቆም ብሎ በነጻነት የታሰበበት ሁኔታ አለመኖሩ ሳያንስ፣ ለትምህርት መቋረጡ ተቃውሟቸውን ያሰሙ በርከት ያሉ ተማሪዎች ጫናው ልቆባቸውና አፍ አፋቸውን ተብለው ዝም እንዲሉ ተደረጉ። ብቻውን የቆመና አንዳንድ እንግዳ እይታዎችን በማንሣት ደግሞም እየተወሰደ ያለውን እርምጃ ዓላማ እና ግብረ-ገባዊ ሕጋዊነት በመጠየቅ ወጀቡን የተቃወመ አንድ ሰው ነበር። ከእይታዎቹ እንደማስታውሰው ከሆነ፣ በአብዮተኞቹ ዘንድ እንደ ሃይማኖተኛ ወግ አጥባቂዎች ይቆጠሩ ከነበሩት ከጴንጤዎቹ የመጣ ሊሆን የሚችል ሰው ሲሆን፣ በወቅቱ ተጨኸበት ከመድረክ እንዲወርድ ተደረገ። እንግዳ የሆኑ አስተያየቶች የነበሯቸው፣ ደግሞም በሆነ መልኩ ለመጮኽ ቅጽበትን የሚቆጣጠሩና





የተሰብሳቢውን ትኩረት የሚስቡ አንዳንድ ለየት ያሉ ተማሪዎች እንደ ነበሩ አስታውሳለሁ። ከእንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች አንደኛው "አረንጓዴው" እንለው የነበረውና አንዳንድ ጊዜ ጠበኛ ዝንባሌ ኖሮት ብረት የሚያነሣው ስፖርተኛ የማነ ነበር። በእርሱ እና ልክ እንደ እርሱ ያልተለመደ ባሕርይ በነበረው የሐረር ተማሪ ሰለሞን መካከል ጭቅጭቅ የተነሣበት አጋጣሚ ትዝ ይለኛል።

ለዚህ የተሳቡ ቡድኖች ያን ጊዜ "የዩተን መፍትሔዎችን ማስፈጸም" ተብሎ የሚጠራውን አዲስ እንቅስቃሴዎች ጀመሩ። መፍትሔውን ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ እርምጃዎች ተሞክረው የነበረ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ክልልን መሠረት ያደረጉ፣ አንዳንዶቹ ጎሣን መሠረት ያደረጉ እና አንዳንዶቹ የተለያዩ መነሻዎችን መሠረት ያደረጉ ነበሩ። በአንድ ሣጥን ውስጥ መካተት ያልፈለጉት ሐረሬዎች ግራ ተጋብተው እንደ ሮቤርቶ፣ አባይ እና ሌሎች ያሉ የሐረር ተማሪ ፖለቲከኞች አሰባሰቡንና በአዲሶቹ የአርት ሕንጻዎች ውስጥ ተገናኘን፤ በዕለቱም በሮቤርቶ የተመራ የተጋጋለ ክርክር አደረግን።

አንዳንዶቹ ውይይቶች ያጠነጠኑት "ወደየመጣንባቸው አካባቢዎች ስንመለስ ምን ልናደርግ ይገባናል?" በሚሉ ማዕከላዊ ጥያቄዎች ላይ ሲሆን፣ ጥያቄው የተነሣው ከሐረር የመምህራን ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት እንደ ተመረቀ በክፍላተ-ሐገራት ለተወሰነ ዓመታት ካስተማረ በኋላ ዩኒቨርስቲ ገብቶ ያን ጊዜ 4ኛ ዓመት ተማሪ በነበረው ሙሉጌታ አበበ ነበር። እርሱ እና እርሱን የመሰሉት ከጥሩ የሕይወት ልምድ ጋር የነበሩ የበሰሉ ተማሪዎች ነበሩና ዩኒቨርስቲውን የተቀላቀሉት ግልጽ የሆነ የሥራ ሕይወታቸውን የሚያጠናክሩበትን ግብ ይዘው ተገኙ። ተራማጅ ተማሪዎቹ እነርሱን ያዩዋቸው የነበረው እንደ ወግ አጥባቂ የሥራ መስመር ፈላጊዎች አድርገው እስኪሆን ድረስ ብዙውን ጊዜ ከተማሪዎቹ እንቅስቃሴ ራቅ ብለው የሚገኙ ነበሩ። በዚያን ዘመን ተማሪዎች ትምህርት ለማቋረጥ ድምፅ ሲሰጡ ያንን ያደርጉ የነበረው በስሜታዊነት ግለት ስለ ነበር፣ አብዛኛውን ጊዜ ተግባራዊ የሆነውን 'ምን ይከተላል?'፣ 'ምንስ ይደረጋል?' የሚሉትን ጥያቄዎች በግልጽ አይወያዩበትም። እስከማስታውሰው ድረስ፣ ትምህርት የማቋረጡ ግብ ምንድን ነው? የሚለውን ማንም ቀደም ሲል ደፍሮ ያላነሣውን እውነተኛ እና ተግባራዊ ጥያቄ ያነሣ ሙሉጌታ ብቻ ነበር። እንደ ጀማሪ ተማሪም ሆነ እንደ ሁለተኛ ዓመት ተማሪ የነበረኝ ልምድ ዩኒቨርስቲውን ካቋረጥኩ በኋላ አብዛኛውን ጊዜ በአዲስ አበባ

ዙሪያ የምግብና የማረፊያ ችግሮችን ለመፍታት እንዘዋወርበት የነበረበት እና በሕይወት ለመቆየት የምንሞክራቸው መንገዶች ተስፋ አስቆራጭ ሲሆኑብን ደግሞ ወደ መጣንበት ከተሞች የምንመለስበት ነበረ። እኔ እና እንደ ታረቀኝ ያሉት ጓደኞቼ ርካሽ በነበረው ጮርናቄ ብስኩት እየቆየን ያልተለመዱ ሥራዎችን ስናፈላልግ አዲስ አበባ ዘመዶች የነበሯቸው እንደ አሌክስ ያሉትና ጥሩ የገንዘብ አቅም ከነበራቸው ቤተሰቦች የተገኙት ተማሪዎች እኛ የተሠቃየነውን ያክል ተሠቃይተው ላይሆን ይችላል። ነገር ግን የምናገኘው ለጥቂት ጊዜ ብቻ ይሆንና ከዚያም አብረውን ያሉት ተግዳሮቶች ወደድንም ጠላን ወደ ትውልድ ቀዬአችን እንድንመለስ ያደርጉን ነበር።

ከዚህ እይታ አኳያ፣ የሙሉ ጥያቄ ተገቢ ቢሆንም፣ ለሙሉ ጥያቄ ሮብ የመለሰው መልስ ግን፣ "ጥያቄህ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ምን ይሆናል ብሎ የመጠየቅ ያክል ተቀራራቢ ነው፤" የሚልና ከአድማጮች ጭብጨባን የተጎናጸፈ ሆነ። ነገር ግን እኔ በመልሱ ስላልተደሰትኩ ጥያቄው የበለጠ ሙሉ በሙሉ እንዲመለስ በምዘጋጅበት ቅጽበት ሙሉጌታም ጥያቄውን ሊከተል ፈልጎ ነገር ግን በጩኸቶች ምክንያት ዝም እንዲል ተገደደ። አጋጣሚው በፈጠረው በዚያ ትኩሳት ውስጥ ሳለን አድርገነው ይሁን ወይም አይሁን ትዝ ባይለኝም፣ አንዳንዶቹ የሐረሪ ተማሪዎች የተማሪ መታወቂያ ካርዶቻችንን እንድናቃጥልና ልክ ድልድይን እንደ ማቃጠል ተግባር ሠልፉን እንድንተወው ጥቆማ አቀረቡ። የትኛውም ነገር ሆኖ ቢሆን፣ የዩተጎ መፍትሔን ተግባራዊ ያደረግነው በዚያ መልኩ ነበር።

እያንዳንዱን ዝርዝር አፈጻጸሙን የማስታውሰው የ1966ቱ አብዮት ሲጠነሰስ እና ሲካሄድ አዲስ አበባ ነበርኩ። ብሩህ የታሪክ ተማሪ የነበረው አዲሱ የአብዮት ጓደኛዬ ጎንደሬው ሙላ ስመ ጥር የነበረው የኤኖ ሊትማን ትምህርት ክፍያ (ስኮላርሽፕ) በትምህርት ፋኩልቲ ውስጥ የተቀበለ ሲሆን፣ ባለቤቱ አደይ እና እኔ በራስ መኮንን ድልድልይ አቅራቢያ በተከራየነው ክፍል ውስጥ አብረን በርጫ ይዘን ስለ ሩሲያ አብዮት መጻሕፍትን እናነብብ ነበር። ሙሉ እና እኔ ስለ 1897ቱ የሩሲያ አብዮት ካነበብነው በመነሣት ስለ ኢትዮጵያ አብዮት ትንበያዎችን ስናደርግ የትኛውም ዓይነት ጠቅላላ አመራር ሳይኖረው በድንገተኝነት እየተጓዘ የነበረውን የኢትዮጵያን አብዮት አቅጣጫ እርግጠኞች ሳንሆንበት የሁለቱን አገራት ተመሳሳይ ሁኔታዎች እያወጣን እናመሳክር ነበር።





እንዲህ እያደረግን እያለን ወታደራዊው አገዛዝ ሥልጣን ሲይዝ አብዮታዊው ሠፈራ አሁን እንደ ተስፋፋ እና ስንታገለው የነበረው ሥርዐት አሁን ጥርስ አልባ አንበሳ እንደ ሆነ አስበን ተደነቅን። በአንድ ወቅት ከአራት ኪሎ ወደ ስድስት ኪሎ በሚወስደው ታዋቂ መንገድ ስሄድ የኢትዮጵያ አየር ኃይል እየተካሄደ ያለውን አብዮት በሚደግፍ መልኩ በራሪ ወረቀቶችን ሲበትን የምስራቹን የሚያበስረውን ወረቀት እያነሣሁ እያለሁ፣ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ በተራማጅ አቋሙ በጥሩ ይታወቅ የነበረውንና ከፖለቲካ ሳይንስ ዲፓርትመንት የሆነውን የአደሬ ጓደኛዬን ቡብሳን "ፊውዳሊዝም ሞተች" እያለ መሬቱን ተንበርክኮ ሲስም አየሁት። በፊቱ ላይ ይነበብ የነበረውን የሚንበለበል ፍንደቃ በጥራት አስታውሳለሁ። እንፈልገው የነበረው ለውጥ እየመጣ እንደ ነበረ፣ የተለየች ኢትዮጵያ በመነሣት ላይ እንደ ሆነች እና ጥንታዊው አገዛዝ ወድሞ አዲስ ዘመን በአድማሱ ላይ እየመጣ እንደ ሆነ ተሰምቶኝ የነበረ ቢሆንም፣ ምን ዓይነት እንደሚሆን ግን እርግጠኛ አልነበርኩም።

ከማስታውሳቸው ነገሮች ሌላኛው ስለ መጪው ጊዜ የአብዮት አቅጣጫ ሁሉም ዓይነት አቋም በነበራቸው ተራማጅ ተማሪዎች መካከል እየተካሄዱ የነበሩትን የተቀጣጠሉ ክርክሮች እና በእያንዳንዱ ንግግሩ ላይ "ለኅብረታችን ለዩተጎ እና ለተወካዩ ትግል" ማለት የማይደክመው ታዋቂው ተራማጅ መሌ ጋር የነበርኝ የበርጫ ጊዜ ናቸው። የሥነ-ሕይወት ተማሪውና የራሱ ገጸ-ባሕርይ የነበረው ሶል እና እኔ መቅደም ያለበት የመደብ ትግል ጉዳይ ወይስ የብሔራዊነት ትግል? እየተባባልን ስንወያይ፣ የሐረር ልጅ የሆነው ሶሎሞን የመደብ ትግል ቀዳሚ የአብዮት ጉዳይ እንደ ሆነ እና የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ከዚያ በታች የሚታይ እንደ ሆነ አጥብቆ ተከራከረ። ከትግራይ የሆነው ተማሪ መሊ አቋሜን ለመለየት ከባድ እስኪሆንብኝ ድረስ በሌላኛው አዙሪት ነገሩን ተከራከረበት። የውይይታችንን ከባድነት ያን ጊዜ ምን ያክል አገናዝበነው እንደ ነበር በእውነት ባላውቅም፣ አማካዩን አቋም ይዤ የነበርኩ ይመስለኛል።

ከአብዮቱም ቀደም ብሎ በ1966 ዓ.ም በጥናት ክበባችን ውስጥ ስለ ማርክሲዝም እና ሌኒንዝም የነበረኝን ተሳትፎ በተመለከተ ልገልጸው የሚገባኝ በጣም ጠቃሚ የሆነ ነገርም አለ። ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ ከተከ ጋር አገናኝ የነበረ ሲሆን፣ በደደር በነበርኩኝ ጊዜ ደብዳቤ ስንለዋወጥ ቆይተን ወደ አዲስ አበባ በምመጣ ገዜ በአብዮታዊ ሕይወቴ ላይ ትንሽ ልኮሳን ለመቀበል በአካል

አገኘዋለሁ። ከዩኒቨርስቲ ተመርቆ ለማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር እንደ ምጣኔ-ኃብት ባለሙያ ሆኖ በሚሠራበት ጊዜ ዎበራ በሚገኙ የኦሮሞ ገበሬዎች ላይ ኮስተር ያለ ምርምር እንዳደርግ ከምሪት ጋር መመሪያዎችን ሰጥቶኝ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። የተከን አካሄድ በሌሎች ሥራ የሚደገፍ ምሁራዊነት አድርጎ የወሰደው ሽሜ የቤት ሥራውን ባጋራሁት ጊዜ በሐሳቡ ላይ ያለማቋረጥ እየሳቀበት ተሰፋ አስቆረጠኝ። ይህ ዐይነቱ ልምምድ ንዑስ ከበርቴያዊ በጣም የወረደ አስተያየት ነው ብሎ ውድቅ በማድረግ ለገበሬዎቹ ማኅበራዊና ምጣኔ-ኃብታዊ ሐቆች እውነተኛ መደበኛ ጥናቶች ያለውን ጥላቻ አሳየ።

ወደ ዩኒቨርስቲ ከተመለስኩ በኋላ፣ ለበርጫ እና የሲጋራ የሚሆን ገንዘብ ይረዳኝ ከነበረው ከተካ ጋር የነበረኝን ግንኙነት እንደ ጠበቅሁ ቆየሁ። የሆነ ነጥብ ላይ የጥናት ክበብ እንዳደራጅ ሲጠየቀኝ እንደ ማዲ፣ አብዲ፣ ጋሹ፣ ኢሉ እና አሴ[19] ያሉ ጓደኞቼን አሰባሰብኩና ማርክሲሳዊ ሥነ-ጽሑፍን እንዴት ስልታዊ ሆነን እንደምናነብብ ምሪት ተሰጠን። ስለ ፖለቲካዊ ምጣኔ ኃብት እውቀት እንዲኖረን ከምንደረግበት ከአፋናሴቭ መጽሐፍ (የፖለቲካ ምጣኔ ኃብት ከሚለው) ጀምረን የቼ ጉቬራ ‹‹ጎሪላ ዋርፌር›› (የደፈጣ/ሽምቅ ውጊያ) በሚለው ላይ እናበቃለን። ማን እንደሚያድል እርግጠኛ ባልሆንም፣ የተዘጋጀው የሚነበብ ነገር በየዕለቱ ይታደልና ከዚያም የማንበብ እና የመወያየት ግሩም ጊዜያት ይኖሩናል። በእኔ በኩል ከባዱ ነገር ለውይይት በጊዜው ማድረስ የመቻል ሥርዐት የነበረኝ አለመሆኔ፣ አንዳንድ ጊዜ በአስቸጋሪ ሁኔታ ሰከሬ ክፍለ ጊዜውን አለመገኘቴ፣ በሌላ ጊዜ በከፊል ሰክሬ ቡድኑን ዘግይቼ መቀላቀሌ እና በተለይ ሥርዐት በነበረው እና ቀርቶ በማያውቀው በመኸዲ ሁልጊዜም መገሡጼ ነበር።[20] እንዴት ሥነ-ሥርዓት እንደምንይዝ የተዘጋጁ ነገሮችን ባናነባቸውም፣ በትክክል ትዝ የማይሉኝ ርእሶቹ "አብዮታዊ ሥነ-ሥርዓት" ወይም "አብዮታዊው ማን ነው?" የሚሉ ዓይነት እንደ ነበሩ አስታውሳለሁ። እነርሱም በሚኖረን መሰጠት ውስጥ እንድንቆይ የሚረዱን እና የሚያነሣሱን ቀስቃሽ ምክሮች ሆነው ያገለግላሉ። የዶላችነት አዝማሚያ ስለ ነበረው ለመኸዲ ግሣጼዎች ቦታ ከመስጠት ይልቅ በእውነት የራሴ አመለካከት ኖሮኝ የእርሱን ባሕርይ እንደ አስመሳይ ጨዋነት እሰይመው ነበር።[21] እርሱ የትኛውንም ሊባል የሚችለው ነገር ሁሉ ላይ በቀላሉ ተረድቶ በጥንቃቄ አጸፋ ማድረግ ይችላል።





ከየካቲት 1965 እስከ መስከረም 1966 ዓ.ም ድረስ ክስተቶች በፍጥነት እየጨመሩ ሄደው "ታዋቂው አብዮት" ከመጨረሻው የድራማ ፍጻሜ በፊት ወታደራዊው ኃይል ንጉሥ ኃይለ ሥላሴን በመገልበጥ ሥልጣን ሲይዝ በርካታ አጓጊ መቀየሶችን አደረገ። በዚያን ጊዜ ወደ ከተማዬ ጉርሱም ሄጄ ነበርና ዜናዎችን በራዲዮ እንከታተል ነበር። መስከረም 2 ላይ የንጉሡ መወገድ ሲነገር፣ ለኢትዮጵያ የአዲስ ዘመን ንጋት ጅማሬ ሆነ በማለት የእውነት ደስታ ተሰማኝ። በሚቀጥለው ማለዳ ከእኔው ከተማ የነበረውና ከጀኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት ጀምሮ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ አብሮኝ የተማረው ኢስማ ጋር ስንገናኝ ስሜቴን አካፈልኩትና እስክንኳሰስ ድረስ "የምታወራውን አታውቅም፤ ኃይለ ሥላሴ በዚህ መልኩ ሊወርድ የማይገባው ታላቅ የአፍሪካ መሪ ነው። በእርሱ አመራር ሥር ኢትዮጵያ ትልልቅ የሚባሉ ልማቶችን አይታለች፤" በማለት ገሠጸኝ። ምን ማለት እንደ ነበረብኝ ባለማወቅ ግራ ተጋብቼና ተወሳሰቡብኝ "የምርህን ነው? ከልብህ ነው የምታወራው?" ስል በቀላሉ ጠየቅሁት። ምላሹም፣ "አዎን፣ ከልቤ ነው፤" የሚል የጎላ ምላሽ ነበር።

ኢስማ በመንግሥት ላይ በጥቅሉ የሆነ ዓይነት ቅያሜ የነበረው የአካባቢው ሶማሌ እንደ መሆኑ በመንግሥት ለውጥ ላይ ይሄ ነው የሚባል ደስታ ሊታይበት ይገባል ብዬ ሳስብ ምላሹ ከጠበቅሁት ተቃራኒ ሆነ። ምናልባት እርሱ ሳይንሳዊ እውቀት የበለጠ የሚመጣው ከልምድ ነው ብሎ የሚያምን (ኢምፒሪሲስት)፣ ተጨባጭ ባልሆኑ ማብራሪያዎችን በሚሰጡ ወላዋይ ሐሳባዊ ጥናቶች ተጽዕኖ ሊደረግበት የማይችል ስለ ሆነ ሊሆን ይችላል። የእርሱ አካሄድ በእርሱ ዘመን ከነበሩት አብዛኞቹ እኩዮቹ ይልቅ በእጅጉ ሊገለጽ የማይችል ስለ ነበር እኔ እና ከጉርሱም የሆንነው ጓደኞቼ ጥሩ ያነበበ፣ የሚያስብ እና ብሩህ ተማሪ የነበረ እንደ መሆኑ ከፍተኛ አክብሮት ለእርሱ በመስጠት እነዚያን ንግግሮች ያለ ጥንቃቄ ዝም ብለን አንናገርም ነበር።

አንድ ወቅት ላይ ወታደራዊው ኃይል ራሱን በደርግ ምሥረታ የፖለቲካዊ ኃይል ኮርቻ ላይ አስቀመጠ። አዲሱ ደንብ ወደ ዩኒቨርስቲ እንድንመለስና ለብሔራዊ አገልግሎት ዘመቻ እንድንዘጋጅ፣ ለዚያ ካልተባበርን ግን የትምህርት እና የመቀጠር ሕዝባዊ መብቶቻችን ኮስታራ አደጋ ውስጥ እንደሚገቡ ከተሰጠ ማስጠንቀቂያ ጋር ወጣ። ጥሪውን ለማምለጥ ጀብደኝነት የሆነ የሞኝ ውሳኔ በመወሰን የምችለውን ሁሉ አደረግሁ። ይህንን ጉዳይ የበለጠ በዝርዝር ላቅርበው።

ወደ አዲስ አበባ መጣሁና የአክስቴ ልጅ ለነበረውና ያን ጊዜ ለብሔራዊ ቲያትር ይሠራ ለነበረው ጋሽ አበበ ወደ ቀደመው የማስተማር ሙያዬ መመለስ እንደምፈልግ ነገርኩት። በደደር የነበረኝን ሥራዬን ኦፊሲያላዊ ባልሆነ መልኩ መልቀቂያ ሳላስገባ ትቼ ነበርና አድራሻዬን አስመልክቶ መንግሥት ምንም ፍንጭ ስላልነበረው አንድ ዕቅድ አወጣን። ዕቅዱ ወደ ቡልጋ/ኢጥሳ መሄድና ተክለሃይማኖት ገዳምን ለማስተዳደር ኃላፊነት የነበራቸውን ቄሶች መላውን ዓመት በገዳሙ ውስጥ ምክር እና መንፈሳዊ ሕክምናን ከጤና ጋር በተያያዘ ጉዳይ ስቀበል እንደ ቆየሁ የሚገልጽ ደብዳቤ እንዲጽፉልኝ በመጠየቅ ለማማከር ነበር። የጠየቅነውን የሚመሰክር ደብዳቤ በማግኘቱ ላይ ስለ ተሳካልን ሠነዱን በእጄ ይዤ ለረጅም ጊዜ ሥራ ገበታዬ ላይ ያልተገኘሁበትን ምክንያት የሚያስረዳ በአእምሮዬ የፈጠርኩትን ታሪክ የሚገልጽ ማመልከቻ ለትምህርት ሚኒስቴር ጻፍኩኝ። በደብዳቤዬ ላይ ዩኒቨርስቲ እንደ ነበርኩ ሳልገልጽ ቀድሞ በነበረኝ የሥራ ገበታዬ ላይ መልሰው እንዲቀጥሩኝ ጠየቅሁ። ያንን ብገልጥ መላው ሁኔታ በአሳፋሪ አደጋ ላይ የሚጥል ይሆናል። ጥያቄዬ ውጣ ውረድ በሚያበዛ አሠራር ውስጥ ወደቀ፤ ደግሞም ሂደቱ ለወራት ተጓተተ። በዚህ ጊዜ *እብደት በኅብረት* ይባል የነበረውን በጣም ታዋቂ የነበረውን *የእድገት በኅብረት ዘመቻ* መንግሥት ጀምሮ ነበር።

*ዘመቻው* ሕዝቡን ለማስተማርና እየሆነ ያለውን ለውጥ ሊያስታውቃቸው ከዚያም በሂደት ቀጣይነት ባለው አብዮት ውስጥ እንዲሳተፉ ሊያስችላቸው መንግሥት የነደፈው መርሐ-ግብር ነበር። ይህ ዘመቻ ምናልባትም ተማሪዎች ራቅ ወዳሉ አካባቢዎች እንዲመደቡና ከዚህም የተነሣ በአዲሶቹ ገዢዎች ላይ የኅብረት ተቃውሞ ለማድረግ ዕድልን እንዳያጡ የታቀደም መርሐ-ግብር ሊሆን ይችላል። መንግሥት ከሁለተኛ ደረጃ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች አንሥቶ እስከ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ድረስ ሁሉም በዚህ መርሐ-ግብር ውስጥ መሳተፋቸውን ግዴታ ስላደረገው ሠራተኞችና የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም በዚህ ውስጥ መሳተፋቸው ግዴታ ሆነ።

እኔ እንደ ሰል፣ አዩ፣ ይልማ እና መስፍን የምላቸው እኔን እንደ አብዮት መሪያቸው ያዩኝ የነበሩ ጓደኞቼ ጋር በስድስት ኪሎ ስቀይ፣ በተከማይቱ ከመዞርና ለበርጫ ገንዘብ የሚሰጡንን አንዳች ዓይነት የመንግሥት ሥራ የነበራቸውን ጓደኞቻችንን ከማጥመድ በቀር ምንም የምንሠራው ነገር





አልነበረንም። እኛ ሐረሪዎች ለዚያ ዓይነቱ ተግባር ፋናና የሚል አስቂኝ የሆነ ስም ሰጥተነው የነበረ ሲሆን፣ ትርጉሙም ወረራ ወይም ለበርጫ በዓላችን የሚሆን ገንዘብን ማጥመድ እንደ ማለት ነበር። እንደ ጎረምሶች በፍቅር ሕይወታችን ውስጥ የነበረንን ፍንደቃ እና ውድቀቶች እየተወያየን ከቀትር በኋላ ያለውን ጊዜ በማንበብ እናሳልፋለን። አንዳንዴ አብሮን የሚሆነው እና የሕግ ትምህርት ቤት አብዮተኛ የነበረው አሴ በዚያን ጊዜ የትርፍ ሰዓት የሶስዮዎሎጂ (ማኅበረሰብ ጥናት) አስተማሪ የነበሩት ጋሽ ሽመልስ አዱኛ የተጣበቀውን የድህነት ሁኔታ በመገንዘብ ሥራ እንዲያገኝ ረድተውት በሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ ስለሚሠራ ለበርጫ በዓላችን የሚሆነውን ወጪ አንዳንድ ጊዜ ይሸፍንልናል። በምሽቶች ላይ ሁላችንም የመነን ትምህርት ቤት አጎራባች ወደ ሆኑት እንደ ደጃች የማም ጠጅ ቤት ያሉት መጠጥ ቤቶች እንሄድና በኦሮምኛ "ማቋረጥ" የሚል ትርጉም ባለው፣ ሐረሪ ውስጥ ጨብሲ ተብሎ በሚጠራው ሁኔታ ውስጥ ጊዜያችንን እናሳልፋለን። ሐረር ውስጥ ጫት ቅሞ ወደ መጠጥ ቤቶች በመሄድ ባለን ገንዘብ ልክ የጫቱን ማነቃቃት ኃይል ለማስተው መጠጣት የተለመደ ነገር ነው። አለዚያ አእምሯችን ንቁ ይሆንና መላውን ሌሊት መተኛት አንችልም። በዚያ ሁኔታ ውስጥ የበርጫ በዓል መናፍስት እነርሱን ባለማክበራችን እኛን የሚገሥጹበት ብዙ ጊዜ ዱካክ ተብሎ ይገለጽ የነበረው ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንገባለን።

ብዙውን ጊዜ ከጠጣን በኋላ እያንዳንዳችን ወደየገዛ መንገዳችን እንሄድና በሚቀጥለው ቀን የሌሊቱን ጀብዶቻችንን እያነሣን ስንሳሳቅ ከሁሉም በላይ እኔ ባህሉ የማይፈቅደውን አደርግና ተጨማሪ ማብራሪያ የማያስፈልገውን መረን የነበረውን የሌሊት ልምምዴን እነግራቸዋለሁ። እያንዳንዳችን በዘመቻ ጣቢያዎቻችን ተጠርተን ቀኖቻችን እስካነሡበት ጊዜ ድረስ ለወራት ያከል ያ ተደጋግሞ እናደርገው የነበረው ሕይወታችን ነበር።

## ዘመቻው

የወታደራዊው መንግሥት ሥልጣን መያዝ በተማሪዎች ዘንድ አከራካሪ ከነበሩ ጉዳዮች አንዱ ስለ ነበር፣ የዘመቻው ጉዳይ ተማሪዎችን በሁለት ከፍሎ አንዳንዶቹ ሊሳተፉ ሲፈልጉ ሌሎቹ በጥብቅ ተቃወሙት። ቆም ብሎ በቁም ነገር ለማሰብ ጊዜ እስኪጠፉ ድረስ ክስተቶች በፍጥነት መተካካት ይለዋወጡ

ጀመር። አንዳንዶች የጦር ሠራዊቱን በታዋቂው የተማሪዎች ረብሻ ውስጥ መሳተፍ አብዮቱን ወደ ፍጻሜው ለማምጣት እንደ ብርቱ ማባባሻ አድርገው ሲያዩት፣ ሌሎች ደግሞ በጣም ተጠራጣሪዎች ነበሩ። እኔን ጨምሮ አሁንም ሌሎች፣ ምናልባትም ብዙውን ቊጥር የያዝነው ምን እየተካሄደ እንደ ሆነ አላወቅንም፣ ጠንካራ አቋምም አልያዝንም። መንግሥት የአገሪቱ ገዢ የፖለቲካ ዘይቤ ኅብረተሰባዊነት (ሶሻሊዝም) እንደ ሆነ ሲያስታውቅና ወደ ጃል ሜዳ ሄደን የዘመቻውን መጀመር እንድናከብር ስንጠየቅ፣ የእኔን ጨምሮ የብዙዎቻችንን ልብ በመማረኩ ለክብረ-በዓሉ በመንግሥት የታደለንን ካኪ የደንብ ልብስ እና ባርኔጣ አድርገን ወደዚያው ሄድን። ሻለቃ መንግሥቱ ኃ/ማርያም፣ ሻለቃ ሲሳይ እና ሌሎች በጊዜያዊው መንግሥት በዘመኑ ታዋቂ መኮንኖች ኃይለ-ቃል የተሞላበትን ንግግሮቻቸውን አደረጉና አብዛኞቻችን "በትብብር መልማት" ስለተባለው መርሐ-ግብር የጋለ ስሜት ውስጥ የገባን መሰለን። ቀልብን የሚስበው ነገር በኅብረተሰባዊነት አዋጅ ውስጥ አዲሶቹ ደንቦች በጥሩ ሁኔታ ባለመቀመጣቸው ለማለት ያልታሰበውን ሌላ ነገር ለማለት ግልጽ ሳይሆን የተቀመጡ መሆናቸው ነበር። የቅርብ ጓደኞቼ እና እኔ በግድግዳ ላይ ጽሑፉን አለማንበባችን በግልጽ የሚያሳየው ምን ያክል ጥቂት መረጃ ብቻ ያለንና በጥሩ ያልተዘጋጀን እንደ ነበርን ነው።

መንግሥት ይፋዊ ማስታወቂያውን ከተናገረ በኋላ የዘመቻ ዝግጅቱ ጥቂት ጊዜ የወሰደ ቢሆንም፣ ለዘመቻው መርሐ-ግብር የትኛውም ይፋዊ ተቃውሞ ስለ መደረጉ ምንም አላስታውስም። የመርሐ-ግብሩ ይፋዊ ዋና መሥሪያ ቤት በምህንድስናው ፋከሊቲ ግቢ ውስጥ እንዲሆን ተደርጐ፣ ይመራ የነበረውም በሻለቃ ኪሮስ ነበር።[22] መርሐ-ግብሩ ከሞላ ጎደል ሁሉንም የአገሪቱ ክፍሎች ያካተተ በመሆኑ፣ በሁሉም ክልሎች ውስጥ በአንድ ጊዜ ሊጀመር ባለመቻሉ፣ የእያንዳንዱ ጣቢያ ዝግጅት እንደ ተጠናቀቀ ወደሚታወቁ ቦታዎች የሚላኩ ተማሪዎች ስም ዝርዝር በሬዲዮ ይነገራል። ምደባችን እንደ ተነገረ ወዲያውኑ ወደየተመደብንባቸው ጣቢያዎች ለመሄድ የጥድፊያ ዝግጅቶችን ማድረግ ይኖርብናል። የጥላዬ ጨዋቃን "እንዲያ እንዲያ ሲሉ፣ እንዲያ እንዲያ/ ጉሮ ወሸባዬ ጉሮ ወሸባ" የሚለው ዘፈን ከእያንዳንዱ የሬዲዮ መግለጫ በፊት ይመጣና፣ "መልካም ነው መልካም ነው ዘንድሮ" የሚለው ዘፈን ደግሞ ተከትሎ ይቀርባል። ለመሄድ የእኔ ተራ እንደ ሆነ የተነገረኝ በነሐሴ ወር ሲሆን፣





የተመደብኩት በጎንደር ክፍለ-አገር ቆላ ድባ በሚባል ሰፍራ ነበር። አዲስ አበባን ትተን የወጣንበትን ትክክለኛ ቀን ባላስታውስም፣ በርካታ የሕዝብ አውቶቡሶች ሁሉንም ተማሪዎች ወደየተመደቡባቸው የጎንደር ክፍለ-ሐገር አቅጣጫዎች እንዲያደርሱ መገደዳቸውን ግን አስታውሳለሁ። ጉዞው ሁለት ቀናትን የወሰደ ሲሆን፣ አንደኛውን ምሽት በፍኖተ ሰላም፣ ጎጃም ያደርን ይመስለኛል። ተመሳሳይ አመለካከት የነበረን ተሳታፊዎች አንዳችን ሌላችንን አውቀን ከሠፈራው በመውጣት መጠጥ ለመጠጣት ከከተማው ስንወጣ የአካባቢውን ቢራ መሸጫ ቤቶች አፈላልገን ዳግም የተባለውን የአካባቢውን አረቄ አገኘን፣ ሲጋራዎችንም አጨስን። ለወደፊቱ እንድጠቀምባቸው ከኒያላ ጀምሮ እስከምወደው ሮዝማን ድረስ ፓኮዎችን ገዛሁ። አንዳንዶቹ ተማሪዎች ወጣት ተማሪዎችን ለማኅበራዊው ዐመፅ አዲስ አበባ ውስጥ በማነሣሣታቸው ይታወቁ ከነበሩበት የኢጋዚ ትምህርት ቤት የመጡ ሲሆኑ፣ ሜዳ ላይ ተቀምጠን እያጨስን እያለ አንደኛው ወደ እኔ በመምጣት 'ትገናኛለህ?' ሲል ጠየቀኝ። ያን ጊዜ ሐሺሽ ለማለት እንጠቀምበት የነበረውን ቃል መጠቀሙ ነበር። በአካባቢው በርካሽ ዋጋ የሚዘጋጀውን ከተለያየ ሲጋራ ተዘጋጅቶ በጉሬዛ የተጠቀለለውን ነገር እያጨሰ ነበር። ቀጫጫው ሰውነቱ፣ አፍሮ ጸጉሬ፣ እና ሞገደኛ አቋሜ ምናልባት የእውነትም ደጋግሜ ሐሺሽ የምወስድ እንዲመስለው አድርገውታል። እርሱ የወተወተኝ ቢሆንም እንኳን፣ እንደዚያ ያለውን ነገር እንደማልወስድ በቀጥታና ደጋግሜ ነገርኩት።

በሚቀጥለው ቀን ጎንደር ስንደርስ የጎንደር እና አካባቢዋ ነዋሪዎች ገበሬዎቹን ጨምሮ እየጠበቁን ነበረና በዘፈን ተቀበሉን። ገበሬዎቹ ሲዘፍኑት የሰማሁት አንደኛው ዘፈን እንዲህ ይል ነበር፡ 'ምናለ ደርጉ ምናለ፣ ሐገሬን ለሰው፣ ሐገሬን ለሰው አልሰጥም አለ፤' የሚል ሲሆን፣ ከአውቶቡሱ ወርደን ሰዎቹን ለማጀብ ዕድል አገኘን። ጉጉ የነበርኩ በመሆኔ፣ እየተጓዙ ከነበሩት ገበሬዎች አንደኛውን "ደርግ ማን ነው?" ብዬ ስጠይቀው፣ መጀመሪያ ላይ መልሱ ራሱን የጠበቀበት 'እኔ እንጃ' የሚል ሆነ። ነገር ግን ሜን ብዬ ስጠይቀው፣ ‹‹ጃንሆይን የተካው ነዋ›› ሲል ስለ መለሰልኝ፣ ደርግ ማለት ከኃይለ ሥላሴ በኋላ እንደ ተተኪ ሆኖ የመጣ ሰው አድርጎ ገበሬው እንደ ተረዳው ለራሴ ግንዛቤ ወሰድኩ። በአእምሮዬ ውስጥ አጠይቅ የነበረው የኃይለ

ሥላሴ መውደቅ በገበሬዎቹ ዘንድ፣ በተለይም ደግሞ "ፀሐዩ ንጉሥ ለዘላለም ይገዛል" የሚል እምነት በነበራቸው "የሰለሞን ስርወ-መንግሥት" የበለጠ ስሜት በማጭርባቸው በሰሜኑ ዘንድ እንዴት ነበር ተቀባይነት የነበረው የሚለወን ለማወቅ ነበር። ንጉሡ ይታዩ የነበረው እንደማይበገሩና ዘላለማዊ ተደርገው ስለ ነበር፣ "ንጉሥ አይከሰስም ሰማይ አይታረስም" የሚለው አነጋገር የታወቀ አነጋገር ነበር።[23]

አነስተኛ በነበረችው ውብ የቆላ ድባ ከተማ ደርሰን በጤና ክሊኒክ ግቢ ውስጥ አሥራ ሁለት ተማሪዎችን በሚይዝ አንድ ክፍል ገብተን እንድናርፍ ተደረገ። ለእያንዳንዳችን አንዳንድ ትናንሽ ፍራሽ እና ብርድ ልብስ ተሰጠን እንጂ፣ አልጋ በጭራሽ ባለመኖሩ እንዲሁ ወለሉ ላይ መተኛት ነበረብን። ከእኛ ጋር ቆላ ድባ የተመደቡ አንዳንድ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሲኖሩ፣ ሌሎች የመጡት ከአስፋው ወሰን፣ ከመነን፣ ከአጋዚ እና የተለያዩ የጎንደር ክልል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነበር።

አንድ ቡድን የምንሆነው በሕንጻው ጥግ ካሉት ክፍሎች ጨዋታ አዋቂ የሆነው የድሬዳዋ ልጅ ዴቭ እና የቅርብ ጓደኛው ባሉበት በአንደኛው ክፍል እንድንሆን ተመደብን። እርሱ እንደ ብዙዎቻችን የተራማጅነት አዝማሚያ በግልጽ የሚያሳይ ሰው አልነበረም፤ እንዲያም ሆኖ በቀሩት ዘንድ እንደ አብዮተኛ የሚቈጠር ነበር። ሊመጡ ላሉት ዓመታት ሁሉ የዘለቀ ጓደኝነት ያቆምኩለት ከዩኒቨርስቲው መምህራን ማሠልጠኛ (ቲቲአ.) መርሐ-ግብር የመጣው ሌላኛው ወዳጃችን ጥሌ አብሮን ተገኝቷል።

አንዴ ከተደላደልን በኋላ፣ የአካባቢው ምግብ ቤቶች፣ መጠጥ ቤቶችና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮች የሚገኙባቸው ቦታዎች የት እንደ ሆኑ ማወቅ ጊዜም አልወሰደብንም። ዘመቻው በጥሩ ሁኔታ አልተቀናጀም ነበርና ቢራ፣ ጠጅ እና ዳጉሳ ጠላ ከመጠጣት ደግሞም ከማጨስ ውጪ ምንም የማናደርግበት የሥራ መፍታት



እኔና ጓደኞቼ በወጣትነት ዘመን





ቀናት በርካታ ነበሩ። የወጣትነት እና ያሰኘን የምናደርግበት እድሜያችን የጠየቃቸውን ሌሎች ነገሮች አድርገናል። አብዮተኞች የነበርነው ከእኛ ጋር በተመሳሳይ መናበብ ውስጥ የነበሩትን ከፖለቲካዊ እውቀታችን ደረጃ አኳያ በአንድ ላይ ማሰባሰብ እንዳለብን አስተዋልን። ተማሪዎቹ ቅይጥ የሆነ ስብዕናዎችን ከተለያዩ የመገኛ ዳራዎችና ጽንፈ-ዓለም አተያዮች ጋር ያሉ ነበሩ። ከአዲስ አበባ የሆኑት ተማሪዎች፣ በተለይም ከአጋዚ ትምህርት ቤት የመጡት የሚታወቅ ባሕሪ የሌላቸው አፈንጋጮች ሲሆኑ፣ ከባለጠጋ ቤተሰብ የመጣው ሮም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ዩላ ብለን እንጠራው የነበረውና ከአስፋው ወሰን ትምህርት ቤት የመጣው አስፋው ኋላ ላይ የእኔ ደቀ መዝሙር የሆነ ብረት አንሺ ስፖርተኛ ነበር። ከአዲስ አበባ የመጣነው ከጎንደር፣ በተለይም ከገጠራማ ክልሎች የመጡትን በአንዳች መልኩ ያነሰ ሥልጣኔና ያነሰ ዘመናዊነት ያላቸው አድርገን ማየታችን አልቀረም። ባልተመጣጠነ መልኩ፣ ከአዲስ አበባ እና የጎንደር አካባቢዎች የመጡ ልጃገረዶችም ስለ ነበሩ የዚያን አንድምታ ልትገምቱ ትችላላችሁ።

ዴቭ እና እኔ በአጎራባቾቻችን ዘንድ አካባቢውን እንደ ማጽዳት እና ጉድጓድ እንደ መቆፈር ዓይነት አንዳንድ ሥራዎችን በጋራ ልንሠራ ተመድበን፣ ገኒ እና የኒ የተባሉ ልጃገረዶችን ማማለልና ኋላ ላይ በፍቅር አብረን ማሳለፍ ጀመርን። ያ ዓለም ትንሽ ነበርና በተለይ ልጃገረዶቹ ከመጡበት ከአስፋ ወሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመጡት ዘንድ ያለን ግንኙነት ብዙም ሳይቆይ ታወቀብን። አንድ ቀን ለእረፍትና ለመዝናናት ወደ ጎንደር ለመሄድ ከሁለቱ ልጃገረዶች ጋር በምሥጢር እንገናኝ ዘንድ ዕቅድ አወጣን። ነገር ግን ሳይነቃባቸው የሚከተሉን ሌሎች ተማሪዎች ስለ ነበሩ፣ ከሚከተሉን ጋር አላስፈላጊ የሆኑ የግጭት ስጋቶችን ለማስወገድ ስንል ሁለቱን ልጃገረዶች ማግኘቱን ተውነው። ዕቅዳችን ሲከሽፍብን፣ ያለችኝን አነስተኛ ገንዘብ አምስቴል ቢራ በመጠጣት ወደ ጨረስኩበት ወደ ቋራ ሆቴል ከሄድኩ በኋላ፣ ዴቭ እና እኔ ተገናኝተን ሌሊቱን በመስፍን መኖሪያ አሳለፍን። መስፍን የዴቭ እና የእኔ የጋራ ጓደኛችን ሲሆን፣ ሲበዛ ደግ ሰው እና በጎንደር ያለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተወካይ የሆነ የድሬዳዋ ልጅ ነው። የሳምንቱን ማብቂያ በጎንደር አሳልፈን በምሽት ወደ ቆላ ድባ ጣቢያችን ተመለስን።

ወደ ክፍላችን ደክሞን ገብተን ለመተኛት በፍራሻችን ላይ ጋደም እንዳልን፣

ተከታታይ የጩኸት ድምፆችን ሰማን። በዴቭ እና እኔ ላይ የአሰፋ ወሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ያቀጣጠሉት ፀመፅ ይሆን እንደ ሆነ አላወቅንም ነበር። ከትምህርት ቤታቸው የመጡ ልጃገረዶችን በማሽኮርመም ያላቸውን ሥልጣን ለመጠቀም የሞከሩ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እንዳሉ ሲናገሩ ሰማናቸው። የመደብ ጦርነት የሚካሄድ ይመስል ይህ ሊታገሡት የማይገባ ጉዳይ እንደ ሆነ ሲናገሩ፣ ግልጽ የሆነው ነገር ዴቭ እና እኔ ዒላማ ውስጥ እንደ ገባን ነበር። የደወል መሪዋ ከአንደኛዋ ልጃገረድ ጋር ግንኙነት የነበራት ዓለም በመሆኗ ወጣንና ወደ ጎንደር የሄድነው የሁለታችንንም ጓደኛ ለማየት እንደ ነበርና ልጃገረዶቹም በዛው አውቶቡስ አብረውን የሄዱት በአጋጣሚ እንደ ነበር እንጂ፣ ሆን ብለን እንዳልሆነ ተናገርን። በእርግጥ ይህ ውሸት ሲሆን፣ የጣቢያው መኮንን ከጎንደር የሆነው ተራማጅ መምህር ሰሎሞን በመሃከል ጣልቃ ገብቶ ማዕበሉን ጸጥ አሰኘው።[24]

በመካከላችን የፖለቲካ ንቃተ ሕሊና ደረጃ ልክ ልዩነቶች እንዳሉ በመገንዘብ ራሳችንን አብዮተኞች ብለን የለየነው ወዲያውኑ በገዛ ራሳችን የመረጥነው ምሽት ላይ ሥራውን ለማካሄድ ኃላፊነት የተሰጠውን መኮንን ፈቃድ አንዳንዴ እያገኘን ማርክሲዝምን የምናስፋፋበት ዝግጅት ጀመርን። በማርክስ እና ኤንግልስ ሥራዎች ላይ በመመሥረት *ሳይንቲፊክ ሶሻሊዝምን* ማስተማር ስንጀምር፣ ቀደም ሲል አንብቤያቸው የነበሩት ሰፋ ያሉ የማርክሲዝም መጻሕፍት ከዚህ አኳያ የመሪነቱን ሚና ለመጫወት ቦታ እንዳገኝ አደረጉኝ። አንድ ጊዜ በ"ሳይንቲፊክ" ሶሻሊዝም እና በ"ዩቶፒያን" ሶሻሊዝም መካከል ያለውን ልዩነት አስረዳ ነበርና ስለ ሁለተኛው አሉታዊ የሆነ ነገር ተናገርኩ። በዚያን ሌሊት ይቆጣጠረን የነበረው የፖሊስ መኮንን ቆሞ ጸረ-ኢትዮጵያዊ ነህ ሲል ከሰሰኝ። "ዩቶፒያን" የሚለው ቃል "ኢትዮጵያ" ከሚለው ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም፣ "ዩቶፒያን" የሚለው ቃል ትርጉም ሌላ እንደ ሆነ በማስረዳት ግልጽ ካደረግሁ በኋላ፣ በሳይንቲፊክ ሶሻሊዝም ላይ ስብከቴን ቀጠልኩ። ምን ያክል ድልብ አላዋቂ መሆኑን የሚያሳይልኝ ስለ ሆነ ያንን ርእስ በማንሣቴ ብደሰትም፣ እርሱ ግን ባላዋቂነቱ ፈጽሞ አላፈረም ነበር።

ከአጋዚ ትምህርት ቤት እና ከጎንደር ገበሬዎች ዘንድ የመጡት ተማሪዎችን መቀየር አስቸጋሪ ቢሆንም፣ በርከት ያሉ ሊባል የሚችል ተማሪዎችን ወደ ማርክሲሳዊ ሰርጥ ማምጣት በመቻላችን በተልዕኳችን ላይ ስኬታማዎች





ነበርን። ለፊተኞቹ ተማሪዎች አብዮቱ የሚጠይቀውን "የድርጊት መመሪያ" ያለው ሕይወት መምራት ከባድ ነበር። ለኋለኞቹ ማርክሲዝም እንደ እኔ ባሉ ወጣት ተራማጆች ዲያሌክቲካል ማርክሲዝም ንድፈ-ሐሳብ ይሰብኩላቸው ስለ ነበር ለዓመታት ያምኑበት የነበረውን እግዚአብሔርን መካድ ከባድ ነበር። ይሁን እንጂ፣ እነዚያ ዓይነቶቹ አንድ ጊዜ ከተለወጡ ቀናተኛ ተራማጆች ይሆናሉ። ከሁለቱም ቡድኖች የተሰጡ ማርክሲስቶችን በማፍራቱ ረገድ የተሳካልኝ ስሆን፣ ለዚህ ምሳሌ ሆነው የሚቀርቡት እንደ በሽር፣ ወንዴ እና አሰፋው ያሉት የእኔ ደቀ መዛሙርት የሆኑት ወጣቶች ናቸው። እዚህ ጋ መስተዋል ያለበት በርካታ በሌኒንና ማዎ የተጻፉ እንዲሁም እንደ አሌክሳንደር ሶልዘኒጺን ባሉ ጸሐፊዎች የተጻፉ በአብዛኛው ተቃራኒ የሆኑ ልብወለድ መጻሕፍትን ከእኔ ጋር የነበሩ መሆኑ ነው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተማሪዎቹ ራሳቸውን አደራጅተው የገጠራማውን አካባቢ ሕዝብ ለመርዳት አንዳንድ ዝግጅቶችን አደረጉ። መጻፍና ማንበብን በምናስፋፋባቸው እና በተማሪዎቹ እንቅስቃሴ "ኋላ ቀር ወይም የተጨቆኑ ሕዝቦች" ተደርገው የተፈረጁትን ሕዝብ የፖለቲካ ትምህርት በምናስተምርባቸው ተግባራት ውስጥ መሳተፍ ጀመርን። እንደ አብዮተኛ ምሳሌ መሆን እፈልግ ነበርና በዚህ ላይ በርትቼ ለመሥራት ስለ ወሰንኩ፣ በሳምንቱ ቀናት ውስጥ ለሰዓታት ወደ ገጠራማ መንደሮች ተጉዘን በዚያ ላሉት የአማርኛ ፊደላትን እናስተምራቸዋለን። ከስንት ጊዜ አንድ ጊዜ ሕዘቡን ወደ ገዳም አካባቢ እና ወደ ቤተ ክርስቲያናት አሰባስበን ንቃተ ሕሊናቸውን ለማነቃቃት የፖለቲካ ትምህርት እንሰጣቸዋለን። በአብዛኛው ንግግሮቼ የሚያጠነጥኑት የመደብ ልዩነት ይባል በነበረው በኃላፊው የብዝበዛ ሥርዓት ላይ እና አግባብ ያልነበረው የመሬት ክፍፍል ላይ ሲሆን፣ ጅማሬ ላይ 'ባላባት ይውደም፣ ይውደም' እያልን ተገቢ ያልሆኑ መፈክሮችን እናሰማ ነበር። መፈክሩም ተገቢ ያልነበረው ደቡብ ላይ የሚሠራው "ባላባት" የሚለው ቃል የመሬት ክፍፍሉ የተለየ በሆነበት ሰሜን ላይ ባለው ባህል ውስጥ ምንም ትርጉም የሌለው በመሆኑ ነበር።

የገዛ ራሳችንን የምግብ ኮሚቴ አቋቁመን በጥሩ ሁኔታ እንመገብ ስለ ነበር፣ እንዲሁም ለእያንዳንዳችን ወደ 40 ብር ገደማ ያክል ገንዘብ መንግሥት መድቦልን ስለ ነበር፣ በዘመቻ ጣቢያው ውስጥ የነበረው ሕይወት መጥፎ

አልነበረም። የምግብ ኮሚቴው በበቂ ሁኔታ የምንመገብ መሆናችንን ብቻ ሳይሆን፣ የሚከታተለው በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ላይ ለምግቡ የተሠፈረው ባጀት ሲተርፍ ለሁላችንም መከፋፈሉን ጭምር ነበር። ተማሪዎቹ ያችን ከተማ ተቆጣጥረዋት በሰከሩ ታዳጊዎች የተፈጠሩትን ሁሉንም ዓይነት ድራማ ተሞልታ ስለ ነበር በዚያ ሌሊት መላው ቆላ ድባ በእሳት የተያያዘች ያክል ሁከት ሆነ።

መንግሥት በመስከረም 1968 ዓ.ም ላይ የመሬት አዋጅ ሲያወጣ ለእያንዳንዱ ዘመቻ ጣቢያ አንዳንድ የተማሪ ተወካይ ወደ አዲስ አበባ እንዲልኩ ብዛት ያለው ደብዳቤ ተሰራጨ። ተወካዩ አዲስ አበባ ውስጥ በሚካሄደው ዐውደ-ጥናት ርእሰ-ጉዳዩ ላይ ገለጻ ይሰጠውና በተራው የቀሩትን ተማሪዎች ያስተምራል። ማስታወቂያው የመጣው በአጭር ጊዜ ውስጥ ስለ ሆነ፣ የተማሪዎቹ ተወካይ በጣም በፍጥነት መመረጥ ነበረበት። አስቸኳይ ስብሰባ እንዳለ አንድ ሰው በሚነግረን ጊዜ ጥቂት ጓደኞቼ እና እኔ በአካባቢው መጠጥ ቤት ውስጥ ጠጅ እየጠጣን ነበር። ኃላፊነት የተሰጠው መኮንን ሁላችንንም ከሰበሰበን በኋላ ለዐውደ-ጥናቱ ወደ አዲስ አበባ የሚሄድ አንድ ሰው እንድንመርጥ ተነገረን እኔ እና በርካታ ለውድድሩ የታጩት ተማሪዎች ለመመረጥ ብለን ተራ በተራ ንግግሮችን አደረግን። ድምፅ በሚቆጠር ጊዜ አስደናቂ በሆነ የብዙኃን ድምፅ እኔ ምርጫውን እንዳሸንፍኩ ይፋ ሲደረግ፣ የተመረጥኩት ከሴት ታዳሚዎች በመጡት በርካታ ድምፆች ስለ ሆነ፣ እኔ በመመረጤ አንዳንድ ተማሪዎች ቅሬታ እንዳሰሙ ቆየት ብሎ ወሬ ደረሰኝ።[25]

ወደ አዲስ አበባ መሄዱ በትንሽ ከተማ ውስጥ ከነበረው አሰልቺ የዘመቻ ሕይወት የሚገላግል ግሩም እረፍት እንደ ሆነ እያሰብኩኝ አዲስ አበባ እንደ ደረስኩ፣ አምስት ኪሎ ባለው የምሕንድስና ፋክሊቲ ወዲያውኑ አሳወቅሁ። የሚያስደንቀው ነገር ከእያንዳንዱ ጣቢያ ተወክለው የመጡት እንደ እቦ ያሉ የማርክሲስት ተራማጆች የነበሩ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መሆናቸውን ማየቴ ነበር። መጀመሪያ ላይ ስለ ተልዕኮው እና ከፊታችን ስላለው ተግባር አጭር ገለጻ ሲሰጠን፣ መድረኩን የዘመቻ ሕይወት ላይ ስላሉ መሠረታዊ ጉዳዮች እንዲሁም በጥቅሉ በመርሐ-ግብሩ ላይ ስላሉት ነገሮች በማንሣት ኮስታራ ወደ ሆነ ውይይት ልንቀይረው ፈለግን። እንዲሁም ደግሞ የምንወክላቸው ተማሪዎች በገጠራማው ክልል እየገጠማቸው ያለውን ተግዳሮቶች እንድናቀርብላቸው ኃላፊነቶችን ሰጥተውን የነበረ ቢሆንም፣ ያንን መስመር መከተል ሳንችል ቀርተን





ስብሰባው ላይ ኃላፊነት ለነበራቸው የመንግሥት መኮንኖች ጫና እጅ ሰጠን። የተለያዩ ተናጋሪዎች በመሬት አዋጁ ባሕርይ ላይ እና ያንን በማስፈጸሙ ሂደት ላይ የተማሪዎችን ሚና በተመለከተ ንግግሮችን አቀረቡ።

ከልምምዱ የምማረው አዲስ ነገር ይኖር እንደ ሆን እኔ በግሌ ምንም የተሰማኝ ነገር አልነበረም። አብዛኞቹ ተሳታፊዎች፣ በመሬት አዋጅ ላይ ድጋፍ ያላቸው ቢሆኑም፣ በርካታ ያልተመለሱ ጥያቄዎች ነበሯቸው። አንዳንዶቹ እንደውም ይህ መንግሥት የሕዝባዊ መንግሥት ምርጫ ባልተካሄደበት ሕጎችን ለማውጣት ሕጋዊ ይሆናል ወይ የሚል ጥያቄ ቢያነሡም የተቀናጀ ምላሾችን ባለማግኘታችን፣ በዐውደ-ጥናቱ ሂደት ውስጥ ዝም ብለን አለፍንና ዐውደ-ጥናቱ ሲጠናቀቅ ወደየመጣንበት ጣቢያ ተመለስን።

አዲስ አበባ ስሆን የማከናውናቸው በእኔ የዘመቻ ጣቢያ ውስጥ ከነበሩ በርካታ ተማሪዎች የተሰጡኝ የቤት ሥራዎች ነበሩኝ። ደብዳቤዎች ያመጣሁላቸውን ቤተሰቦች ለማግኘት የምችለውን ሁሉ በማደርግበት ጥረት ውስጥ የገኒን አባት ጨምሮ የኅበኘኋቸው ወላጆች ለልጆቻቸው በታማኝነት ያደረስኳቸውን ጥቂት ምግብ እና ገንዘብ ሰጡኝ። ለራሴ ጥቂት ገንዘብ የሰጠኝን አሠልጣኜን ተከንም ማግኘቴ ሳያንስ፣ ከጉሬዛና ኒያላ ጀምሮ ሮዝማንስ እና ዊንስተን ሲጋራዎችን ካመጣሁላቸው ጓደኞቼ ጥቂት ገንዘቦችን ሰበሰብኩ። ለተጨማሪ ንባብ የሚሆኑኝን አንዳንድ አዳዲስ የማርክሲስት መጻሕፍትንም አመጣሁ። በቆላ ድባ ሞቅ ያለ አቀባበል ተደረገልኝና ከቅርብ ጓደኞቼ ከዴቭና ጥሌ ጋር ገንዘቦችን በፍጥነት እስከታልቅ ድረስ ለጥቂት ቀናት በአብዛኛው ቢራ እየጠጣን ስንደሰት ቆየን። ከዚያ በኋላ መደበኛ ወደ ሆነው የዳጉሳ ጠላችን ፍጆታ ተዘዋወርን።

የዘመቻው ለሁለት ዓመታት መራዘም፣ በጊዜው እየተገለጡ የነበሩት የበርካታ ያልተፈቱ ችግሮች መኖር (አንዳንዶቹ አስተዳደራዊ፣ ሌሎቹ የመሬት አዋጁን ለማስፈጸም ባለው ሂደት ውስጥ የገጠሙ የተወሳሰቡ ሁኔታዎች ዓይነት ሙያዊ ነገሮች)፣ በዘመቻ መርሐ-ግብሩ ውስጥ ባሉት ተማሪዎች ዘንድ ያልተረጋጉ ልምምዶችን ፈጠሩ። የጥንታዊውን አገዛዝ ያክል ያረጁትን እና ከአብዮቱ ጋር ወደ ፊት ለመሄድ ቅናት ከሌላቸው በአካባቢው ካሉት የመንግሥት ሠራተኞች ዘንድ ድጋፍ በማጣታችን ሲበዛ ተስፋ ቆረጥን። የተለየ ነገር መጠበቃችን በራሱ የዋህነት ነበር በሚያስብል መልኩ የአሮጌው ሥርዓት

አካል በመሆናቸው ሌላ ምን ሊሆኑና ሊፈይዱ ይችላሉ? የሚል ጥያቄ ተነሣ።

ገበሬዎችን መጻፍና ማንበብ የማስተማር ዘመቻ እና ቅስቀሳ ያለበት ሕሊናቸውን የማንቃቱ/የማስተማሩ ሂደት በከፍተኛ ፍጥነት እየተካሄደ ሲቀጥል፣ በየትኛውም ዓይነት እንደ ውኃ ጉድጓድ መቆፈር እና አንዳንድ የፍሳሽ ውጥን-ሥራዎች የምንሠራባቸው አካላዊ እገዛዎች ይልቅ መላው ጥረታችን በፖለቲካዊ ትምህርት ላይ ትኩረት አድርጎ ነበር። አንዳንዶቹ የአካባቢው ሰዎች አካሄዳችንን ሲወዱት ሌሎች ደግሞ ነገሮችን ያን ጊዜ የምናይበትን ከእኛ ጋር የሚንቀሳቀሰውን በማየት ጥርጣሬዎች የነበሯቸው፣ ደግሞም ጥላቻቸውንና ተቃውሟቸውን የገለጡም ስለ ነበሩ፣ ሂደቱ ቅይጥ ውጤቶችን አስገኘ። ለኋለኛው ቡድን አስተያየት የበለጠ ተራማጅ የሆነውን የአምባጓሮኝነታችንን አመለካከት በከፊል አዘጋጅተን የትብብር ግብርና ጥረቶች ሐሳብ ላይ ብዙ ጥረቶች በማድረግ ገፋንበት። አብዛኞቻችን ከገበሬ ቤተሰብ የተገኘን ባለመሆናችን፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ከመጽሐፍ የተገኘ እውቀት ብቻ ነበር የነበረን። የትብብር እርምጃዎች በገበሬዎቹ ምርጥ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ለማስረዳት ብዙ የጣርን ቢሆንም፣ ፈጽሞ አዲስ ተሞክሮ በመሆኑ ዝግጁ ሆነው ያስተናግዱት ዘንድ ለእነርሱ በጣም ከበዳቸው። በተቃውሟቸው እጅግ የደነዙ አንዳንዶች በመኖራቸው፣ ‘እያ ጥበበ በቀደም በደብራችን ያደረጉት ንግግር ጥሩ ነበር ብቻ…’ ይሉን ነበር። ነገሮችን ከእነርሱ እይታ ስላላየናቸው የዋኾች ነበርን። የትብብር ግብርናውን አጀንዳ በገፋንበት ቁጥር፣ በተለይ ከወጣቶቹ እና የአካባቢውን ወይም የትውፊታዊውን የፈረሰኛ እና የጎበዝ አልጋ የተሰኙትን ስፍራዎች ከሚወዱት የበቁ ገበሬዎች ዘንድ የበለጠ ተቃውሞ ይደርሰን ነበር።[26]

እነርሱን ለማገልገል እንቀበላቸው የነበሩትን መሥዋዕትነቶች ከገዛ ራሳችን ሕይወት ሊያዩት ይችሉ ነበር ብለን እስከናምን ድረስ የገበሬዎቹን ዕጣ ፈንታ ለማሻሻል በጣም የተሰጠን እንደ ነበርን ምንም ጥርጥር አልነበረውም። ከዚህ አንጻር እኔ እና ጓደኞቼ ፍላጎታቸውን በመጠበቅ ሕይወታችንን ለአደጋ ያጋለጥንባቸው ጊዜያት ነበሩ። እስኪ የሚያስደምም የሆነ መረጃ በማድረግ አንዱን አጋጣሚ ላያይዘው።

በአንድ በርከት ያለ የቀንድ ከብቶች በነበሩት ገበሬ ቤት ውስጥ ሌሊቱን ያሳለፍንበትን አንዱን ምዕራፍ አስታውሳለሁ። በዚያ ሌሊት ሽፍታ ተብለው





በአካባቢው የሚታወቁ የታጠቁ ዘራፊዎች የቀንድ ከብቶቹን ለመውሰድ መጡ። ስለዚህ ነገር ባወቅን ጊዜ፣ በእኛ ዙሪያ ያሉትን፣ ማለትም መስተንግዶ የተቀበሉንን እና እኛን ለመጎብኘት የመጡትን እንግዶች በየትኛውም መንገድ ሽፍቶቹን እንዲከተሉ፣ አስፈላጊም ከሆነ የጦር መሣሪያዎቻቸውን እንዲጠቀሙ በመንገር ለአንዳች እርምጃ አሰባሰበናቸው፣ ደግሞም ከእኛ ጋር እንዲሠለፉ አዘዝናቸው። መሣሪያዎቻቸውን ተሸክመው እንደ ወጣን እኔ እና ከእኔ ጋር የነበሩ የተወሰኑ ተማሪዎች ወደ ፊት ተሰለፉ። ሽፍቶቹ ከካኪ ደንብ ልብሶቻችን ጋር ሲያዩን እነርሱን ለማጥመድ ወደ መንደሪቱ የመጣን የተለዩ የመንግሥት ኃይሎች የሆንን መስሏቸው በፍጥነት መሮጥ ሲጀምሩ፣ ከእይታችን እስኪሰወሩ ድረስ ለብዙ ርቀት ያክል ተከተልናቸው። በዚህ አደጋ የሞላው ልምምድ መጨረሻ ላይ፣ ስብሰባ ጠርተን ከእኛ ጋር ሙጥሙጥ ጓንዴ ዓይነት ጠብመንጃ ተሸክመው የነበሩትን ገበሬዎች መሣሪያዎቻቸውን በሽፍታዎቹ ላይ ያልተኮሱበትን ምክንያት ስንጠየቃቸው፣ "እናንተ ልትመሩን ይገባል። መመሪያዎችን ከእናንተ ልናገኝ ይገባናል" የሚል የሚያስደንቅ መልስ ሰጡን። ኋላም፣ የመንደሮቻቸውን ደህንነት ከእንዲህ ዓይነቶቹ አጥቂዎች መጠበቅ የእነርሱ ግዴታ እንጂ፣ የእኛ የጊዜያዊ እንግዶች እንዳልሆነ ነግሬያቸው ከዚህም ሌላ፣ የትኛውንም ዓይነት መሣሪያ እንደማንይዝ አሳወቅናቸው። ሽፍቶቹን ለማስፈራራት ዝም ብሎ ጩኸቶችንና በእጅ ባትሪዎቻችን የውሸት ምልክቶችን እንደ ተጠቀምን እውነቱን ስንነግራቸው ሊያምኑን ቢቸገሩም፣ ለእነርሱ ብለን ሕይወታችንን አደጋ ላይ እንደ ጣልን ግን ተረዱን።

ለገበሬዎቹ ከእነርሱ ጎን እንዳለን እና አብዮቱም ለእነርሱ የታሰበ እንደ ሆነ ለማሳየት ብዙ ነገር ያደረግን ሲሆን፣ ከእነዚህም አንደኛው ለገበሬዎች ታዳሚዎቻችን የታሰበ ጨዋታን አዘጋጅተን በጣና ሐይቅ ዳርቻ የወደብ ከተማ በሆነችውና ለጎርጎራ በምትቀርበው የጮሃይት ከተማ ገበሬዎቹን መጥራት ነበር። ከቆላ ድባ የሆኑት ወደ 15 የሚደርሱ ተማሪዎች በዚያ ጣቢያ ሲመደቡ፣ "ሀማፂያን" ተደርገን እንቆጠር የነበርነው እና የማይታዘዙት ተማሪዎች በዚያ ጣቢያ እንታጎር ስለ ነበር ቦታው የግዞት ጣቢያ ተደርጎ ይቆጠራል። በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደ ሰለባዎች ሆነን በአንድ ላይ ስንጣመርና አንድነትን መፍጠር ስንጀምር፣ ሁላችንንም የከረረ በሆነው የማርክሲዝም ጥናት ለማሳተፍ፣ ቀጥሎም ያንን ተከትሎ በተደረገ ብዙኃኑን በትጋት ባገለገለ ሁኔታ እርስ በርስ

እንድንናበብ ለማድረግ ተነሣሽነቱን ወሰድኩ። የቡድኑ መሪ እኔ እንድሆን ከተደረገ በኋላ፣ በጥረቱ ላይ እንዲያግዘኝ ደግሞ የአለማያ ኮሌጅ ተማሪ የነበረው ደሜ ተመድቦልኝ ቀን እና ሌሊት ማርክሲዝምን ማጥናት ስንጀምር ከወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ መላው ቡድን በአንድ ልብ እና ሐሳብ የሚሠራ የወጣለትና የለየለት አብዮተኛ ሆነ። በዚያን ጊዜ የማርክሲዝምን መሠረታዊ ሐሳቦች ለሕዝቡ ማስተማር የሚል ስም የተሰጠውን ቅስቀሳ ሽፋን አድርገን ገበሬዎቹ የፖለቲካ ንቃተ ሕሊና ያላቸው እንዲሆኑ ለማድረግ ማስተማራችንን ግንባር ቀደም ሥራችን አደረግነው። ገና ትናንሽ ወጣቶች እንደ መሆናችን፣ ምንም ልምድና ምሪት ሳይኖረን ያንን በጥበብ መፈጸሙን እንዴት እንደ ቻልንበት በእውነት አላውቅም። ወደ ገጠራማ መንደሮች እየሄድን ገበሬዎቹን በመደብ ትግል፣ በሰብዓዊ መብቶች እና ከሁሉ በላይ ደግሞ በገዛ ማኅበረሰባቸው ውስጥ ለውጦችን ለማምጣት ተዋናዮችና ወኪሎች መሆን እንዳለባቸው አስተማርናቸው።

በንዑሳን ወረዳዎች እንኳን ያሉትን ገበሬዎች ሁሉ በመጋበዝ ተውኔት ጽፈን ድራማ ተጫወትንላቸው። ዕለታዊ ሕይወታቸውን፣ አሳዛኝ ሥቃያቸውን፣ እና ኢትዮጵያ ውስጥ እየሆነ ባለው ቀጣይነት ባለው አብዮት ውስጥ ለመካተትና ለመሳተፍ ደስ የሚሰኙበት ፍላጎት በአሁኑ ጊዜ የሌላቸው መሆኑን ጭምር አሳየናቸው። ተውኔቱን ልክ እንደ እነርሱ የምንተውን እንደ መሆኑ፣ ቋንቋዎቻቸውን እንናገር ስለ ነበረ ትክክለኛ ስሜት የሚሰጣቸውና ለገበሬ ታዳሚዎቻችን ተብሎ የቀረበ አስደናቂ ድራማ የእውነት ተጫወትንላቸው። አነስተኛ የአካባቢው ሹማምንትን ጨምሮ ከአካባቢው የሆኑ ሰላማዊ ሰዎችን ያካተተው ተመልካች እጅግ በጣም ተደሰቱበት።

ይሁን እንጂ፣ የገበሬዎቹን ትብብር በማጠናከር ሐሳብ ላይ የበለጠ ወደ ፊት ስንገፋበት፣ አንዳንዶቹ ግለሰቦች እንደ ገዳማት ወይም የገበያ ስፍራዎች ባሉ ሕዝባዊ ስፍራዎች ላይ በይፋ ስለ ተናገርነው ጥላቻቸውን ምሥጢር ባልሆነ መልኩ መግለጽ ጀመሩ። በዚህን ጊዜ፣ በቁጥጥር ሥር ልናውላቸውና በአካባቢው የፖሊስ ጣቢያዎች ልናስራቸው ኃላፊነት ወስጄ ተንቀሳቀስኩ። መብታቸው እና ፍላጎታቸውን የተጋፈጥንባቸው ግለሰቦች ላይ እንዲህ ያለ ጥቃት ፈጻሚ ተግባር ማድረጉ ጠባብነት ብቻ ሳይሆን፣ አላዋቂነትም ጭምር መሆኑን ያስተዋልኩት ግን ዘግይቶ ነበር።





ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ በእኛ እና ተግባሮቶቻችን ሕጋዊ መሠረት የሌላቸው መሆኑን ነግረውን እስረኞቹን እንድንለቅቃቸው በጠየቁን በአካባቢው አስተዳዳሪ እና የፖሊስ መኮንን መካከል አለመግባባቶች ተነሡ። በእርግጥም፣ ገበሬዎቹን ቋሚ እና በሕግ የጸኑ ምክንያቶች ሳይኖሩን ለቀናት የማሰር መብት ስላልነበረን፣ አቋማቸውን ለገለጹበት ተራ ምክንያት በመታሰራቸው ተጠያቂዎች የምንሆነው እኛ ነበርን። በእስር ውስጥ የሆኑት ገበሬዎች ጸረ-አብዮተኞች እና የሰፊው ሕዝብ ጠላቶች መሆናቸውን ለአካባቢው ሹማምንት ብንነግራቸውም፣ ከእስር ስለ ፈቷቸው ይህ ሁኔታ በእነርሱና በሹማምንቱ፣ በተለይም በአካባቢው የፖሊስ ሹም መካከል ኮስታራ ጭቅጭቅ ፈጠረ። ጥላቻው በየዕለቱ እያደገ ሄደና የተቀባበለ መትረየሱን በደገነብን የፖሊስ መኮንን ፊት ለፊት ወደ ፖሊስ ጣቢያው በመሰለፍ መፈክሮችን እያሰማን ወደ ሕዝባዊ ዐመፅ የሚያድግ ትልቅ ስብሰባ አደረግን። አስታራቂ እንደሚያስፈልግ ሰምቶ ከቆላ ድባ የመጣው የወረዳው ፖሊስ መኮንን ከእርሱ ጎን ሲቆም ፍጥጫው ወደሚንተከተከበት ነጥብ ላይ ደረሰ። የወረዳው አስተዳዳሪ ጣቢያው ውስጥ እያለ የዘመቻው ግብረ-አበሮቻችን የሆኑ ተማሪዎች ዐመፁን ለመቀላቀል አንዳንዶቹ በእግር ሌሎቹ አውቶቡስ በመያዝ ከቆላ ድባ ወደ የጮሃይት በፍጥነት መጡ። የወረዳው ገዢና መኮንኑ ውጥረቱንና የሚፈነዳውን ተቃውሞ ለማርገብ በእኛ መካከል ሲገቡ የፖሊስ መኮንኑ በቁጥጥር ሥር እንዲውል እና ከአብዮቱ ተቃራኒ የሆነ ተግባር በመውሰዱ ለፍርድ እንዲቀርብ ጥያቄ አቀረብን። የወረዳው መኮንን ለመደራደር ሞክሮ ባልተሳካለት ጊዜ የፖሊስ መኮንኑ በድንገት መትረየሱን አውጥቶ፣ "አሁን እኔ ይፋዊ ግዳጄን እየተወጣሁ ባለሁበት በሥራዬ ላይ ነኝ። ከማንም ዘንድ ትእዛዝ አልቀበልም" አለ። አውቶማቲክ መትረየሱን ወደ እኛ በደገነበት ቅጽበት ያስተዋልኩት ነገር ፊት ለፊት የተጋጠምነው እኔ እና እርሱ ብቻ መሆናችንን ብቻ ሆነ። በዚያን ጊዜ የምሩን ከሆነ እንዲተኩስ በድፍረት ስጠይቀው፣ እርሱም፣ "እኔ በሥራዬ ላይ ነኝ፤ ማድረግ ያለብኝን ሁሉ ላደርግ ነው" ማለቱን ቀጠለ። የመሣሪያውን ሳንጃ በእኔ ላይ እንደ ተደገነ፣ ጣቱም በመሣሪያው ምላጭ ላይ እንደ ተጠመደ እርግጠኛ ስለ ነበርኩ ከመተኮስ ያስቆመው ነገር ምን እንደ ሆነ እስከ ዛሬ ድረስ አላውቅም። ያየሁት ነገር እርሱ በመጨረሻ መሣሪያውን ሲጥል እና እጁን ከቆላ ድባ ለመጣው የወረዳው የፖሊስ መኮንን ሲሰጥ ነበር።

ከዚያን ቀን በኋላ አስረናቸው የነበሩት ገበሬዎች ወደ ሽፍትነት ተለውጠው ሊገድሉን እንደሚፈልጉ ስለ ሰማን ዜናው ፍርሃት ጫረብንና ወደ እነዚያ መንደሮች ላለመሄድ በመወሰን በቆላ ድባ ያለው የዘመቻ ጣቢያው ኃላፊ ከጮሃይት እንዲያወጣን ጠየቅነው። ወዲያውኑ የተሰጠን ምላሽ ባለመኖሩ ለቀናት ያክል ምንም ነገር ላንሠራ አድማ ስንመታ በምትኩ የነበረው ሥራችን ቀንና ሌሊት መጠጣትና ስለ ጭንቀቶቻችን ማውራት፣ ደግሞም ታዋቂው አብዮት ቢኖርም ምንም ስላልተነካው ሥርዓት እያለቀስን መቆየት ብቻ ሆነ። በሕሊናችን ሥለነው በነበረው እና በእውነተኛ የሕይወት ሁኔታዎች ውስጥ የገጠሙን መካከል ትልቅ ክፍተት ስለ ነበረ፣ አብዮቱ ትልቅ ተስፋ አስቆራጭ ነገር መሆን ጀመረ። ከዚህ የተነሣ በሚያስፈራ አደጋ ውስጥ ስለ ሆንን በዋናው ጣቢያ የሚገኙትን ጓደኞቻችንን እንድንቀላቀላቸው በውትወታ ጠይቀን ከተደጋገሙ ልመናዎች በኋላ ወደ ነበርንበት መልሰው ወሰዱን።

ያ አጋጣሚ ከተከሰተ ጀምሮ፣ መንግሥትን በተለይም በቆላ ድባ ወረዳ የሚገኘውን የአካባቢውን አስተዳደር በግልጽ መገዳደር በመጀመራችን፣ በዘመቻ ጣቢያችን የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች በጣም የተለየ ተለዋጭ አቅጣጫን መያዝ ጀመሩ። በእኛ እይታ፣ እነርሱ የአብዮቱን አቅጣጫ ለመፈጸም ምንም መነሣሣት የሌላቸው የአሮጌው አገዛዝ አባላት ናቸው የሚል ስለ ነበረ፣ ልክ በዩኒቨርስቲ እናደርገው እንደ ነበረው በከተማው ውስጥ ተደጋጋሚ ሠልፎችን አደረግን። አዲስ የአብዮታዊ ዝማሬዎችን አቀናብረን አሮጌዎቹንም መልሰን እንደሚከተለው ተጠቅምንባቸው፤ *ጥላሁን ለምን፣ ለምን ሞተ? ፋኖ ተሰማራ፣ ፋኖ ተሰማራ እንደ ሆ ቺ ሚኒ እና እንደ ቼ ጉቬራ።*[27]

ውጣ ውረድ ያለበትን አሠራር ስለሚከተሉ እና የጸረ-አብዮታዊ ዝንባሌ ያላቸው በመሆናቸው፣ አንዳንድ የአካባቢው መኮንኖች ከሥልጣናቸው እንዲነሡ መጠየቅ ጀመርን። ምንም እንኳን አንዳንድ ገበሬዎች የተቀለበሱ ቢሆንም፣ አብዛኞቹ የአካባቢው ገበሬዎች ከእኛ ጋር ወግነው ወጡ። በጥቅሉ፣ በጎንደር እና ሌሎችም ዙሪያ-ገብ አካባቢዎች ያሉት ጓደኞቻችንም ጋር እንዲሁ ዓይነት ተስፋ መቁረጦች እንዳሉና መንግሥትም ተገቢውን እርምጃ እንደማይወስድ መረዳት ስንጀምር፣ የበለጠ እየጨመረ የሚሄድ ግልጽ ተቃውሞ በማድረግ ተጨማሪ አድማዎች እና ሠልፎች ማድረጋችንን ገፋንበት። 'ግሪን' ብለን በዩኒቨርስቲ እንጠራው የነበረው የም ዋና መሪ በሆነበት





ማክሰኞት፣ የሕግ ትምህርት ቤት ተማሪ የነበረው ጥሌ ቁልፍ መሪ በሆነበት በጎርጎራ፣ እና አበ ቁልፍ አበረታች በሆነበት በዳባት ተመሳሳይ ሁከቶች ተቀጣጥለው ነበር። በዩኒቨርስቲ እርስ በርስ እንተዋወቅ የነበርነውና በእነዚህ እየተካሄዱ ያሉ ተቃውሞዎች ላይ ቁልፍ ሚናዎችን እንጫወት የነበርነው በጎንደር ክፍለ-ሐገር ውስጥ አውራ የሆነ ክልላዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴን መረብ መዘርጋት ጀመርን።

መንግሥት የአዲሱን እንቅስቃሴ ቁልፍ መሪ የሆኑትን ከየጣቢያዎቻቸው እንዲለቀሙና እንዲያስራቸው ትእዛዝ መስጠቱን ጭምጭምታ በሰማንበት አጋጣሚ እየተገለጠ ያለውን ሁኔታ በማስተዋል የአካባቢው የመንግሥት መኮንኖች ይገዙብን ጀመር። መኮንኖቹ እኔን እንደ ዋናው ጠብ አጫሪና ችግር ፈጣሪ አድርገው በለዩኝ ጊዜ፣ ለእኔ ቅርብ የነበሩት እና አድማዎችንም ሆነ ሠልፎችን በማቀናጀት ይሳተፉ የነበሩት ግብረ አበሮቼ ለሕይወታቸው በመፍራት አንደኛው ሌሊት ላይ ወደ እኔ መጡና በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር መካከል ባለው በመተማ በኩል አድርገው አገሪቱን ለቅቀው ለመውጣት እንደሚያስቡ ነገሩኝ። ዕዳቸው እንዴት እንደ ተቀናበረ ምንም ፍንጭ ባይኖረኝም፣ ዐቅደውት የነበረው ነገር ግን ለተወሰነ ጊዜ ሱዳን ለመቆየት እና ከዚያም ወደ ጀርመን ለመሄድ ነበር። ከሙስሊም ቤተሰብ የተገኘውና ጫና ፈጣሪ ተናጋሪ የነበረው ደቀ መዝሙሬ በሽር ወደ እኔ ቀርቦ ነገሩን ካጫወተኝ በኋላ በምሥጢራዊ ዕቅዳቸው ውስጥ ከእነርሱ ጋር እንድቀላቀል ሲጠይቁኝ፣ በተለይ በዚህ የተጋጋለ ቅጽበት ላይ አገሬን የምለቅቅ በቅቧቃ እንዳልሆንኩ ነገርኳቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ ያሰቡበት የምራቸውን ነበርና በሚቀጥለው ቀን እንደ ሄዱ፣ ዘግየት ብሎም እመካከላቸው ያለችውን አንደኛዋን ሴት ሰማይን ጨምሮ አሥራ አንዱም ወደ ሱዳን መግባት እንደ ቻሉ ሰማሁ።

በጎንደር ውስጥ ያለው የፖለቲካ ደመና እየባሰበት ስለ ሄደ እና በጣቢያው ውስጥ ንቁ አብዮተኞች የነበሩት አንዳንዶች በመኮብለላቸው፣ ከመንግሥት የሚመጣብኝን ጫና ብቻዬን ሆኜ እንድሸከም እና እየጨመረ የሚሄድ ዋስትና የማጣት ስሜት እንዲሰማኝ አደረገ። ጎንደር የሚጨምሩና እየባሱ የሚሄዱ የተማሪዎችን ሁከት እና አርማጭሆ ወደሚባል ቁጥቋጦ እንደ ሽፍታ ሆነው የሄዱ የኃይለ ሥላሴን ታዋቂ ሹማምንትን ጨምሮ የአካባቢውን ሕዝብ ፅመፅ ታስተናግድ ጀመር። የበጌምድር ገዢ የነበሩት ፊታውራሪ በዛብህ በአካባቢው

ሕዝባዊ አድማ ላይ በደብረ ታቦር አካባቢ ጣልቃ ሊገቡ ሲሞክሩ ሕይወታቸውን በማጣቸው የዘመቻ አብዮተኞች እና ቆስቋሾች በክልሉ ለተነሡ ለእነዚህ ያልተረጋጉ ሁኔታዎች ተጠያቂ ተደረጉ።

የአካባቢው ፖሊስ ለእኛ የወገኑትን አቦሃየ አለማየሁ የተባሉትን ቄስ ስላሰራቸው፣ ሁኔታው በቆላ ደባ የነበረንን ተቃውሞ ያቀጣጠለ አንድ ክስተት ሆነ። ጉዳያችንን ካስተናገዱ እና የአካባቢው ቤተ ክርስቲያን ቄስ ሆነው ሳሉ በአመዛኙ ማርክሲዝምን ከተቀበሉ ሰዎች አንደኛው እርሳቸው ነበሩ። እንዲለቀቁ መጠየቃችንን ብንቀጥልበትም፣ ግትሮቹ የአካባቢው ሹማምንት የዙሪያ-ገባውን ዐመፅ በማነሣሣት ከሰሷቸውና ሊለቋቸው ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። ያ ሁኔታ ተስፋ ስላስቆረጠን፣ በከተማው ውስጥ ተከታታይ ሠልፎችን እንድናደርግ አስገደዱን።

በጮሃይት አስረናቸው የነበሩት ገበሬዎች እንዲሁም የአካባቢው የደህንነት መኮንኖች ጭምር ሊገድሉኝ እያሤሩ እንደ ሆነ ስለ ሰማሁ፣ ጊዜ እየገፋ በሄደ ቍጥር ስለ ሕይወቴ የበለጠ ዋስትና እንዳጣሁ ተሰማኝና የማምለጫ ሤራዎችን አዘጋጀሁ። የዘመቻ መኮንኖቹን ለማሳመን በአእምሮ ሕክምና ተቋም ውስጥ የሕክምና እርዳታ እንደሚያስፈልገኝ አስመስዬ ያልተለመዱ ነገሮችን ሳደርግ ጊዜ ወደ ጎንደር ሆስፒታል ተወሰድኩ። የገጠመኝ የሕክምና ሰው ዶ/ር አደም ከትውልድ አካባቢዬ ከሐረር የተገኘ አደሬ ስለ ነበር፣ ስለ ሁኔታዬ የእውነቱን ነግሬው ብቸኛው የሥነ-ልቡና ተቋም ወደ ሆነውና አዲስ አበባ ወደሚገኘው አማኑኤል ሆስፒታል መተላለፊያ (ሪፈር) እንዲጽፍልኝ ጠየቅሁት። ግልጥልጥ ያለውን እውነት ከነገርኩት በኋላ፣ ይህን ማድረጉ ከሙያው ሥነ-ምግባር ጋር የሚጻረር በመሆኑ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ፍርጥ አድርጎ ከነገረኝ በኋላ፣ አንዳች የእንቅልፍ ኪኒን ሰጠኝና ወደ ጣቢያዬ መለሰኝ። የመጀመሪያው ዕቅዴ ሲከሽፍብኝ ከችግሩ ለመውጣት እንደ ብቸኛ መንገድ ያንኑ ማድረግ ነበረብኝና የምር እያበድኩ እንደ ሆነ ለዘመቻ መኮንኑ ለማሳመን በድጋሚ የወፈፌነት ባሕርያትን ማሳየት ጀመርኩ።

አንድ ቀን፣ ከጣቢያው በተመደቡ የሚረዱኝ ሰዎች ጋር ሆኜ በድጋሚ ወደዚያው ዶክተር ተወሰድኩ። በዚህ ጊዜ በአንዳች ዓይነት የአእምሮ ችግር ውስጥ እንደ ሆንኩ አመነና በመንገዴ ላይ የሚያጅበኝ እና የሚንከባከበኝ ፖሊስ መኮንን ተመድቦልኝ አዲስ አበባ ወደሚገኘው አማኑኤል ሆስፒታል አስተላለፈኝ።





## ከዘመቻው መልስ

ዶክተር እንዲያየኝ ወደ ሆስፒታል ተወሰጄ ከታየሁ በኋላ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ እያስመሰልኩ እንደ ሆነ ማንም ባላወቀበት ሁኔታ፣ ወዲያውኑ አልጋ ይዤ እንድታከም አስገቡኝ። በተቋም ውስጥ የሚረዱ የአእምሮ ችግር ያለባቸው እብዶችን ያየሁበት የመጀመሪያው ጊዜ ይሄ ስለ ነበረ፣ ሆስፒታሉ ውስጥ በነበርኩበት የመጀመሪያው ሌሊት የምሬን ፈራሁ። ከተለያዩ ዘመቻ ጣቢያዎች ከባድ የአእምሮ ችግር ኖሮባቸው በዚያ የሚታከሙ በርካታ ተማሪዎች ሲኖሩ፣ አብዛኞቹ የሥነ-ልቡና ችግር ኖሮባቸው በሆስፒታል የተገኙት ጫት በከፍተኛ መጠን ከሚቃምባቸው ከሐረር እና ጉራጌ ክልል የመጡ እንደ ሆኑ ማስተዋል ጀመርኩ። ከእኔ መንደር ከጉርሱም የመጣውን የባለጠጋው ነጋዴ የሼክ አደም ልጅ የሆነውና ፈጽሞ ያበደውን ሰማሌው ሐሰንን ለይቼ አወቅሁት። ቀን ላይ በዚያ ሲዞር ቆይቶ፣ ሌሊት ላይ የአካባቢውን ጋዜጣ ዘቅዝቆ የሚያነበው ሐሰን ምንም እንኳን የአንድ ሰፈር ልጆች ብንሆንም፣ እኔ ማን እንደ ሆንኩ ለይቶ አላወቀኝም ነበር። ከእኔ ጎን አልጋ የነበረው አንድ በጺም የተሞላ እና ከምሥራቅ አውሮጳውያን አገሮች በአንደኛው የትምህርት ቆይታ የነበረው የሚመስል በከፍተኛ ደረጃ የተማረ ሰው የነበር ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ጤነኛ ይመስልና ሌላ ጊዜ ደግሞ መስመሩን ይለቃል። ለማውራት በሚችልበት ስሜት ውስጥ ሲሆን ከእኔ ጋር አንዳንድ ውይይቶችን በመለዋወጣችን ጠልቆ የሚያስብ ሰው እንደ ሆነና አንዳንድ ጊዜም ሐሳቦቹን ለመከተል ከባድ ሆኖ የማገኘው መሆኑን ብዙም ሳልቆይ አስተዋልኩ። ላርጋክቲል የሚባለውን እንክብል ልትሰጠኝ ነርሷ በመጣች ቍጥር በአፌ ውስጥ አስገብቼ በምላሴ ሥር በማቆየት እንደ ዋጥኩት አስመስዬ ወዲያውኑ አወጣውና ነርሷ ስትሄድ እንክብሉን በእጄ አውጥቼ ወደ ሽንት ቤት እወረውረዋለሁ።

ለሁለት ሳምንት ገደማ በቆየሁበት በዚያ ሆስፒታል ሁሉም ዓይነት የአእምሮ በሽተኞች ዘግናኝ ባሕርያትን በሚያሳዩበት ቦታ ሕይወትን የመምራት ፈጽሞ ያልተለመደ ገጠመኝ ስላሳለፍኩ፣ ልምምዶቼን በዕለት ውሎ መመዝገቢያዬ ላይ እጽፋቸው ነበር። ትክ-ረቴን የሳቡትን የተረጋገጠ የአእምሮ በሽታ ያለባቸውን ሰዎች ያልተለመዱ ባሕርያት በአትኩሮት መዝግቤያለሁ። ስለሚጽፈው ነገር ምንም ነገር አይግለጥልኝ እንጂ፤ ደግሞም መልከት እንኳን እንዳደርገው ዕድሉን አይሰጠኝ እንጂ፣ ከጎኔ የነበረውም ሰው እንዲሁ በብዛት